ቁም ነገር



ቁም ነገር
የእርስዎና የቤተሰብዎ መፅሔት

200 ኛ ልዩ ዕትም

እየመጣ ነው!


ምርትና አገልግሎትዎን ያስተዋውቁ!

ቁም ነገር መፅሔት በቅርብ ጊዜ ሳምንታዊ! !

ፀሓፍት አዝናኝ፤ አስተማሪና ቁም ነገር አዘል የጠዐር ትሩፋታችሁን እንድታቀርቡ ትጋበዛላችሁ!

ይቀጥላል...

ማውጫ



10



21



30

7

ይልቅ ወሬ ልንገርህ፡-
ለአንጋፋ አርቲስቶቻችን ስለተሰጠው
የገንዘብ ‹ሽልማት›

10

‹የዲኤንኤ ምርመራ ለሁሉም ህመሞች
ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ ምርመራ ነው›

16

አውሮፓውያን በሽብር
ስጋት ውስጥ

26

የቀበጡ ዕለት ሞት ይገኛል?

ደብዳቤዎቻችሁ

‹ሚዲያዎቻችን ትውልዱን ከማነጽና ባህሉን ከማሳወቅ አንጻር ብዙ እየሰሩ አይደለም›

በቅጽ 13 ቁጥር 196 ላይ ‹የተረት አባት ያጣ ትውልድ› በሚል ትውልዱን የሚያንጽ ሰው ማነው በማለት ያደረጋችሁት ሰፊ የዳሰሳ ጽሁፍ በእርግጥም ብዙዎቻችን ልብ ያላልነው ወይም እያየን እንዳላየን ያለፍነው ትልቅ አደጋ የሚጠቁ ጹሁፍ ነው፡፡ በግልጽ እንደሚታየውም ሆነ እናንተም በጹሑፋችሁ እንደገለፃችሁት በአሁኑ ጊዜ ትውልዱ አቅጣጫውን እየሳተ እንዳለ ያሳያል፡፡ ለዚህ ደግሞ በቀጥታ ተጠያቂ እንደኔ አመለካከት ከወላጅና ት/ቤቶች ቀጥሎ ሚዲያው ነው ፡፡ በሀገራችን ያሉ ሚዲያዎች ትውልዱን ከማነጽና ባህሉን ከማሳወቅ አንጻር ብዙ እየሰሩ አይደለም ብሎ ለመናገር ያስደፍራል፡፡ እንደውም የአውሮፓዊያኖችን ባህልና አኗኗር የሚያሳዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን በቀጥታ በመቅዳት፤ ከኛ ሀገር የአኗኗ ዘይቤ ፣ኢኮኖሚና ባህል ጋር የማይዛመድ የብልጭልጭ ህይወት ልጆቻችንን እያስተማሩብን ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ምሳሌ መጥቀስ ካስፈለገ በአረብ ሳተላይት ላይ በ(mtv) ቻናል ላይ (mtvs 16) የተሰኘ የሀብታም ልጆች ልደታቸውን ለማክበር የሚያደርጉትን ትርምስ እንደ ወረደ በሀገራችን በሚታየው የ(ebs)የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ ለልጆቻችን ሲያቀርቡ እያየን ነው፡፡ ይህ ሲሆን ሃይ የሚል አካል አለመኖሩም በጣም ያሳዝናል፡፡ ትውልዱን ለማነጽና ማንነቱን እንዲያውቅ ለማድረግ ከወላጅና ት/ቤቶች ቀጥሎ ሚዲያውና የኪነ -ጥበብ ስራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው መዘንጋት የለበትም፡፡ እናንተም እንደ አንድ የሚዲያ አካል የሚጠበቅባችሁን ሃላፊነት ስለተወጣችሁ ልትመሰገኑ ይገባል፡፡

መስጌታ ስጦታው /ከፈረንሳይ/

‹አርያ የሚሆኑ ሰዎች መኖራቸው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው›

ውድ ቁም ነገሮች ባለፈው እትምታችሁ በቁጥር 195 ላይ ‹አስራ አራት ዓመት በፍቅር ደብዳቤ ፍቅር› በሚል ለረጅም አመት በደብዳቤ ብቻ ፍቅረኛሞች ስለሆኑትና አሁን በትዳር ዓለም ስለሚገኙት አቶ ስዩም ገ/ፃዲቅ እና ወ/ሮ ገነት ጥጋቡ ያቀረባችሁት ታሪክ በጣም የሚያስገርም ነው፡፡ ሰው በአሁኑ ሰአት እንኳንስ አስራ አራት አመት በፍቅር፣ ያውም ሳይተያዩ በደብዳቤ ብቻ አብሮ ሊዘልቅ ይቅርና አራት ዓመት በትዳር መቆየት አቅቶታል፡፡ እንደነሱ ያሉ አርያ የሚሆኑ ሰዎች መኖራቸው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡ ይህ ጽናታቸውም በተገናኙ በወራቸው ለሚለያዩ ፍቅረኛሞች፣ በተጋቡ ደግሞ በዓመታቸው ለሚፋቱ ባለትዳሮች ጥሩ ትምህርት የሚሆን ይመስለኛል፡፡

ሰላማዊት ሰይፉ /ከሳሪስ/

‹ጥሩ ምሳሌ ነው›

ውድ የቁም ነገር መጽሔት አዘጋጆች እንዴት ሰነበታችሁ? የመጽሔታችሁ የዘወትር ተከታታይ ነኝ፤ ባለፈው እትምታችሁ በቁጥር 195 ላይ ስለ ‹ዓለማችን ምሑራን የሀገራት መሪዎች› በሚል የመሪዎቹን የትምህርት ሁኔታ ያቀረባችሁትን አንብቤዎለሁ፡፡ ባለፈው ጊዜ የኢትዮጲያው ጠቅላይ ሚንስትር በዓለም ሦስተኛ ምሑር እንደሆኑ አንድ የህንድ ጋዜጣ እንደፃፈ ሰምቼ ነበር፤ይህ እናንተ አሁን ያቀረባችሁት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የኛን ጠቅላይ ሚንስትር ሦስተኛ ናቸው ላሉ አካሎች ጥሩ ምላሽ ነው፡፡

መኳንንት አባተ/ከ6ኪሎ/

‹ሐሳቡ ባሐይቅረጥ ጥሩ ነበር ›

ውድ የቁም ነገር መጽሔት አዘጋጆች እንዴት ሰነበታችሁ? የመጽሔታችሁ የዘወትር ተከታታይ ነኝ ፤ በተለይም ይልቅ ወሬ ልንገርህ የሚለው አምዳችሁ አዳዲስ መረጃዎችን የማገኝበት ስለሆነ በጣም እወደዋለሁ፡፡ በአሁኑ እትምታችሁ ግን በቁጥር 195 ላይ በዚሁ እትምታችሁ ላይ ‹ ስለአርቲስቶቻችን የደደቢት ጉብኝት › በሚል አንዲት በስፍራው የተገኘች ጋዜጠኛ ያቀረበቸውን ጹሁፍ አንብቤው ነበር፤ነገር ግን በጹሁፉ ላይ የአስቴር በዳኔ ጥያቄዎችን ስትጽፍ ሐሳቡን ቆርጣ ነበር ፤ ይህ ባይሆን ጥሩ ነበር ፤ አሁንም ቢሆን ከተቻለ የአስቴር በዳኔ ጥያቄዎቹ ሙልውን ብታቀርቡት ደስ ይለኛል፡፡ በተረፈ ቸር ይግጠማችሁ፡ :

ሰናይ ገ/አምላክ ከ/ሲኤምሲ/

የሚቀጥለው ዕትም
ቁምነገር መፅሔት ቁጥር 197 ጥር 30 ቀን 2007 ዓ.ም ይጠብቀት!





ለቁም ነገር እንሰራለን!

በቁም ነገር ሚዲያና ኢንተርቴመንት
ኃ/የተ/የግ/ማ ሥር እየታተመ በየ15 ቀኑ የሚወጣ በኪነ ጥበብና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መፅሔት

በ1994 ዓ.ም ተመሰረተ

13ኛ ዓመት ቁጥር 196

ዋና አዘጋጅ፡- ታምራት ታይሉ / 0911 23 20 15
የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 13/14 የቤት ቁጥር 212
አዘጋጆች፡- ፍስሃ ጌትነት
- ሳምሶን አብደላ
ሪፖርተር፡- ትዕግስት ታደለ
አማካሪ፡- ካሣ ለገሠ (ከ አሜሪካ ቨርጂኒያ)
ግራፊክስ ዲዛይነር፡- ተክለ ኪዳነ አምባዬ
ኮምፒውተር ፅሁፍ፡- አለምብርሃን ሃፍቱ
ሽያጭና ስርጭት፡- ቴዎድሮስ ንጉሴ /0913-887175/
ሕትመት ክትትል፡- በዛብህ ተክሉ/0911-416800/
የሕግ አማካሪና ጠበቃ፡- ጳውሎስ ተሰማ
/0911-234441/
የዘግጅት ክፍሉ አድራሻ
ቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 17/18 የቤ.ቁ 401
ካሳንቺስ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ወረድ ብሎ
ምናለ ህንጻ አንደኛ ፎቅ
ስልክ፡- 011-5-507410 / ፋክስ፡-011-5-507410
ፖስታ፡- 25099 ኮድ 1000 አ.አ
ኢሜይል፡- kumneger10@gmail.com
አታሚ ፋኖስ ጌት አታሚዎች
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 15 ቀበሌ 04 የቤ.ቁ334
ስልክ፡- 011-4700324

ከአዘጋጁ

ጣይቱ እመቤቲቱ
ጣይቱ እመቤቲቱ
የኛ ድራማ ዘማሪያን

ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረውና ከአዲስ አበባ መቆርቆር ጋር ተያያዘ ታሪኩ የሚወሳለት የከተማችን ብቻ ሳይሆን የሀገራችን የመጀመሪያው ሆቴል ‹ጣይቱ ሆቴል› ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ላይ በእሳት ስለመቀጣጠሉ በሰፊው ተዘግቧል፡፡

ዘመናዊ ስልጣኔን ወደ ሀገራችን በማስገባት በኩል ግንባር ቀደም የበሆኑት በዳግማዊ አጤ ምንሊክ ባለቤት እቴጌ ጣይቱ ስም የተሰየመውና የተቋቋመው ሆቴሉ የዘመኑ የጥበብ አሻራ ያረፈበትና እንግዶችን በቤት ውስጥ ከማስተናገድ ባለፈ ድግስ ሳይደግሱ ግብግ ማካሄድ የሚቻልበትን አዲስ ስርዓት ያስተዋወቀ ሆቴል ነው፡፡

እቴጌዋም ይህንን አዲስ ሆቴል ከፍተው ስራ በጀመሩበት ወቅት በወቅቱ በነበረው ባህላዊ አስተሳሰብ የተነሳ ብዙም ደንበኛ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ራሳቸውና ባለቤታቸውን እንዲሁም አልፎ አልፎም መኳንንቶቻቸውንና መሳፍንቱን በነፃ ይጋብዙበት እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡

ይህ ታሪካዊ ኪነ ህንፃ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ያለበት በበቂ እንክብካቤና ጥገና መሆን እንዳለበት ግልፅ ነው፡፡ ከቸልተኝነትም ሆነ ከንዝህላልነት በሆቴሉ ላይ የደረሰው የእሳት አደጋ በትላንት ማንነቱ የሚኮራ ኢትዮጵያዊን ልብን ሰብሯል፡፡


በሆቴሉ ላይ የእሳት አደጋ በደረሰበት ዕለትም የመንግስት ከፍተኛ የስራ ሀላፊዎች በስፍራው በመገኘኘት የጉዳት መጠኑን ሲመለከቱ ታዝበናል፡ ፡ መንግስት የዚህ አይነት ታሪካዊ ፋይዳቸው ከፍ ያሉ ቅርሶች ላይ ጉዳት ከደረሰ በኋላ ብቻ ሳይሆን ከመድረሱም በፊት የስራ ሀላፊዎቹን እየላከ ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ ሊገመግም ይገባል፡፡

እንደ ጣይቱ ሆቴል ሁሉ በመዲናችን ከከተማዋ መቆርቆር ጋር በተያያዘ ከ200 በላይ ታሪካዊ ቤቶች እንዳሉ ይታወቃልና ጥንታዊ ቤቶቹን በልማትም ሆነ መሰል ሰው ሰራሽ አደጋዎች ከመፍረሳቸውና ከመውደማቸው በፊት አስፈላጊው ትኩረት እንዲሰጣቸው ቁም ነገር መፅሔት ጥሪዋን ታቀርባለች፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን ይባርክ!

ቁም ነገር መፅሔትን በfacebook.com/kumneger magazine ማግኘት ይችላሉ፡፡ ቁም ነገርን ላይክ ያድርጉና ቤተሰብ ይሁኑ!
የቁም ነገር መፅሔት ዕትሞች በwww.afroage.com ድረገፅ ላይ ያገኛሉ!

ያለፈው ዕትም ቁጥር 195




ቁጥር 194



ቁጥር 193





የከተማችን የሌሊት ገመና ‹ማሳጅ›

መነሻ

በቅርቡ ማክቤዝ ሚዲያ ኮሚኒኬሽን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ኤች አይ ቪ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ወሲባዊ ንግድ የሚፈጸምባቸው ማሳጅ(መታሻ) ቤቶች መስፋፋት በወጣቶችና በሴቶች ላይ የሚያስከትሏቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች በሚል ርዕስ አንድ ጥናት አሰርቶ ነበር፡፡ ወሲብና ወሲባዊ ተግባራት የሚፈፀምባቸውን ማሳጅ ቤቶች በተመለከተ ከማህበራዊ ስነልቦና ባለሙያዎቹ አቶ በላይነህ ዘለለውና አቶ ዮሴፍ አህመድ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው በአዲስ አበባ ከተማ በተለይም ቦሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ መታሻ (ማሳጅ) ቤቶች ውስጥ ህገ ወጥ የሆኑ ማሳጅ ቤቶች በአሳሳቢ ደረጃ ተስፋፍተዋል፡፡ ማሳጅ ቤቶች ለወሲብ ቱሪዝም መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

እንደሚታወቀው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተለያዩ ሃገራት ዲፕሎማቶችና የውጭ ሃገር ድርጅት ሰራተኞች በብዛት ይኖራሉ፡፡ ትላልቅ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችና ጉባኤዎች በተደጋጋሚ ይደረጋሉ፡፡ በነዚህ ጉባኤዎች ላይ ለመሳተፍ የሚመጡ የባህር ማዶ ሰዎች በአብዛኛው ጊዜ አዳራቸውን የሚያደርጉት በህገወጥ ማሳጅ ቤቶችና በትላልቅ ሆቴሎች ውስጥ በግዥ ከሚቀርቡላቸው ሴተኛ አዳሪዎች ጋር አንዳንዴም በደላሎች አማካኝነት ከሚቀርቡላቸው የቤት ልጆች ጋር እንደሆነ ይነገራል፡፡ በዚህ ሂደት በገንዘብ ተጠቃሚ የሚሆኑ በርካታ ሰዎች አሉ፡ ፡ በወጣት ሴቶች ስነልቦና እና ስነተዋልዶ ጤና እንዲሁም በማህበረሰቡ ግብረገባዊ አስተሳሰብ ላይ የሚነግዱ፣ ኢ - ሞራላዊና ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ገንዘብ የሚሰበስቡ ማሳጅ ቤቶች ድርጊት በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ይላል ጥናቱ፡፡ ይሁንና ችግሩን ለመፍታት የተደረጉ እንቅስቃሴዎች የሉም ወይም አነስተኛ ናቸው፡ ፡ የዚህ ጽሁፍ አላማ ጥናቱን ጨምቆ በማቅረብ የጉዳዩን አሳሳቢነት በማሳየት የሚመለከታቸው አካላት በፍጥነት ወደተግባራዊ እርምጃ እንዲገቡ ግፊት ማድረግም ነው፡፡

16ኛው “ዓለም አቀፍ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የአባላዘር በሽታዎች ጉባኤ በአፍሪካ” (16th International Conference on AIDS and STLs in Africa – ICASA) ከሦስት ዓመት በፊት በኢትዮጵያ እንደተስተናገደ ይታወሳል፡፡ከዚያ ቀደም ብሎ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ያስደነገጠና ያወዛገበ አንድ ስብሰባ ሊደረግ ታስቦ ነበር፡፡ “የአፍሪካ ግብረ ሰዶማውያን የቅድመ ኮንፈረንስ ማነቃቂያ ስብሰባ” የተባለው ይህ ስብሰባ በተለይ በሃይማኖት ተቋማት ከፍተኛ ውግዘት ገጥሞት ነበር፡፡ በማህበራዊ ድረ ገጾችና በተለያዩ የሃገር ውስጥ ጋዜጦችና መጽሔቶች (ቁም ነገር መጽሔትን ጨምሮ) ብዙ ፅሁፎች በጉዳዩ ዙሪያ ወጥተው ነበር፡ ፡ ለግብረ ሰዶማውያን መስፋፋትና የወሲብ ቱሪዝም እየጨመረ እንዲመጣ ከሚያደርጉ አባባሽ ነገሮች አንዱ የህገ ወጥ ማሳጅ ቤቶች መኖር ነው፡፡ እንደ ታይላንድ ያሉ ሃገራት ለዚህ ምሳሌ መሆን ይችላሉ፡፡

የወሲብ ቱሪዝም ‹ማግኔት›

በቅርቡ በወጣ አንድ ዓለም አቀፍ ሪፖርት ላይ ኢትዮጵያ የወሲብ ቱሪዝም እየተስፋፋባቸው ከመጡ ሃገራት አንዷ መሆኗን «Ethiopia has become a magnet for sex tourism» (ኢትዮጵያ የወሲብ ቱሪዝም ማግኔት እየሆነች ነው) በማለት ይገልጻታል፡፡ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ጉባኤዎችንና ስብሰባዎችን ማስተናገዷ እያስገኘላት ከሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ገቢ በተጓራሪ ለማህበራዊ ችግሮች እየዳረጋት መሆኑ ተጠቁሟል፡፡ ወደ ሃገሪቱ የሚገቡ የውጭ ሃገር ጎብኝዎችና የጉባኤ ተሳታፊዎች ለመጤ ባህሎች እያጋለጧት ነው፡፡ በመጠጥ ቤቶችና በተለያዩ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች የሚዘወተረው ወሲባዊ ንግድ ወደ መኖሪያ ቤቶችም ገብቷል፡፡ በተለይ የእንግዳ ማረፊያ ተብለው የተዘጋጁ አንዳንድ ቤቶች ለህገ ወጥ ማሳጅ ቤቶችና ለወሲብ ንግድ መፈጸሚያነት እየዋሉ ነው፡፡

እንደ ተባበሩት መንግስታት የዓለም የቱሪዝም ድርጅት (UNWTO) « የቱሪዝምን ቅርጽ እና መረብ በመጠቀም በማንኛውም የወሲብ ነክ እንቅስቃሴ ላይ ለመሳተፍ የሚደረግ ጉዞ » የወሲብ ቱሪዝም ወይም ዘመናዊ የወሲብ ንግድ ነው ሲል ይገልጻል፡፡

በዓለማችን ከቅርብ አሥርት ዓመታት ወዲህ የወሲብ ቱሪዝምን ህጋዊ ማዕቀፍ እንዲኖረው በማድረግ ለሃገሪቱ እንዲሁም ለዘርፉ ተዋንያን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያመጣ በሚችል መልኩ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

ከእነዚህ ሃገራት ውስጥ ጀርመን፣ ብራዚል ፣ሞሮኮ፣ ዶሚኒካን ሪፐብሊክ እንዲሁም በምርጥ የእግር ኳሰኞቿ የምናውቃት ኔዘርላንድስ ከአጠቃላይ የሃገራቸው ኢኮኖሚ ከ ሁለት እስከ አምስት በመቶ የሚሆነውን ከዚሁ ዘርፍ ይሸፍኑበታል፡፡

ይህ ዘርፍ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በርከት ያሉ አገልግሎት ሰጪዎችን የሚያቅፍ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አየር መንገዶች፣ሆቴሎች የየብስ ትራንስፖርት ተቋማት የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡ :

ከዚህ በተጨማሪ እነዚሁ ሃገራት በድርጊቱ ለሚሳተፉት ሴት ዜጎቻቸው የማህበራዊ ዋስትናን እስከ ጡረታ ድረስ በመስጠታቸው ድርጊቱ የሚያስከትለው ማህበራዊ ቀውስ ዝቅተኛ ቢሆንም ሞራላዊ ተጠያቂነቱ ግን ከፍ ያለ ነው፡፡

በሃገራችን በተለይም በመዲናችን እና በተለያዩ የቱሪስት መናኸሪያ በሆኑ አካባቢዎች ከራቁት ጭፈራ ቤቶች የጀመረው ይህ የዘመናዊ የወሲብ ንግድ (የወሲብ ቱሪዝም) በአሁኑ ሠዓት በርከት ያሉ የወሲብ ንግድ ተቋማትን፣ ሰፊ የድርጊቱ መረብ፣ እሳት የላሱ ደላሎችን እንዲሁም ሰፋ ያለ ካፒታል የሚያንቀሳቅስ እና ወደ ኢንዱስትሪ ደረጃ ሊሸጋገር የደረሰ ተግባር ሆኗል፡፡

በተለይም የሃገራችን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ እየተጠናከረ በመጣበት በአሁኑ ወቅት እየጨመረ ያለውን የወጭ ሃገራት ዜጎችን ፍሰት ተከትሎ ዘርፉ ጠንከር ወደማለት እና የአደባባይ ሚስጥር በሚባለው ደረጃ ላይ ለመድረስ ችሏል፡፡

እነዚህ የወሲብ ንግድ ማዕከላት በዘርፉ ተዋንያን እና ቅርበት ባላቸው ወገኖች ዘንድ «ፍርድ ቤት » በመባል የሚታወቁ ሲሆን የድርጊቱ ተሳታፊ ሴቶች ደግሞ ከፈረንሳይኛ ቃል በተወረሰ ነገር ግን ከድርጊቱ ጋር ምንም ተዛምዶ በሌለው «ትራባዬ» በሚል ስያሜ ይታወቃሉ፡፡

እነዚህን «ፍርድ ቤቶች» እና «ትራባዬዎች» ከውጭ ሃገራት ዜጎች ጋር በማገናኘት ረገድ የአንበሳውን ሚና የሚጫወቱት ደላሎች በተለምዶ «ጋይድ»የሚባሉ ሲሆን የትራባዬዎች (የወሲብ ንግድ ተሳታፊ ሴቶች) ማደሪያ እና መዋያ ቦታ የወሲብ ንግድ ማዕከላቱ «ፍርድ ቤቶቹ» ናቸው፡፡

አንድ ፍርድ ቤት በውስጡ ከ 15-20 ለሚሆኑ «ትራባዬዎች» ደንበኞቻቸው እስኪመጡ የሚገለገሉበት የማደሪያ አልጋ እና ሌሎች ቁሳቁሶችን የሚያሟሉ ሲሆን ለሚጎበኟቸው የውጭ ሃገራት ዜጎችም በውድ ዋጋ የሚሸጡ መጠጦችን ለሽያጭ ያቀርባል፡፡

አንድ የውጭ ሃገር የወሲብ ደምበኛ የመረጣትን «ትራባዬ» ከፍርድ ቤቱ ለአንድ አዳር ወይም ውሎ ይዞ ለመውጣት ከአንድ ሺህ እስከ አምስት ሺህ ብር የሚከፍል ሲሆን እንደየ ፍርድቤቱ ህግ ደግሞ ተጨማሪ የመውጫ የኮቴ የመሳሰሉትን ክፍያ መክፈል ይጠበቅበታል ::

ለአንድ አዳር ወይም ውሎ የተስማማች አንድ «ትራባዬ» ሊከፈላት ከተስማማችው የብር መጠን ውስጥ ከ50-70 በመቶ የሚሆነው በወሲብ ተቋሙ ባለቤት እና በደላሎች የሚወሰድ ነው፡፡

እነዚህ የወሲብ ንግድ ተቋማት በአብዛኛው በትላልቅ ቪላ ቤቶች የሚገኙ ሲሆን በተለይም ከቦሌ ድልድይ እስከ ደምበል፣ በሃያ ሁለት ፣ሲኤምሲ፣ መስቀል ፍላወር እንዲሁም የቱሪስት እንቅስቃሴ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ተበራክተው ይገኛሉ፡፡

ይህ የወሲብ ቱሪዝም ወይም የወሲብ ንግድ ከወሲብ ንግድ ተቋማቱ ባለፈ መሸታ ቤቶችን፣የጫት ማስቃሚያ ቤቶችን ፣ የእንግዳ ማረፊያዎችን እንዲሁም ሌሎች መሰል ተቋማትን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንደማስተሳሰሩ መጠን የሚያዘዋውረው የገንዘብ መጠን ከፍተኛ ቢሆንም ከዚህ ዘርፍ መንግሥትም ሆነ የድርጊቱ ተሳታፊ ሴት እህቶቻችን የሚያገኙት ጥቅም ዘላቂነት ያለው እና ቀጥተኛ ባለመሆኑ በህብረተሰቡ ላይ የሚፈጥረው ማህበራዊ ቀውስ ከፍተኛ ነው፡፡

ምንም እኳን ይህ ተግባር በኢትዮጵያ ህጎች የተከለከለ ቢሆንም ድርጊቱን ከመቆጣጠር አኳያ የመንግሥት ጥረት ዝቅተኛ የሚባል ነው፡፡ለዚህም በከተማችን በርከተው የሚገኙት እነዚህ የወሲብ ንግድ ተቋማት ምስክሮች ናቸው፡፡

በዚሁ በወሲብ ንግድ ላይ በሁለት ጎራ የተከፈሉ አስተያየት ሰጪዎች የሚደመጡ ሲሆን በአንደኛው ወገን ድርጊቱ የሃገሪቱን መልካም ስም እና የማህበረሰቡን ሞራል የሚነካ በመሆኑ የቱንም ያህል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ቢያመጣ ሊወገዝ እና ቁጥጥር ሊደረግበት የሚገባ ተግባር ነው ሲሉ የሚሞግቱ አሉ፡፡ በሌላኛው ጎራ ይህን ተግባር ማስቆም ለሚጠይቀው ቁርጠኝነት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት አሊያም ድርጊቱ ይፋዊ በሆነ መንገድ ተፈቅዶ ከድርጊቱ ተዋንያን ከግብር እና ከሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎችን በመሰብሰብ የሚገኘውን ገቢ በመጠቀም ድርጊቱ የሚፈጥረውን ማህበራዊ ቀውስ መቀነስ ተገቢ ነው ባዮች ናቸው፡፡

የማሳጅ ታሪካዊ ዳራ

የማሳጅ ታሪካዊ አመጣጥ በብዙ ሀገሮች የብዙ ሺህ ታሪክ ያስቆጠረ ነው፡፡ በጥንታዊ ጽሑፎች ላይ ተጽፎ እንደሚታየው በምስራቃዊያንና በምዕራባዊያን ስልጣኔ ሰዎችን ለመፈወስና ለማሻል ሰዎችን በመንካት/በማሸት/ እንደሚያደርጉ ታሪካዊ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ አብዛኛውን በአሁኑ ሠዓት የምንጠቀመው የማሳጅ ዘዴዎችና አቀራረቦች አጀማመራቸው ከጥንቱ የማሳጅ ዘዴዎች ነው፡፡በጥንት ጊዜም ቢሆን ማሳጅን የሰዎችን ህመም ለማሻል፣አደጋን ለማሻል(ጉዳቱን ለመቀነስ)፣ሰዎችን ሰውነታቸውንና አዕምሮአቸውን ዘና ለማድረግ(ለማዝናናት) እንዲሁም ህመምን ለመከላከልና ለማዳን ሲጠቀሙበት ነበረ፡፡

በምስራቁ ዓለም የማሳጅ ታሪክ እንደሚያሳየው ማሳጅ እንደ መለኮታዊ ተዓምር/ Divinely- created system/ ተደርጎ የሚታይበት ሁኔታ ነበር፡፡በህንድ ሀገር ማሳጅን አይሩቨዳ / Ayurveda/ ብለው ይጠሩት የነበረ ሲሆን፣ይህም ህዝብ ይተገበርበት/ይገለገልበት የነበረው ከ3000 ዓ.ዓ ቀደም ብሎ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎችና ቦታዎች እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ ኢሲያ ሀገራትም ተስፋፋተው እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡





በተመሳሳይ ሁኔታ የማሳጅ ህክምና በጥንታዊት ቻይና የረዥም ዓመት ታሪክ ያለው ነው፡፡ይህም የህክምና አይነት ከ2700 ዓ.ዓ አካባቢ ተግባራዊ ይደረግ እንደነበረ የታሪክ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ጥንታዊ ቻይናዊያን ማሳጅን ለህክምና አገልግሎትና ራስን ለማዝናናት ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ወደ አህጉራችን አፍሪካ ስንመጣም ይህ የማሳጅ ህክምና አይነት በተለያዩ ሀገሮች ተግባራዊ መሆን ከጀመረ በሺ የሚቆጠሩ ዓመታት አስቆጥሯል፡ ፡ለምሳሌ በጥንታዊ ግብጽ የእራሳቸው የሆነ የማሳጅ አይነት ይጠቀሙ እንደነበር በፖፒረስ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡የተለያዩ ተመራማሪዎች እንደሚገምቱት ሪፈሎኤሶሎጂክ/Reflexology/ የሚባለው ማሳጅ አይነት በግብጽ በ2500 ዓ.ዓ አካባቢ እንደተጀመረ ይገመታል፡፡ይህን የማሳጅ አይነት የተወሰነ የሰውነት ክፍልን ብቻ የማሻል ስራ ላይ ያተኩራል፡፡(በሀገራችን ወጌሻ ጋር እንደምንሄደው)

በተለያዩ ጊዜያት እንደሚታየው ማሳጅ የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳለው ቢታወቅም ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወደቀ እየተነሳ የቆየበት ሁኔታ ስለነበረ አንዳንድ ባለሙያዎች በተለይም ከጥቂት መቶ ዓመታቶች በፊት ጠቀሜታው ወሳኝ እንደሆነ በመረዳት በ1600 ዓ.ም አከባቢ በምዕራባዊያን የህክምና ባለሙያዎች ድጋሚ ጠቀሜታውን በመገንዘብ ለአገልግሎት እንደ ገና ማዋል ተጀመረ፡ ፡ሆኖም ግን እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ማሳጅ ከፍተኛ እውቅና በማግኘት በብዛት ጥቅም ላይ መዋል ጀመረ፡፡

አዲሱ ጥናት

በቅርቡ ማክቤዝ ሚዲያ ኮሚኒኬሽን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና ኤች አይ ቪ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ወሲባዊ ንግድ የሚፈጸምባቸው ማሳጅ ቤቶች ላይ ትኩረት አድርጎ የተሰራው ጥናት ዋና ዓላማ ‹‹በሀገራችን መዲና በሆነችው አዲስ አበባ መጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች በተለይም የተለየ ወሲባዊ ንግድ የሚፈጸምባቸው መታሻ/Massage parlor/ ማረፊያ ማሳጅ ቤቶች መስፋፋት እያስከተለ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፤የስነተዋልዶ ጤና እና ስነልቦናዊ ተፅዕኖዎች እና ቀውሶች በሚመለከት ለቸግሩ መነሻ ፣ አባባሽ ምክንያቶች እና የምክረ ሀሳብ/ የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ እንደሆነ›› ይገልፃል፡፡

መጤ ባህልና ልማዳዊ ድርጊቶች በወጣቶችና ሴቶች ላይ የሚያደርሷቸው ተጽዕኖዎች በርካታ መሆናቸውን የሚጠቅሰው ጥናቱ በአፍሪካ ሀገራትም መጤ ባህል በአምራች ትውልዱ ላይ አሉታዊ ተጽኖ እያሳደረው እንደሆነ እንደ አብነትም ለምሳሌ፡ -በግብጽ ፤በሊቢያ(ከጎረቤት ሀገር)፤በሞሮኮ(ወንደኛ አዳሪነት..)፤በኬፕ ቬርዴ(የወሲብ ቱርዝም)እንዲሁም በናይጄሪያ(በፍተኛ ወሲብ ንግድ የሚተዳደሩ ሴቶችን ወደ ሌሎች ሀገሮች በመላክ የቀዳሚውን ድርሻ ከያዙት ሀገራት ውስጥ እንደሆኑ ያብራራል፡፡

ጥናቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ፤ ማለትም ከማሳጅ ማሰልጠኛ ተቋማት፣፤ ከማሳጅ ቤት ተጠቃሚዎች ፤ ከማሳጅ ቤት ሰራተኞች ጋር በርእሱ ዙሪያ ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተሰራ ሲሆን ከዚህ ‘በተጨማሪም በአሳታፊ የአካል ምልከታ ማሳጅ ቤቶችን በመቃኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል ይላል ::

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አስር ክፍለ ከተማዎች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህ ክፍለ ከተማዎች ማሳጅ የሚከናወንባቸው ቦሌ187 ፣ጉለሌ 5 ፣የካ 20፣ አዲስ ከተማ 9 ፣አቃቂ ቃሊቲ 0 ፣ቂርቆስ 77 ፣አራዳ 10 ፣ንፋስ ስልክ 30 ፣ልደታ 3፣ ኮልፌ 8 ሲሆኑ በጠቅላላው 349 (ሶስት መቶ አርባ ዘጠኝ) ማሳጅ ቤቶች ከአዲስ አበባ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ፈቃድ አግኝተው በመስራት ላይ እንደሆኑ ጥናቱ ያመለክታል :: አብዛኛዎቹ የሚገኙትም ቦሌ አካባቢ በመሆኑ ቦሌ ክ/ከተማ ውስጥ ከሚገኙ 187 ማሳጅ ቤቶች ውስጥ 35 የሚሆኑ ማሳጅ ቤቶችን በመምረጥ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ የማሳጅ አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውም ትላልቅ ህንፃዎች፣ ሰፋ ያለ ግቢ ያላቸው ቤቶች፣ አፓርታማዎችና በከተማዋ ዋና ዋና አካባቢዎች በሚገኙ ፎቆች ላይ የሚገኙ ቤቶች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከእነዚህ ማሳጅ ቤቶች መካከል አብዛኞቹ ወደ ህገወጥ ተግባራት እየገቡ ሲሆን ጥናቱ እንደሚለው ለህገወጥ ማሳጅ ቤቶቹ መስፋፋት ተከታዮቹ ምክንያቶች በዋናነት ይነሳሉ፡-

- ወሲባዊ ንግድ የሚፈጸምባቸው ማሳጅ ቤቶች ለባለቤቱና ወሲባዊ ንግድ ለሚትፈጽሙ ሴቶች ከፍተኛ ገንዘብ ስለሚያስገኙላቸው፣

- ተገልጋዮቹ የተሻለ ነጻነት እንዲሰማቸው ስለሚያደርግ፣

- ወሲባዊ ንግድ የሚፈጽሙ ሴቶች በሆቴልና በጎዳና ላይ ከሚያደርጉት ወሲባዊ ንግድ የማሳጅ ቤቱ በተሻለ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ስለሚያደርግላቸው፣

- ደላሎች ከዚህ ስራ የተሻለ ገንዘብ እያገኙበት ስለሆነ ስራውን እንዲስፋፋ አድርጎታል፣

- ወሲባዊ ማሳጅ ቤቶች ተጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍል እየጨመረ መምጣቱና ሌሎችም ምክንያቶች እንዳሉት ጥናቱ ደርሶበታል፡፡

ከገቢ አንፃርም በእነዚህ ማሳጅ ቤቶች ውስጥ መስራት ስለሚያስገኘው ገቢ በጥናቱ ውስጥ የተካተተ አንድ ሰራተኛ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቶ እናገኛለን፡፡ ‹‹በአሁኑ ሰዓት በመዲናችን ስትዟዟር በተለይም ደግሞ ቦሌ ክ/ከተማ ዞር ዞር እያልክ ብታይ ልክ እንደ ካፌ በየአካባቢው ወሲባዊ ንግድ የሚፈጸምባቸው ማሳጅ ቤቶች ተከፍተው ታገኛለህ፡፡ለዚህ ስራ በዋናነት ምክንያት የሚሆነው ደግሞ ለተጠቃሚው የሚሰጠው ተጨማሪ አገልግሎት (ወሲብ) ነው፡፡ለምሳሌ እኔ እሰራበት የነበረው ቤት ወደ ስድስት ማሳጅ የሚደረግባቸው ክፍሎች ነበሩት፡፡ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከምንሰራው ስድስት ወጣቶች ውስጥ እኔ ብቻ ነኝ ወንድ አምስቱ ሴቶች ናቸው፡፡እኛ ሁሌም ቀን ቀን ነው የምንሰራው፡፡ ማታ ፈረቃ የሚሰሩ በሙሉ ሴቶች ናቸው፡፡ እያንዳንዳችን በቀን ወደ 25 የሚጠጉ ደንበኞችን እናስተናግዳለን፡፡የማታ ፈረቃ ሰራተኞች ደግሞ ከ25 በላይ የሚሆን ሰው ያስተናግዳሉ፡፡በቀላሉ 50 ሰዎች ቢያስተናግዱ ለአንድ ሰው ዝቅተኛው ከ500 ብር እስከ 1200 ብር ያስከፍላሉ፡፡ በትንሹ 500 ብር ቢያስከፍሉ በአንድ ቀን 25,000 ብር ያገኛሉ ማለት ነው፤በወር ደግሞ 750,000 ብር ያገኛሉ፡፡ለሰራተኞችና ለአንዳንድ ወጪዎች 250,000 ብር ቢያወጡ ወደ 500,000 ብር ያገኛሉ፡፡በዚህም ምክንያት ማሳጅ ቤቶች እጅግ በፈጣን ሁኔታ እየተስፋፉ ይገኛሉ ፡፡›

እንደዚህ ያለው ስራ በአብዛኛው ሀገር እጅግ በጣም የሚያዋጣ የስራ ዘርፍ ነው፡፡ እንደ ታይላንድ ያሉ ሀገሮች በወሲብ ንግድ በዓመት ውስጥ ወደ 4.3 ቢሊየን ዶላር ያገኛሉ ከወሲብ ንግድ ብቻ፡ : ይህም ብዙ ሰዎች በእንደዚህ አይነት ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ከሚያደርጓቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ እንደሆነ በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በአሜሪካ በተደረገ አንድ ጥናት መሰረት ወሲባዊ ንግድ ወደሚፈጸምባቸው ማሳጅ ቤቶች ስራ እንዲሰማሩ ምክንያት ከሆናቸው አንዱ ህጋዊ ማሳጅ ሲሰሩ የሚያገኙት ገንዘብ ዝቅተኛና ስራው አድካሚ ስለሆነ ወሲባዊ ንግድ ላይ ቢሰማሩ ግን በቀላሉ በዛ ያለ ገንዘብ ስለሚያገኙ ወደዚህ ስራ ይገባሉ ይላል ጥናቱ፡፡

ወደ ገጽ 33 ዞሯል



ደልቅ ወሬ ልንገርህ



ለአንጋፋ አርቲስቶቻችን ስለተሰጠው የገንዘብ ‹ሽልማት›

መቼም የሀገራችን የመጀመሪያው እንደሆነ ስለሚነገርለት ቴአትር ቤት አላውቅም አትለኝም፡፡ አንጋፋው ቴአትር ቤት ሀገር ፍቅር በጠላት ፋሽስት ወረራ ወቅት ተቋቁሞ የተለያዩ አርበኝነትን የሚያበረታቱ ዜማችንንና ድራማዎችን ያቀርብ እንደነበር መቼም ታውቃለህ አይደል?

እናስ? አንጋፋው ቴአትር ቤት ምን ሆነ? ምንም አልሆነም፤ ቴአትር ቤቱ ዘንድሮ የተመሰረተበትን 80ኛ ዓመት ልደት ለማክበር ተፍ ተፍ እያለ እንደሆነ ተሰምቷል፡፡ እናስ? እናማ የዚሁ ክብረ በዓል አካል ይሆናል የተባለ አንድ ዝግጅት ላይ ባለፈው ሳምንት በቴአትር ቤቱ ቅጥር ግቢ ተዘጋጅቶ ነበር፡ ፡ እናስ? ተገኘኋ!

እናልህ በዚህ ዝግጅት ላይ ቴአትር ቤቱ ሲመሰረት የነበሩ ሰዎች በህይወት ባይኖሩም ከ60 እስከ 70 ዓመት ድረስ ከቴአትር ቤቱ ውስጥ ያልጠፉና በመድረክም ልዩ ልዩ ስራዎችን በማቅረብ ህዝቡን ሲያዝናኑ የነበሩ አንጋፋ አርቲስቶች ተገኝተው ነበር፡፡ አንጋፋ አርቲስቶቹ የጥንት ዜማዎችን በቡድን በቡድን ሆነው ሲጫወቱ ለተመለከተ ‹የሀገር ፍቅር እውነትም አልሞተም › ለማለት ይገደዳል፡፡

እናስ? እናማ እነዚያ አንጋፋ አርቲስቶች በየተራ እንዲሁም በቡድን ወደ መድረኩ እየወጡ ያንን በቲቪ ብቻ የምናውቀውን የድሮ ዘመን ሲያስታውሱን አምሽተዋል፡፡ ግን ግን አንዳንዶቹ በዕድሜ መግፋትም ይሁን በጤና መታወክ ሳቢያ እንደዚያ እንደ እንዝርት ሲሾሩበት በነበረው መድረክ ላይ መውጣት ሲያቅታቸውና በድጋፍ ወዲያና ወዲህ ሲሉ መመልከት ልብን ይሰብራል፡፡

ታዲያ አንጋፋው ቴአትር ቤት እነዚህን አንጋፋ የጥበብ ቤተሰቦች ጠርቶ መድረክ ላይ እንዲወዛወዙለት ብቻ እንዳይመስልህ የጠራቸው፡፡ እናስ ደግሞ ምን አደረገላቸው? ‹ዳጎስ› ያለ ሽልማትም አዘጋጅቶላቸው ነበር፡፡

እንደምታውቀው እነዚህ አንጋፋ አርቲስቶች ሙሉ ዕድሜያቸውን በመድረክ ላይ ጥበብን ብቻ ሲዘሩ ይህ ነው የሚባል ‹ፈረንካ› በእጃቸው እንዳልገባ ግልጽ ነው፡፡የሚተዳደሩትም ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የጡረታ ገንዘብ ነው፡፡ እናስ? እናማ ይህንኑ ከግምት ያስገባ የሚመስለው አዲሱ የቴአትር ቤቱ ማኔጅመንት ‹ላይ- ታች› ወርዶ ስፖንሰር ፈልጎ ለአንጋፎቹ ሽልማት በእለቱ ሰጥቻቸዋል፡፡

ለመሆኑ ሞት ሳይቀድማቸው በአንጋፋው ቴአትር ቤት ልደት ላይ ለመታደም መድረክ ላይ የወጡት አንጋፋ አርቲስቶች ስንት እንደሆኑ አውቀሃል? እኔ እቴ አላወቅሁም 42 ያህል ናቸው፡፡ ታዲያ ለነዚህ 42 አንጋፋ አርቲስቶች ስፖንሰር ተፈልጎ ስንት ስንት ብር ሽልማት የተሰጣቸው ይመስልሃል? ካገለገሉበት ዕድሜ አንፃር ሽልማቱን ለመገመት ያስቸግራል፡፡

አትድከም፤ እኔ እነግርሃለሁ፤ 100 ሺህ ብር፡፡ ለእያንዳንዳቸው ወይስ ለሁሉም? ቴአትር ቤቱ በዚያ ምሽት ወደ ቤታቸው ለመመለስ የታክሲ አጥተው ሲቸገሩ ለተመለከትናቸው ለሁሉም አንጋፋ አርቲስቶች ያዘጋጀው አንድ መቶ ሺህ ብር ነበር፡፡ ስንት ሰንት ደረሳቸው? አካፍለዋ! 100 ሺህ ሲካፈል ለ42፤ ለዚያውም ብሩ የተሰጣቸው እንዳይመስልህ፤ እናስ? እናማ በብሩ የህዳሴ ግድብ ቦንድ ግዙበት ተብለው ሰርተፍኬቱ ነው የተሰጣቸው፤ በል ቻዎ...



‹ምንም አይነት ፀብና ግጭት አስመኖሩ ችግር ደኖረው ይሆን?›

አንዳንድ ጊዜ በትዳሬ ውስጥ አንድ የሆነ የጎደለ ነገር ይኖር ይሆን ስል አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም እኔና ባለቤቴ ፈፅሞ ተጣልተን (ተደባድበን) አናውቅም፡፡ አይደለም መደባደብ ተጨቃጭቀን እንኳን አናውቅም፡፡ በእርግጥ ሁለታችንም የመጣነው እጅግ በጣም ወግ አጥባቂና ሃይማኖተኛ ከሚባሉ ቤተሰቦች ሲሆን ሁለታችንም አባትና እናቶቻችን ሲጨቃጨቁም ሆነ ሲደባደቡ አላየንም፡፡ በብዙ ነገር ተስማምተን እንኖራለን፡፡

በእርግጥ እውነት ስመናገር ትዳራችንና የፍቅር ግንኙነታችን በጣም ፍቅር የተሞላበት የሚባል አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ፀጥ ያለ.... የተረጋጋና ጥንቃቄ የተሞላበት ነው ቢባል ይበልጥ ይገልፀዋል፡፡ ስመሆኑ ውድ አማካሪ የሆነ ያጣነው ነገር ያለ አይመስልህም?

ዮዲት ነኝ ከ/ወሎ ሰፈር/

ውድ ዮዲት፡- ግምትሽ ትክክል ነው፡፡ አ ዎ ን በትክክል ይኖራል፡፡ አንቺና ባለቤትሽ የፈለገውን ያክል የተጣጣማችሁና ፍፁም አብራችሁ የምትሄዱ ብትሆኑም እንኳን ሁለት የተለያያችሁ ሰዎች መሆናችሁን መዘንጋት የለባችሁም፡፡ ምናልባት ነገረኛ ላለመባል እየፈራችሁ ካልሆነ በቀር በየቀኑ አንድ ቤት ውስጥ እየኖራችሁ አንድም ቀን ተጣልተን አናውቅም ማለት የማይመስል ነገር ነው፡፡

እኔ በበኩሌ ፈፅሞ አንጋጭም የሚሉ ጥንዶች ‹ጥንቃቄ የተሞላበት የፍቅር ግንኙነት» (Careful loving) ውስጥ ናቸው ነው የምለው፡፡ ከሁለት አንዳቸው ወይም ደግሞ ሁለቱም ማንኛውም አይነት ግጭት ወይም ፀብ የፍቅር ግኙኝነታችንን ይጎዳል ብለው ይሰጋሉ ፡ ፡ በዚህ የተነሳ በሚችሉት አቅም ሁሉ ፀብን ሲሸሹ ይኖራሉ፡፡ የዚህ ውጤቱ ታዲያ ህይወት ህይወት የማይሸት ደባሪ (አሰልቺ) የሆነ ትዳር ይሆናል፡፡

አንቺም እራስሽ የትዳር ህይወታችሁ ያን ያክል ፍቅር የተሞላበት ነው የሚባል አይነት እንዳልሆነ ነው የገለፅሽው፡፡ ነገር ግን ማወቅ ያለብሽ ነገር ንዴት፣ ቁጣ ሃዘን፣ ብስጭት..... ወዘተ ያሉትን አሉታዊ ስሜቶች በመውሰጣችን አምቀን ስንይዛቸው ፍቅርና ርህራሄ እንዲርቁን እናደርጋለን፡፡ አንቺና ባለቤትሽም እነዚህን የፍቅርና ርህራሄ ስሜቶቻችሁን በደግነታችሁ እየገደላችኋቸው ነው፡፡

እንደ ገለፅሽው አንቺም ሆንሽ ባለቤትሽ የመጣችሁበት ቤተሰብ በአሁኑ ስብዕናችሁ ትልቅ ተፅዕኖ አሳድሮባችኋል፡፡ ብዙ ጊዜ እንደሚታወቀው ቁጥጥር ከሚያበዙ ወይም ወግ አጥባቂና በጣም ሃይማኖተኛ ቤተሰብ የሚወጡ ልጆች እንደ እንዴት ቁጣ .... ወዘተ ያሉ አሉታዊ ወይም ቅዱስ ያልሆኑ ስሜቶች ሃጢያት እንደሆኑ እየተነገራቸው ነው የሚያድጉት፡፡ ፍርሃትም እንደዚያው ሃጢያት ነው ይባላል፡ ፡ የእምነት ማጣት ምክልት ነውም ይባላል፡፡ በዚህ የተነሳ ባለቤትሽ የሚያናድድሽን ነገር እንኳን ቢያደርግ አንቺ የተሰማሽን ስሜት አምቀሽ ትይዥዋለሽ፡፡ ይህ ነገርም በየጊዜው እየተደጋገመ ሲሄድ በመጨረሻ ውጤቱ ታማኝነትና መቀራረብ የራቀው ትዳር ይሆናል፡፡

በእርግጥም መልካሙ ነገር አንቺም ሆንሽ ባለቤትሽ ችግሩን ተረድታችሁ ለውጥ ለማምጣት ፍላጎት አላችሁ፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁሉንም ስሜቶቻችሁን በግልፅነት ለመጋራትና ትዳራችሁን መልሳችሁ እንደ አዲስ ለመገንባት ለራሳችሁ ቃል ግቡ፡፡ ጤናማና ደስታ የተሞላበት ትዳር ለመገንባት የሚረዱ ፅሁፎችን አንብቡ፡፡ የተለያዩ ትምህርታዊ ገለፃዎችን ተከታተሉ፡፡ ከ ሁሉም በላይ ግን ትዳራችሁን በየዕለቱ የሚከሰቱ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን መቋቋም ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንስ እያንዳንዷ ግጭት አልፋችሁ ወደ ፍቅራችሁ በተመለሳችሁ ቁጥር ፍቅራችሁ የበለጠ እያደገ እየጠነከረ እንደሚሄድ ሙሉ እምነት ይኑራችሁ፡፡



‹አርቲስት ፖለቲከኛ ሳይሆን መስታወት ነው›

አርቲስት አስቴር በዳኔ

ሰሞኑን በማህበራዊ ድረገፆች እና አንዳንድ መገናኛ ብዙሃን ላይ ስሟ በተደጋጋሚ የሚነሳው አርቲስት አስቴር በዳኔ የሀገራችን ‹ታዋቂ› አርቲስቶችን ባሳተፈውና ህወሃት የተመሰረተበትን 40ኛ ዓመት ክብረ በዓል ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀው የጉብኝት ፕሮግራም በጠየቀቻቸው ጥያቄዎች መነጋገሪያ አጀንዳ ሆና ሰንብታለች፡፡ አስቴር ስመከላከያ ሚኒስትር ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ስሆኑት ስጄኔራል ሳሞራ የኑስ ባቀረበቻቸው ጥያቄዎች የደነገጡ አንዳንድ የሙያ ጓደኞቿ ሳይቀሩ ‹ማግለልና መድልዎ› ስመፍጠርም ሲሞክሩ ስስመታየታቸው ይነገራል፡፡ የራሷን አቋም በግልፅና በድፍረት በዚያ መድረክ ላይ ካቀረበችው አስቴር በዳኔ ጋር አዲስ አበባ ላይ አጠር ያለ ቆይታ አድርገናል፡፡

ቀም ነገር፡- ሰሞኑን በማህበራዊ ድረ ገፆች ላይ ስምሽ በስፋት እየተነሳ ነው፤ ምንድነው?

አስቴር፡- እንግዲህ ከሰሞኑ የደደቢት ጉዞ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል፡፡ በጉዞው ላይ ለየት ያሉ ጥያቄዎች ጠይቃለች በሚል መሰለኝ የተለያየ ነገር እየተባለ ያለው፡
፡

ቀም ነገር፡- አንቺስ የተሰየ ጥያቄ ጠይቄያለሁ ብለሽ ታስቢያለሽ?

አስቴር፡- ያሉና ሁሉም የሚያውቀውን ህዝቡ ውስጥ ያሉ ጥያቄዎችን ነው የጠየቅሁት፤ አዲስ ነገር አለው ብዬ አላስብስም፡፡

ቀም ነገር፡- በመጀመሪያ አስኪ በጉዞው ላይ እንዴት አንድትሳተፊ እንደተጠራሽ ንገሪኝ?

አስቴር፡- እንደማንኛውም አርቲስት ነው የተጠራሁት፤ ጉዞው እንዳለ የነገረኝ አርቲስት መለሰ ወልዱ ነው፡፡ የህወሃትን 40ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ አርቲስቶችን ወስደው ሊያስነቡኙ አስበዋል አንቺም ተጋብዘሻል ሲለኝ ደስ አለኝ፡፡ እንደ ፊልም ሰሪ ታሪካዊ ፊልም የመስራት ፍላጎት ልቤ ውስጥ ስላለኝ ለወደፊቱ የሚሰራ ነገር አይጠፋም ብዬ ሄድኩ፡፡ወደ እዛ ስንሄድ በቲቪ ብቻ የምታያቸው ባለስልጣኖች ከእኛ ጋር ጃኬት አድርገው መንገድ በመንገድ ሲሄዱ ሳይ ገረመኝ፡፡

ቀም ነገር፡-እነማን እነማን ነበሩ?

አስቴር፡- ዋና ዋናዎቹ ባለስልጣናት ነበሩ፤

> **ግንቦት ሲመጣ 24 ዓመት ይሆናችኋል፤ እና ከዚህስ በኋላ በአዲስ አስተሳሰብና ፍልስፍና ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ በሃርጫ አሸንፌ ሀገሬን ሲመሩ ልናይ እንችላለን ወይ? የሚልም አለ**

እንግዲህ ሁሉንም ላላውቃቸው እችላለሁ፤ ግን የማውቀውን ያህል ጥሪ ካልኩኝ፤ አቦይ ስብሃት፤አቶ በረከት ስምኦን፤አቶ አዲሱ ለገሰ፤ አቶ ስዩም መስፍን፤ ጄኔራል ሳሞራ የኑስ፤ አቶ አባዱላ፤ ዶ/ር ካሱ ኢላላ ነበሩ፡፡

ቀም ነገር፡- ስጄኔራል ሳሞራ ያነሳሽው ጥያቄ ምን ነበር?

አስቴር፡- ከስብሰባው በፊት በአውቶብስ ስንሄድ አብረን ካለን አርቲስቶች ጋር ያው የተለመደ ወሬ እናወራለን፡፡ ሁሉም የመሰለውን ነው የሚናገረው፡፡ እኔ ደግሞ የምናገረው የማምንበትን ነው፡፡ የማስበውን እግዚአብሔር ያውቃል፤ ኑሮዬ ካሜራ ፊት ለፊቱ እንደተደቀነበት ሰው መሆን አለበት ብዬ ነው የማስበው ፡፡ ማስመሰል አልወድም፡፡እና እዛ አውቶብስ ውስጥ ስናወራ የምናወራውን የሰማ አንድ የኢህዴግ አባል የሆነ አርቱስት ‹ለምን ይህንን እዚህ የምታወሩትን መድረክ ተዘጋጅቶ አትናገሩም?› አለ፡፡ እኔ ደስ ይለኛል አልኩና በማግስቱ ነው መሰለኝ የደርግ 604ኛ ክፍለ ጦር የተደመሰሰበትን ቦታ አስንብኝተውን ስንመለስ ስብሰባ ተጀመረ፡፡አዳራሹ በሙሉ ሰው ሞልቷል፤ፖሊሶች ጠባቂዎች አሉ፤ የመከላከያ ሰራዊት አባላትም አሉ፡፡ እና ስብሰባው ተጀምሮ ጄኔራል ሳሞራ ገለፃ ሲያደርጉ አንዳንድ ማስታወሻዎችን እየፃፍኩ ነበር፡፡ ለምሳሌ እሳቸው ሲናገሩ ምን አሉ ‹ለአስር ዓመታት ያህል ስንታገል

ቆይተን ውጤት አልመጣ ሲል በአዲስ አስተሳሰብ ነው ለውጥ ያመጣነው› ብለው ነበር፡፡እንደውም ምንድነው ያሉት ‹አሮጌ አስተሳሰብ አዲስ አስተሳሰብን ለመቀበል ይጎትታል› ብለው ነበር፡፡እንግዲህ እስከ እዛ ቀን ድረስ የተለያዩ የትግሉን ቦታዎች ተመልከተናል፡፡ እና ከእሳቸው ገለፃ በኋላ መድረኩ ለጥያቄ ከፍት ሲሆን አርቲስት አበበ ባልቻ መጀመሪያ ጠየቀ፤ ከዚያ ሳምሶን ማሞ ጥያቄ ጠየቀ/እናንተ እንደውም ባለፈው እትማችሁ ላይ አውጥታችሁታል/ ከዚያ ጥያቄ የሚጠይቅ ጠፋ፤ ቤቱ ፀጥ አለ፡፡ጠይቁ እየተባለ በየሻይ ቤቱና በየምግብ ቤቱ ባለስልጣናቱን በጀርባ ከማማት አሁን ነው መጠየቅ ያለብኝ ብዬ አሰብኩ፡፡ግን ፈራሁ፤ከዚያ ለአቶ በረከት በትንሽ ወረቀት ላይ ‹ ጥያቄ መጠየቅ ፈልጌ ነበር፤ ግን ፈራሁ› ብዬ ላኩላቸው፡፡›

ቁም ነገር፡- እንዴት ስእሳቸው ስደተሽ ደህንን ጥያቄ ጠየቅሽ?

አስቴር፡- ምን ሆነ መሰለህ? ከዚያን ቀን ቀደም ብሎ፤ እዚህ አዲስ አበባ ኤፍኤም ላይ ተንሻፎ ስለእኔ የተወራ ወሬ ነበር፤ በጉዞው ላይ በነበርኩበት ጊዜ ትንሽ አሞኝ ነበር፤ መንገዱም ሙቀቱም በሰዓቱ ምግብም ስለማንበላ አንዳንዴ ከጉብኝት በኋላ በ10 ሰዓት ነበር ምሳ የምንበላው በዚህ በዚህ የተነሳ ታምሜ በየቦታው እቀመጥ ነበር፡፡ የሆነ ቦታ ተቀምጬ ሳለ ከጀርባዬ አንድ ሰው ትከሻዬን መታ መታ አድርጎ ‹ውሃ ጠጪ የእኔ እህት› ሲለኝ፤ ‹እሺ የኔ ወንድም› ብዬ ቀና ስል አቶ በረከት ናቸው፡፡ እንዴት እንደደነገጥኩ ልነግርህ አልችልም፡፡በስመ አብ ሁሉ ብዬ አማትቤ ነበር፡፡ ከዛ በየመንገዱ ላይ ሌሎቹም ባለስልጣናት ሲያገኙን ‹አስቴር እንዴት ነው? በርቺ› ይሉኝ ነበር፡፡ ያ ስብሰባ የተካሄደው ከዛ በኋላ ስለነበር ለአቶ በረከት ወረቀቷን ስልክ አንብበው ‹የፈለግሽውን ጠይቂ› ብለው ምልክት ሰጡኝ፡፡ በወቅቱ ለሴቶች ዕድል ይሰጥ ሲባል ሌላ ሰው ስላልነበረ ለእኔ ተሰጠኝ፡፡ የተቀመጥኩት ከበስተጏላ ግራ ወንበር ላይ ነበር፡፡ የመጠየቅ ዕድሉ ሲሰጠን ግን ማይክ ስለማይደርስ ወደፊት ነይ ተብዬ ፊት ወንበር ላይ ተቀምጬ ነበር የጠየቅሁት፡፡ እንዴት እንደፈራሁ ልነግርህ አልችልም፡፡ አንዳልኩህ ቤቱ በሙሉ በባለስልጣናት ተሞልቷል፡፡ግን እንደምንም ብዬ የፃፍኩትን ወረቀት እያየሁ ጠየቅሁ፡፡

ቁም ነገር፡-ምንድነው የጠየቅሽው?

አስቴር፡-ለምሳሌ ደርግን ለምን ጠላት ብለን እንጠራለን? ከደርግ ውስጥ ያሉ የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው፤ በአይዲዮሎጂ ልዩነት ነው እንጂ በአብዛኛው ንፁህ የኢትዮጵያ ልጆች አሉበት፤ አሁንም ጠላት ማለት ተገቢ ነው ወይ? የሚለው የመጀመሪያ ሲሆን ተቃዋሚ ፓርቲዎችንም ለሀገር ለመስራት ብለው የሚወዳደሩ በመሆናቸው ተፎካካሪ ፓርቲ ለምን አይባሉም? ተቃዋሚ የሚባለው ግን ከስሙ ጀምሮ የግድ መቃወም ያለበት ይመስለዋል፤ ግንቦት ሲመጣ 24 ዓመት ይሆናችኋል፤ እና ከዚህስ በኋላ በአዲስ አስተሳሰብና ፍልስፍና ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫ አሸንፎ ሀገሪቱን ሲመራ ልናይ እንችላለን ወይ? የሚልም አለ፡፡መንግስት ለመቀየር ከዚህ በኋላ የግድ ጦርነት አያስፈልግም፤ ስለዴሞክራሲ ስታስቡ ልባችሁ ምን ይላችኋል? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ነው የጠየቅሁት፡፡

ቁም ነገር፡- ምላሹስ?

አስቴር፡- ጀኔራል ሳሞራ የተቻላቸውን ያህል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ደርግን በተመለከተ ጠላት ያልኩትን ይቅርታ አድርጊልኝ ነው ያሉት፡፡ ትክክል ነው የደርግ ወታደር ተገዶ የሚዋጋ ነው፤ ነገር ግን ምን አለ መሰለሽ በወታደራዊ ውጊያ ውስጥ መጀመሪያ ላይ ተዋጊን ሞት ሞት እንዲሸተው ማድረግ ያስፈልጋል› ሲሉ አርቲስቱ ሁሉ አጨበጨበ፤ ተቃዋሚ ፓርቲን በተመለከተ ተፎካካሪ በሚለው ቢተካ እኔ ተቃውሞም የለኝም ግን አንዳንድ ተቃዋሚ የሀገሩን ጥቅም ለውጪ ሁሉ አሳልፎ የሚሰጥ አለ ብለዋል፡፡

አስቴር፡- ከፕያቄሽ በኋላ በአርቲስቶች በኩል የነበረው ስሜት ምን ይመስላል?

ቁም ነገር፡- ብዙዎቹ ሸሹኝ፤ከእኔ ጎን መሆን ራሱ የፈሩ ነበሩ፤ ትተውኝም የሄዱ አሉ፡፡ የሚገርምህ ግን ባለስልጣናቱም ሆነ የእነሱ ደጋፊዎች እኛ እኮ የታገልነው ማንም ሰው የመሰለውን እንዲናገር ነው፤ ጥሩ ጥያቄ ነው የጠየቅሽው፤ ነበር ያሉኝ፡፡

አስቴር፡- ከዋናዎቹ ጥያቄውን ከተጠየቁት ሰዎች ሳይመጣ ከሙያ ጓደኞችሽ መምጣቱ ምን ስሜት ፈጠረብሽ?

ቁም ነገር፡-አላወቅም፤ እንግዲህ ምናልባት እንደዚህ ብላ ትጠይቃለች ብለው አስበው ላይሆን ይችላል፡፡ ግን ውስጤ አንድ ነገር ነግሮኛል፤ አንዳንዶቹ ደስተኛ ላይሆኑ እንደሚችሉ፡፡ ምናልባትም ትንሽ ደፋር ሳልሆንባቸው አልቀረሁም/ሳቅ/ አንድ አርቲስት እንደውም ማታ ራት ከበላን በኋላ አጠገቤ መጥቶ ምን አለኝ መሰለህ? አንቺ ምን ይሁን ነው የምትይው?› አለኝ፤ ምን ይሁን አልኩኝ? አልኩት ‹ኢህአዴግ ህዝብ እስከመረጠው ጊዜ ድረስ ሺ ዓመትስ ቢነግስ ምን አለበት?› አለኝ፡፡ እኔ ታዲያ ምን ቸገረኝ፤ እኔ እኮ ስለዲሞክራሲ ስለተነሳ ነው ጥያቄ

ወደ ገጽ 27 ዞሯል



በአይነቱ ልዩ የሆነው ዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተር ስራ ጀመረ

በአሜሪካ ከ25 ዓመታት በላይ በህክምና ሙያ ሲያገለግሉ በቆዩ የውስጥ ደዌ ስፔሻሊስት ሀኪሞች እና በሀገር ውስጥ ባሉ ሌሎች ኢትዮጲያዊያን ሀኪሞች ጥምረት የተቋቋመው ዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተር እጅግ ዘመናዊ በሚባሉ የህክምና መስጫ መሳሪያዎችና ባለሙያዎች ተደራጅቶ ባለፈው ቅዳሜ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡

ቦሌ ሩዋንዳ ኤምባሲ ፊት ለፊት የሚገኘው ዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተርን መርቀው የከፈቱት የኢፌዲሪ ንግድ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አሊ ሲራጅ ናቸው፡ ፡ አቶ አሊ በወቅቱ እንደተናገሩት ባለፉት አስር ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ባለችው ኢትዮጵያ ከኢኮኖሚው ጋር የሚጓዙ ደረጃቸውን የጠበቁ የህክምና ተቋማት ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ጠቅሰው በዚህ ረገድ ሀገራቸውን ለማገልገል ወደ ሀገር ቤት በተመለሱ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተከፈተው ዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል፡፡ የዚህ አይነት ተቋማትንም መንግስት ከጎናቸው ሆኖ እንደሚያግዝም ተናግረዋል፡፡

የዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተር ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ማርቆስ ፈለቀ በበኩላቸው ባደረጉት ንግግር የረጅም ዓመታት ሙያዊ እውቀታቸውና ልምዳቸውን ይዘው ወደ ሀገር ቤት በተመለሱ ኢትዮ አሜሪካውያንና በሀገር ውስጥ በሚሰሩ ባለሙያዎች በ60 ሚሊዮን ብር ካፒታል የተቋቋመው ዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተር ካርድ ከማውጣት ጀምሮ በዘመናዊ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚከናወን እንደሆነ ጠቅሰው የታካሚዎች የህክምና ሪከርድም ከወረቀት ነፃ ሆኖ በኮምፒውተር የሚገናኝ እንደሆነና ማዕከሉ የራሱ መድኃኒት ቤት በዘመናዊ አምቡላንስ፤ ዲጂታል የኤክስ ሬይ ማሽን፤ አልትራ ሳውንድ፣ ኢ ኬ ጂ ምርመራ እና ዘመናዊ ላቦራቶሪ የተደራጀ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ማዕከሉ በቀጣይነትም ሙሉ በሙሉ ወደ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በማሳደግ ተደራሽነቱን እና አገልግሎቱን እንደሚያሰፋ ዶ/ር ማርቆስ ጨምረው አስታውቀዋል፡፡

ሀገርንና ወገንን የማገልገል ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ወደ ሀገር ቤት በተመለሱ ስፔሻሊስት ሀኪሞች የተቋቋመው ዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተር አገልግሎቱን ለሁሉም ታካሚ ተደራሽ ሊባል በሚችል ተመጣጣኝ ዋጋ ለሀገር ውስጥና ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ ለሆኑ ዲፕሎማቶችና የውጭ ሀገር ሰዎች በአካል፤በስልክ፤ በኢንተርኔት በሚያዝ ቀጠሮ የማዕከሉን ስፔሻሊስት ዶክተሮች ማግኘት እንደሚቻል የማዕከሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ዶ/ር ፋሲል ተፈራ ገልፀዋል፡፡

‹ለሁሉም የውስጥ ደዌ ህመሞች በሙያው የካበተ ልምድ ያላቸውን ሀኪሞች ለ24 ሰዓታት የህክምና አገልግሎት ይሰጣል፡፡አስፈላጊ ሲሆንም የተለየ ህክምና ለሚያስፈልጋቸው ታማሚዎች ሌሎች ስፔሻላይዝድ የሆኑ ሀኪሞችን በሀገር ውስጥ ያሉና ከውጪ ሀገር በማስመጣት ተጨማሪ የሙያና የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት ሥርዓትም ተዘርግቷል› ብለዋል ዶ/ር ፋሲል፡፡›

ዋሽንግተን ሜዲካል ሴንተር ተመርቆ ስራውን ሲጀምር ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፤የህክምና ባለሙያዎች፤ዲፕሎማቶች አምባሳደሮችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል፡፡ በአሜሪካ የተማሩና ያገለገሉ ሀኪሞች ይህንን ሜዲካል ሴንተር ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለመክፈት የአንድ ዓመት ጊዜ የወሰደባቸው ሲሆን ለማዕከሉ እውን መሆን መንግስት አስፈላጊ የሆኑ ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎችን ወደ ሀገር ቤት ለማስገባት የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ከማድረግ ጀምሮ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ሙሉ ድጋፍ ማድረጋቸው ተዘግቧል፡፡


ደራሲ ታደሰ ሊበን

‹የጉለሌው ሰካራም አሞር ልቦለድ ለመባል የሚጎሉት ብዙ ነገሮች አሉ›

በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አንደተጀመረ የሚነገርለት የአሞር ልቦለድ (short story) በአርግጠኝነት በየትኛው ሀገር እንደተጀመረ ማወቅ ያስቸግራል ። አሜሪካ ፣ጀርመን ፣ራሺያና ፈረንሣይ ሁሉም የየበኩላቸውን የመከራከሪያ ነጥብ በማቅረብ ለጀማሪነት ታሪክ ሺሚያ ይሚገታሉ። ወደ ሀገራችን የአሞር ልቦለድ አጀማመር ስንመጣ ደግሞ 20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ይጥለናል፤የሀገራችን የመጀመሪያው አሞር ልቦለድ ጸሀፊ ማነው? ብለን ስንጠይቅ የሁለት ደራሲዎች ስም ሲጠራ እንሰማለን፤የመጀመሪያውበ1941 ዓ.ም የታተመው ‹የጉሌው ሰካራም›ጸሐፊ የሆነው ተመስገን ገብሬ ሲሆን ከሱ በመቀጠል ደግሞ ታደሰ ሊበን በ1949ዓ.ም ‹መስከረም› ጽፏል።

በዘርፉጥናት ያደረጉ የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ተመራማሪዎች ታደሰ ሊበን የመጀመሪያው የአሞር ልቦለድ ደራሲ እንደሆነ ሲናገሩ ፤በአንዓሩ በሌላ ወገን ደግሞ ‹የስም የመጀመሪያው የአሞር ልብ ወለድ ኢትዮጲያዊ ጸሐፊ ተመስገን ገብሬ ነው›ሲሉ ይከራከራሉ። የአሞር ልብ ወለድ ነጠላ ታሪክ በመፃፍ ተመስገን ገብሬ የሚቀድም ሲሆን የአሞር ልብ ወለድ መጽሐፍ በማሳተም ግን ታደሰ ሊበን የመጀመሪያው ነው።

ትዕግስት ታደስ



ደራሲ ታደሰ ሊበን በ1949 ዓ.ም ‹መስከረም› ፣1952 ደግሞ ‹ሌላው መንገድ› ለአንባቢዎች አበርክቷል፡ ፡ በድርሰቱ ከማህበረሰቡ ቀድሞ በማሰብና ማህበረሰቡ አውጥቶ ለማውራት የማይደፍረውን በመፃፍ የሚደነቅ ደራሲ ቢሆንም በስነ ጹሁፉ አለም ብዙም ሊቆይ አልቻለም። መጻህፎቹ ከታተሙም ብዙ አመታት ስላስቆጠሩ በገበያ ላይም ስለማይገኙ አብዛኛው የአሁኑ ትውልድ ወጣቱ የሚያውቃቸው የሁለተኛ ደገጃ ት/ቤት የአማረኛ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ለአጭር ልቦለድ አፃፃፍ መማሪያነት በታተመው ‹ጅብ ነች› ድርሰታቸው ነው። ታደሰ ሊበን ከድርሰት ስራቸው በተጨማሪ በኢትዮጲያ ንግድ ባንክ የተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎችና እና በኢትዮጲያ ንግድ ምክርቤት (chamber of commerce) ፕሬዚደንት በመሆን ለበርካታ ዓመታት ሰርተዋል።



በቅርቡ «መስከረም» እና «ሌላው መንገድ» በድጋሚ ለህትመት ሊበቃ እንደሆነ ስሰማ የነዚህ ድንቅ መጽሐፎች ደራሲ የሆነው ታደሰ ሊበን ወዴት አሉ? ብዬ መጠየቄ አልቀረም ፤ እሳቸውን ለማግኘትም መዳረሻዬም ከአዲስ አበባ በ37 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው የቀድሞዋ ደብረ ዘይት የአሁኗ ቢሾፍቱ ከተማ ሆኗል።

የያኔው ወጣቱ ደራሲ ታደሰ ሊበን ዛሬ የ84 ዓመት አዛውንት ሆነዋል። ደራሲ ታደሰ ሊበንን ባገኘናቸው ጊዜ ከዚህ በፊት እንደሰማሁት እና እንዳየኋቸው አንጋፎቹ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ውለታቸውና ስራቸው ተዘንግቶ ፣ተሳሳቁለውና ተንድተው አልነበረም ፤ይልቁንስ ከገነት በማይተናነሰው የመናፈሻ ቅጥር ግቢ ውስጥ ባሳደጉት የወንድማቸው ልጅ እና የእህታቸው ልጅ በሚያደርጉላቸው ድጋፍና እንክብካቤ በሙሉ ጤንነትና ንቃት ነው። የመጣሁበትን ጉዳይና ከመጽሐፎችን ጋር በቃለ መጠይቅ ቆይታ እንዲያደርጉ ስጠይቃቸው በደስታና በፍቅር ነበር የተቀበሉኝ፤ ከደራሲው ጋር የነበረኝ ቆይታም ይህን ይመስላል።

ቁም ነገር ፡- እስቲ መጀመሪያ ትውልድዎና እድገትዎ ምን እንደሚመስል ስጫውቱኝ?

ታደሰ ፡- የተወለድኩት በ1923 ዓ.ም ደንቢ ዶሎ ውስጥ ነው። ከዛ እስከ ስድስት አመቴ ድረስ እዛው ካደኩኝ በኋላ አባቴ ሲሞቱ እናቴ ወደ አዲስ አበባ ይዘውኝ መጡ፤ እድሜዬም ለትምህርት ሲደርስ አድቬንቲስት ሚሲዮን አስገቡኝ፤እናቴም እንዲሁም አኳቴ በደንብ እየደገፉኝ ምንም ሳይጎልብኝ በደንብ ነው የተማርኩት። በልጅነቴ ትምህርት በጣም እወድ ነበር፤ነበዝ ተማሪ ነኝ። በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ደግሞ አሁን መምህራን ኮሌጅ የሆነው ኮተቤ በኛ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነበረ፤እዛ ተማርኩ፤ አስራ ሁለተኛ ክፍል እንደጨረስኩ መርካቶ አካባቢ ያለ ኤመር ሰመትር የተባለ ት/ቤት የእንግሊዝኛ እና አማርኛ መምህር ሆንኩኝ።

ቁም ነገር ፡- ንግድ ባንክስ የገቡት እንዴት ነው ?

ታደሰ ፡- ንግድ ባንክ የገባሁት ከዛ በኋላ ነው። እዛ እየሰራሁ እድገት እያገኘሁ ሄድኩ፤በንግድ ባንክ ውስጥ ከአካውንታትነት ጀምሮ እስከ የሰሜን ባንኮች ዞን ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ሰርቻለሁ። ባንኩ እኔን ውጭ ልኮ ለማስተማር በጣም ይጥር ነበር፤ በኋላ ተሳካና ለባንክ ትምህርት ወደ ጣሊያን ሀገር ሮም ሄድኩ፤አሜሪካም እንዲሁም ሌሎች ሀገሮች ባንኩ እየላከኝ ለአጫጭር ትምህርቶች ሄጀለሁ። ከዛ ከተመለስኩ በኋላ ነው የሰሜን ባንኮች ሪጅናል ማናጀር ሆኜ እሰራ የነበረው አስመራ ነበር፤ እዛ እያለሁ ለንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንትነት ተወዳድሬ ስላሸነፍኩ ወደ አዲስ አበባ የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት በመሆን መጣሁ፤ ከዛ በኋላ ጡረታ እስከ ወጣሁበትም ጊዜም፤ ጡረታም ከወጣሁ በኋላም የተለያዩ ድርጅቶች ሰርቻለሁ።

ቁም ነገር ፡- በልጅነትም መሆን የሚፈልጉት ምን ነበር?

ታደሰ ፡- እኔ በልጅነቴ መሆን የምፈልገው ፓይለት መሆን ነበር። ይሄንንም አሳክቼው አየር መንገድ ፈተና ወስጄ ሁሉም ነገር ካለቀ በኋላ እናቴ ሰዎች በአውሮፕላን ሲሄዱ የሚሞቱ



መስሏቸው፤ ጡታቸውን ይዘው ‹ባጠባሁህ ጡቴ ይገፍሀለሁ፤ ይህንን ነገር ተው› ሲሉኝ በዛ የተነሳ ተውኩትና ወደሌላ አቅጣጫ ገባሁ።

ቁም ነገር ፦ ወደስነ ጹሑፉስ እንዴት ገቡ?

ታደሰ ፦ ትምህርት ቤት እያለሁ ጀምሮ እፅፍ ነበር፤ ድራማዎችን እሞክራለሁ ፤እንዲሁም በጣም በውጭ ሀገር ደራሲዎች የተጻፉ አጫጫር ድርሰቶችን አነብ ነበር። በዋነኝነት ግን እኔ የስነ ጽሁፍ ሰው እንድሆን የእናቴ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ምክንያቱም እናቴ በጣም ተረት አዋቂ ናቸው። ከልጅነቴ ጀምሮ ተረቶችን እየነገሩኝ ነው ያደኩት፤ የዚህ የፃፍኳቸው ጹሑፎች ሁሉ ከበስተጀርባው የእናቴ እጅ አለበት

ቁም ነገር ፦ እርስዎ ጊዜ ከነበሩ ደራሲዎች የእርስዎ ወዳጆች እነማናቸው? እነማንንስ ያደንቃሉ?

ታደሰ ፦ ወዳጆቼ የነበሩት እነ አስፋው ዳምጤ ፣ እንዲሁም ሌሎች አሉ። የማደንቀው ከበደ ሚካኤልነው፤ እኔ ብዙም የሀገር ውስጥ ጸሐፊዎች አይስቡኝም፤ ምናልባትም የውጭ ሀገራትን መፃሐፍትን በማንበቤ የተነሳ ይሆናል።

ቁም ነገር ፦ የመጀመሪያው የአጭር ልብ ወለድ ኢትዮጲያዊ ጸሐፊ ማነው? በሚሰው ሳይ ሁለት አይነት አስተያየቶች ሲሰጡ እንሰማለን፤ አንዳንዶቹ ‹የጉስሌው ሰካራም ›ጸሐፊ የሆነው ተመስገን ገብረ ነው ሲሉ፤ሌሎች ደግሞ ታደሰ ሲበን ነው የሚሉ አሉ፤ እርሶ በዚህ ሳይ ምን አስተያየት አሎት?

ታደሰ ፦ ተመስገን ገብረ ‹የጉለሌው ሰካራምን› ከኔ በፊት ቢጽፍም አጭር ልብ ወለድ ለመባል ብዙ የሚጎሉት ነገሮች አሉ፡ ፡ አንድ አጭር ልብ ወለድ ሊያሞላ የሚገባውን ባህሪያትን አያሟላም። አሁን ልዩነቱ ምን እንደሆነ ለመናገር አልተዘጋጀሁም እንጂ ጉድለቱ ምን እንደሆነ መናገር እችላለሁ። ከዚህም በፊት ተጠይቄ በደንብ አውርቻለሁ። ነገር ግን ይህን በማለቴ አንዳንድ ሰዎች እንደ ታሪክ ሺሚያ ያዩት አሉ። እኔን በደንብ የሚያውቁኝና ስለስራው የሚያውቁም ስለጉዳዩ ሊደግፉኝና ሊናገሩ አልቻሉም።

ቁም ነገር ፦ እርሶ ሴሎች ሰዎች ከሚናገርሎት ይልቅ በአጭር ልብ ወለድ ጸሐፍ እኔ ነኝ የመጀመሪያው በማለት ስምን ደፍረው አልወጡም?

ታደሰ ፦ ከዚህ በላይ ምን ልበል?

ቁም ነገር ፦ ‹ጅብ ነች› የተባለው ድርሰትም በዛን ወቅት በጣም የቀደመ አስተሳሰብን ያንጸባርቅ ነበር፤በዛን ወቅት እንዴት እንደዚህ አይነት ሐሳብ መጣሎት? ምናልባት እንደዚያ አይነት ጹሑፍ እንዲፅፉ ያነበቧቸው የውጭ መጽሐፍት ተጽዕኖ ውጤት ይሆን?

ታደሰ ፦ /...ሳቅ/ አንዱም እሱ ሊሆን ይችላል። ብዙ የውጭ ሀገራት ደራሲዎች አጫጭር ድርሰቶችን ማንበቤ ‹ጅብ ነሽን› ለመፃፍ ቀሎኛል። ‹ጅብ ነች› ታሪኩ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ነው። እኔ ራሴ ለረፍት ወደ እናቴ ሸኖ ሄጄ ያቺን ገጸ ባህሪ እመለከታታለሁ፤ እናቴንም ስጠይቃቸው «ተው አይሆንም፤ ቡዳ ነች ይሉኛል ፡፡» በጊዜው እንደዚህ ናቸው ብለው የሚያስቡዋቸውን ሰዎች ቡዳ ነበር የሚሏቸው። እነሱን ለሌት ሌት ወደ ጅብ ይለወጣሉ የሚል ነገር ስለነበረ ያንን መነሻ አድርጌ ወደ ‹ጅብ ነች› በመለወጥ ጻፍኩት።

ቁም ነገር ፦ ስታሪኩ መነሻ የሆነችው ገፀ ባህሪ በትክክል በድርሰቱ እንደተፃፈው በአሳት የተቃጠለች ነበረች?

ታደሰ ፦ አይ አይደለም ፤ እሷ ሳትሆን እኔ ከዛ በፊት በአደጋ በእንደዛ የሆነች ዘመድ እኛ ቤት ትኖር ነበር፤ ያንን አቀናብሬ ነው የጻፍኩት።

ቁም ነገር፦ የመጀመሪያ መጽሐፍዎ መስከረም በዛን ጊዜ አምስት ሺህ ኮፒ ነው የታተመው፤ ይህን ያህል ኮፒ ማሳተምህ የመጀመሪያ ስራህ እንደመሆኑና ብዙም ያልተስመደውን አጭር ልብ ወለድ እንደመፃፍዎ ተቀባይነት አጣለው የሚል ሥጋት አልፈጠረብዎትም ?

ታደሰ ፦ በፍጹም ! እንደዚህ አይነት ፍራቻ ጨርሶ አልነበረኝም። ለየት ያለና አዲስ የሆነ ሥራ ይገፍ በመቅረቤ ተቀባይነት አጣለሁ የሚለው ስጋት አልነበረብኝም።

ቁም ነገር፦ ስስ አንተ ሥራዎች ሲነገሩ፤ታደሰ ሲበን በልብ ወለድ አፃፃፍ ዘይቤው በጣም ለየት ያስ ነው። በተለይ አጨራረሱ ያልተስመደና አስደማሚ አጨራረሶችን ይሰጣል ደባሳል? አንተ ደሄ እንዴት ታየዋለህ?

ታደሰ ፦ ይሄ የአጭር ልቦለድ ትክክለኛ

ወደ ገጽ 34 ዞሯል

> **"ባለቤቴን በጣም እጠዳታለሁ፤ጥሏ ሰው ነበረች ለኔ፤ እኔ እሷ እምነት ታጎላለች ብዬ አልጠረጥራትም ፤እሷ ግን እኔን አታምነኝም። ያኔም እስከመጨረሻው ድረስ አብረን እንሁን ብዬ ጠይቄያታለሁ**

ከሰሞኑ

ስለ እናት ልጅ ፊልም በአሜሪካ ሊታይ ነው



በደራሲና ዳይሬክተር ሙሉቀን ተሾመ ተሰርቶ በቅርቡ በሁሉም ሲኒማ ቤቶች የተመረቀው ‹ስለ እናት ልጅ› ፊልም በቅርቡ ወደ አሜሪካ ተጉዞ ሊታይ እንደሆነ ዳይሬክተሩ ሙሉቀን ተሾመ ለቁም ነገር መፅሄት ገልፃል።

አዲስ አራረብና ልብ አንጠልጣ ታሪክ ያለው ስለ እናት ልጅ ፊልም በተመረቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሁሉም ሲኒማ ቤቶች መድረክ ያገኘ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ፊልሙ ወደ አሜሪካ ከመጓዙ በፊት ከሳምንት እስከ ሳምንት በከተማችን ሲኒማ ቤት እየታየ እንደሆነ ሙሉቀን ተናግሯል።

ወጣትና አንጋፋ አርቲስቶች የሚሳተፉበት ስለ እናት ልጅ ፊልም ላይ ዳይሬክተሩን ሙሉቀንን ጭምሮ ሰለሞን ቦጋለ፤ሳምሶን ታደሰ /ቤቢ/፤አለማየሁ ታደሰ፤ቃልኪዳን ጥበቡና ሌሎችም አርቲስቶች ይሳተፉበታል።

በአቀረፃና በቀለም ውህደቱ የብዙዎችን ፊልም ተመልካቾች ቀልብ የያዘው ስለ እናት ፊልም በየካቲት ወር አጋማሽ በአሜሪካ መታየት እንደሚጀምር ታውቋል።

ዶ/ር ዘውዱ ተረፈ ወርቅ

‹የዲኤንኤ ምርመራ ለሁሉም ህመሞች ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ ምርመራ ነው›



ዶ/ር ዘውዱ ተረፈ ወርቅ በአዲስ አበባ አራት ኪሎ ሲጋባ ቢሮ የሚባለው አካባቢ ባህታ ሰፈር ነው የተወለዱት፡የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ኢትዮጵያ አንድነት ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በቀድሞው በዳግማዊ ምንሊክ የአሁኑ መስከረም ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው ያጠናቀቁት፡፡ዘጠነኛና አስረኛ ዳግማዊ ምንሊክ ተምረዋል፡፡ አስራ አንደኛና አስራ ሁለተኛን አስማያ የተማሩ ሲሆን በባዮሎጂ መምህርነት በዲፕሎማ ተመርቀው በሐረር በመድሃኒያለም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተምረዋል፡፡ ለረጅም ዓመታት በሆላንድና በተለያዩ ሀገራት በስራ ላይ የቆዩት ዶ/ር ዘውዱ በቅርቡ ደግሞ ወደ ሀገራቸው ጠቅልለው ገብተው ‹ሼም አር ሲ -ኢትዮ ላቦራቶሪ ሞሎኪዩላር ዲያግኖስቲክስ› የተባለውን ከፍተኛ የህክምና ተቋም ከፍተው በመስራት ላይ ናቸው፡፡ ከዶ/ር ዘውዱ ጋር ያደረግነው ቆይታ ይህንን ይመስላል፡፡

ቀም ነገር፡- ስመጀመሪያ ጊዜ ከኢትዮጵያ የሄዱት ወደ የት ሀገር ነበር?

ዶ/ር ዘውዱ፡- መጀመሪያ የሄድኩት ወደ ራሺያ ሲሆን ከዚያም አንድ ሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ ፊንላንድ ነው ሄጄ ከፍተኛ ትምህርት የተማርኩት፡፡

ቀም ነገር፡-ምን ተማረ?

ዶ/ር ዘውዱ፡- የመጀመሪያ የማስተርስ ድግሪዬን የተማርኩት አፕላይድ ኬሚስትሪና ማይክሮ ባዮሎጂ ነው፡፡ ውጤቴም በጣም ጥሩ የሚባል ስለነበር በኢንተርናሽናል ጆርናል ላይ ታትሞ ስለነበር ለምን በዛው የዶክትሬት ድግሪህንም አትሰራም ተብዬ ዕድሉ ሲሰጠኝ እዛው የተማርኩበት ኮሌጅ ውስጥ እያስተማርኩኝ የዶክትሬት ትምህርቴን ጀመርኩ፡፡ ከአራት ዓመታት በኋላም ትምህርቴን ጨርሼ ከተመረቅሁ በኋላ በዛው ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እያስተማርኩና በተመራማሪነት ለሰባት ዓመታት ያህል ከሰራሁ በኋላ ወደ ሆላንድ ሄድኩ፡፡

ቀም ነገር፡-ስምን?

ዶ/ር ዘውዱ፡- ሆላንድ በአመስተርዳም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ባለ የጥርስ ህክምና ፋካሊቲ ውስጥ የማይክሮ ባዮሎጂ ተመራማሪ ያስፈልጋቸው ስለነበር ነው የሄድኩት፡፡ይህ ምርምር የሚያተኩረው በጥርስ ውስጥ ያሉ ባክቴሪያዎች ያላቸውን ምንነት እና ምን እንደሚያደርጉ ማጥናት ላይ ስለነበር ይህንን የሚያሳይ የሞሎኪዩላር ቴክኒክን ለማበልፀግ ነበር እዚያ የሄድኩት፡፡ይህ ምርምር ውጤታማ ስለነበር ትላልቅ የጥርስ ሳሙና አምራች ኩባንያዎች ወስደውኝ እስከ አሜሪካ ድረስ ሄጀ ምርምሩን በተመከለከተ ስልጠና ሰጥቼ ነው የተመለስኩት፡፡ ከአሜሪካ መልስ ከአመስተርዳም ዩኒቨርሲቲ ከለቀቅሁ በኋላ በዘር የሚተላለፉ በሽታዎችን /የጂኔቲክስ ቴስቲንግ/ የሚመረምር ኬሚካሎችን የሚያበለፅግ አንድ ተቋም አለ እዛ ገባሁ፡፡ ተቋሙ እነዚህን በዘር የሚተላለፉ የዘር በሽታዎችን የሚለየውን ኬሚካል አበልጽጎ ለተለያዩ ተመራማሪዎችና ለህክምና ተቋማት ያቀርብ ስለነበር በዚህ ድርጅት ውስጥ በከፍተኛ ተመራማሪነት ነው የተቀጠርኩት፡፡ በዚህ ድርጅት ውስጥ አንድ ሶስት ዓመት ያህል እንደሰራሁ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ኢትዮጵያ እመላለስ ስለነበር ከዚህ በኋላ ለምንድነው የያዝኩትን እውቀት ይዤ ወደ ሀገሬ ጉበቼ አንዳንድ ስራዎችን የማልሰራው ብዬ ወስንኩ ማለት ነው፡፡

ቀም ነገር፡- ወደ ሀገር ቤት ሲመጡ የህክምና ስራ ደሰሩ ነበር?

ዶ/ር ዘውዱ፡- ወደ ሀገር ቤት ስመጣ የተለያዩ ስልጠናዎችንና ትምህርቶችን ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እሰጥ ነበር፡፡ በተለይም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባዮሎጂ ዲፓርትመንት፤ የህክምና ፋካሊቲና እንዲሁም የህፃናት ህክምና ዲፓርትመን ጋር ውስጥ ካሉ መምህራን ጋር እንተዋወቅ ስለነበር በመጣሁ ቁጥር ያለኝን አዳዲስ እውቀቶች እያስተማርኩ ነበር የምመለሰው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የጂኔቲክስ ቴስቲንግ ፋሲሊቲ እንደሌለ ተመልክቼ ስለነበር ሆላንድ ውስጥ እኔ እሰራበት ከነበረው ተቋም ይህንን ፋሲሊቲ መጠቀም እንደሚቻል ተነጋግሬ ነበር፡፡የተወሰኑትን የምርምር ኬሚካሎች እዚህ ላሉ ወዳጆቼም አምጥቼ ሰጥቻቸው ስለነበር ውጤት አግኝተውበታል፡፡ እርግጥ ነው አዲስ ቴክኖሎጂ በመሆኑ ወደ ሶስተኛው ዓለም ሀገራት ሲገባ የተወሰኑ መሰፈርቶች ሊበጅለት ይገባል፤አዲስ ቴክኖሎጂ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ እውቀቶችን ለህብረተሰቡ ማምጣት አለበት፡፡በዘር የሚተላለፉ በሽታዎችን በዚህ ኬሚካል አማካይነት የመለየቱ አዲስ ቴክኖሎጂ ሲመጣ የህብረተሰቡንም አቅም ባገናዘበ መልኩ መሆን ስላለበት የምሰራበት ተቋምም እናግዝሃለን ብለውኝ ስለነበር ነው ጠቅልዬ ወደ ሀገር ቤት የመጣሁትና በሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን የጂኔቲክ ቴስቲንግ ማዕከል የከፈትኩት፡፡

ቀም ነገር፡- ይህ አዲስ ቴክኖሎጂ የሚያተኩረው ምን ላይ ነው?

ዶ/ር ዘውዱ፡- ከቴክኖሎጂው ስንነሳ በቀላሉ በዲኤንኤ ላይ የተመሰረተ የህክምና አገልግሎት ነው ::ዲኤን ኤ ማለት ማንም በህይወት ያለ ፍጡር ከትንሷ ባክቴሪያ ጀምሮ እስከ ትልቁ ሰው ልጅ ወይም ግዙፉ አሳ ነባሪ ድረስ ሰውነታቸው የሚሰራውን ስራ የሚይዝ በኮድ መልክ የተቀመጠበት ሞሎኪዩል ነው፡፡ይሄ ዲኤን ኤ የአንድን ፍጡር ማንነት ብቻ ሳይሆን ምንነቱንም ጭምር ይገልፃል፡፡እኛም የሰው ልጅ ምንነታችንን የሚገልፅ ሞሎኪል በሴላችን ውስጥ ይዘን ነው



የምንኖረው::ይህ ዲኤንኤ የሚባለው ሞሎኪዩል ከትውልድ ወደ ትውልድ የእየተላለፈ የሚመጣ በዘር የሚተላለፍ ነው::የኛ የዲኤንኤ አሻራ ከዛሬ ሚሊዮን ዓመት በፊት ከነበረችው ከሉሲ አሻራ ጋር የሚመሳሰልበት ነገር እንዳለው የሚረጋገጥበት ነው:: በሰለጠኑት ሀገራት የህክምና ቴክኖሎጂው እያደገ ከመምጣቱ ጋር በተያያዘ ማንኛውንም ህክምና ከዲኤንኤ ምርመራ ጋር በማቆራኘት በቀላሉ ህክምና መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: በዲኤን ኤ ምርመራ አንድ ሰው ምኑ ሲቀንስ ምን እንደሚሆን፤ ምን ሲበዛ ምን እንደሚታመም የሚታወቅበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: ይህ በመሆኑ የተነሳ ለእያንዳንድ ሰው የግለሰብ ህክምና ደረጃ እየወረደ ነው::

ቁም ነገር:- ምን ማለት ነው የግለሰብ ህክምና ማለት?

ዶ/ር ዘውዱ:- የግለሰብ ህክምና ማለት የአንድ ሰው ምንነት በዲኤንኤው አማካይነት በትክክል በመታወቁ ለእርሱ ብቻ ተብሎ የሚሰጥ መፍትሔ ማግኘት ደረጃ ላይ ተደርሷል::ይህንን ህክምና መስጠት የሚቻለው የግለሰቡን ሁኔታ የሚገልፀውን ምርመራ በዲኤንኤ በማድረግ ነው: :በመሆኑም በዘር ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ በሽታዎችን በዲኤንኤ ምርመራ ማረጋገጥ ስለሚቻል ነው ይህንን ቴክኖሎጂ ወደ ሀገር ቤት በማስገባት ህብረተሰቡ ምርመራ በማድረግ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግ እና ለችግሩ የበለጠ እንዳይጋለጡ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማገዝ ጥረት እያደረግን ያለነው::

ቁም ነገር:- በመድሃኒት አወሳሰድ ላይስ የዲኤንኤ ምርመራውን ቀድሞ ማድረግ ምን ያህል ጠቀሜታ አለው?

ዶ/ር ዘውዱ:- በጣም ይጠቅማል:: አንዳንድ ሰዎች ትንሽ መድሃኒት ወስደው የሚድኑ ሰዎች አሉ፤ ለነዚህ ሰዎች ብዛት ያለው መድሃኒት መስጠት አያስፈልግም:: መሉ ለሙሉ ደግሞ መድሃኒት መውሰድ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ መጠን ያለው መድሃኒት መውሰድ ያለባቸው ሰዎች ይኖራሉ::ይሄንን ለማወቅ የዲኤንኤው ምርመራ ግልፅ መረጃ ይሰጣል:: እነዚህንና የመሳሰሉትን የህክምና ታሪኮች ለማወቅ ይጠቅማል::

ቁም ነገር:- ከዘር ጋር የተቆራኙ እንደ ስኳር ያሉ ህመምተኞች ላይ ያለው ጠቀሜታስ?

ዶ/ር ዘውዱ:- እንደ ስኳር ብቻ ሳይሆን የአንጀት ካንሰር እና የጡት ካንሰርን ጨምሮ ለማከም ከዘር ጋር ያለውን ቁርኝት እስካላወቅን ድረስ የምንሰጠው ህክምና የተሟላ አይሆንም ተብሎ ነው የሚታመነው::ለምሳሌ የስኳር ህምም በዘሩ ውስጥ እንዳለ የሚያውቅ ሰው በስኳር በሽታ እንዳይጠቃ ወይም የሚጠቃም እንኳ ቢሆን ቀሪ ህይወቱን እንዴት በሰላማዊ መንገድ መምራት እንዳለበት በቀላሉ ማወቅ ይችላል::የአንጀት ካንሰር በቤተሰቡ ውስጥ ያለበት ሰውም የአመጋገብ ሁኔታውን በማስተካከል ብቻ ከበሽታው ራሱን መጠበቅ ይችላል::ካንሰር ማለት በአንድ ጊዜ መመረት ካለበት መጠን በላይ ብዙ ሴሎች መመረት ወይም የማይገባቸው ሴሎች ተመርተው መገኘት ማለት ነው:: ሁሉም ካንሰር ግን አጥፊ



ነው ማለት አይደለም:: የካንሰሩን ምንነት ለማወቅ የሚቻለው የሴሎቹን ሞሎኪዩላር ስትራክቸው ወይም ቁጥር በመመርመር ነው:: በዲኤንኤ ምርምራ ነው የሚታወቀው:: ይህንን የካንሰር ስፔሻሊስት ሀኪሞች ናቸው ይህንን በደንብ የሚያውቁት::

ቁም ነገር:- ከእርግዝና ጋር በተያያዘስ ቴክኖሎጂው ምን ያህ ጠቀሜታ አለው?

ዶ/ር ዘውዱ:- ለምሳሌ አንድ እናት አርግዛ ገና በሽል ደረጃ ፅንሱ እያለ የእናቲቱን የሽንት ውሃ በመውሰድ ብቻ ከህፃኑ ገላ ላይ እየተቀረፉ የሚወድቁ ቆዳዎች ላይ ያለውን ዲኤንኤ በመመርመር ወደ ፊት ልጁ የሚያጋጥመውን የጤና ችግር ከወዲሁ ማወቅ ይቻላል: :ሴቶች እድሜ ከገፉ በኋላ ከሚፈፀም እርግዝና ጋር በተያያዘ በልጆች ላይ የሚከሰትን የአዕምሮ ዝግመትና ኦተስቲክ አይነት እግሮችን አስቀድሞ ማወቅ ይቻላል: : አስቀድሞ ከታወቀ ደግሞ በእናቲቱ ጤና ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ የሚወለደው ልጅም የሚይቆይ ከሆነና ሌሎች ችግሮች የሚመጡ ከሆነ አስቀድሞ እርምጃ ለመውሰድ ይህ የጂኒቲክስ የናሙና ምርምራ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው::በመሆኑም ቴክኖሎጂው በእናቶችና በጨቅላ ህፃናት ሞት ላይ ያለውን ሁኔታ ከወዲሁ መታደግ የሚቻልበትን አማራጭ የሚያስገኝ ቴክኖሎጂ ነው::

ቁም ነገር:- ብዙ ጊዜ በሀገራችን የተሰመደው ሰዎች የዲኤን ኤ ምርመራ የሚያደርጉት ታመው ሀኪም ቤት ከሄዱ በኋላ በሀኪም ትዕዛዝ ነው፤ ግን ከዛ በፊት ማንኛውም ሰው ጤነኛ ሆኖ ነገር ግን የቤተሰቡንና በዘር የወረሰው ነገር እንዳስ ለማወቅ ይችላል?

ዶ/ር ዘውዱ:- ይችላል፤ለምሳሌ በቤተሰብ ውስጥ አባት ወይም አያት፤ወደታች አክስተና አጎት በተመሳሳይ መልኩ በአንድ አይነት በሽታ የተያዙ እንደነበር የሚያው ሰው በዘሩ ምክንያት እሱም በዚያ በሽታ የመያዝ ዕድል ሊኖረው ስለሚችል መጥቶ በምርምራ ማረጋገጥ ይችላል::ይህንን ምርምራና ምክር እኛ ጋር መጥተው ሲወስዱ የግድ የህኪም ትዕዛዝ አያስፈልግም:: በእርግጥ ህኪም አዞ የሚመጡ ሰዎች አሉ:: ነገር ግን የወደፊት አኗኗርን ከወዲሁ ለማስተካከልም ምርመራውን አድረጎ ራስን ማወቅ ይቻላል::ምርምራውን አድርገው ችግሩ እንዳለባቸው

ወደ ገፅ 28 ዞሯል



ቫቲካን በገና ዋዜማ

በታምራት ኃይሉ

ባለፈው ዕትም ከቬይና ወደ ሮም ጣሊያን በባቡር ተጉዘን የጥንታዊቷን ሮም ከተማ አንዳንድ ታሪካዊና የቱሪስት መስህቦች መቃኘታችን ይታወሳል፡፡ ሮምን ልዩ ከሚያደርጓት ነገሮች መሀከል አንዱ የዓለማችን ብቸኛ የሁለት ሀገሮች ዋና ከተማ መሆኗ ብቻ ሳይሆን በሆዷ ራሷን የቻለች ሉዓላዊት ሀገር አቅፋ መያዟ እንደሆነ ጠቅሰናል፡፡ ይህም ቫቲካንን ሲቲ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት /ዩኔስኮ/ በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡ ከተሞች መሀከል አንዱ አድርጓታል፡፡

የቫቲካን ሲቲ ታሪካዊ ዳራ

ቫቲካን የሚለው ቃል Vaticani ከሚለው የላቲን ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም ኮረብታ ማለት ነው፡፡ ቫቲካን ሲቲ በሮም የደቡብ ምስራቅ አቅጣጫን ተከትሎ የሚፈሰው የቲበር ወንዝ ግርጌ የምትገኝ ሀገር ናት፡፡ከክርስቶስ ልደት በፊት የሮሙ ገዢ ንጉስ ካሊጉላ በዚህ ስፍራ የግሉን የሰርከስ መመልከቻና መዝናኛ ማዕከል አስገንብቶ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ከክርስትና ሀይማኖት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ደግሞ በአካባቢው የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መታነፅ ከጀመሩ በኋላ ቦታው መንፈሳዊ ትሩፋቶችን መያዝ ጀምሯል፡፡ የሮማዋ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እንደ መጀመሪያው ጳጳስ ተደርጎ የሚወሰደውና ከክርስቶስ ማረግ በኋላ

> ሮም ከተማን ከቫቲካን የምትለየው በጥናት በዙፊያዋ ባለው ኪነ ህንፃ ግንብ ሲሆን ከህንፃዎቹ ውጪ ያለው የሁለቱ ሀገሮች መለያ በመሬት ላይ የተሰመረ ነጭ መስመር ነው::

ክርስትናን ለመስበክ ወደ ሮም ተጉዞ ያስተማረውና በኋላም በሮም ወታደሮች ተዘቅዝቆ የተገደለው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የተቀበረው በዚሁ አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ቫቲካን ሲቲ እንደ ክርስትና ሀይማኖት ማዕከል ስትታይ ቆይታለች፡፡ እ.ኤ.አ ከ337 ጀምሮም የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ዋና መቀመጫም ሆና አገልግላለች፡፡

በኋላም ከ16ኛውና ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስን ጨምሮ ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት መታነፃቸው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በከተማዋ ላይ የተለየ አመለካከት እንዳላት አሳይቷል፡ ፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግም የተለያዩ የራስ ገዝና የአስተዳደር ጥያቄዎች ሲነሱ ቆይተዋል፤ ቫቲካን ሙሉ ለሙሉ ሉዓዋላዊ ነፃነቷን ከጣሊያን ያገኘችውና እንደ ሀገር የተመሰረተችው እ.ኤ.አ ጁን 29 ቀን 1929 ነው፡፡ ቫቲካንን እንደ ሉዓላዊ ሀገር አድርጎ ለመቀበል ልዩ ልዩ ድርድሮች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን ህጋዊ ማዕቀፍ ተበጅቶለት የፀደቀው ስምምነት የላተራን ስምምነት / Lateran Pacts /ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህንን ስምምነት የተፈራረሙት የወቅቱ የጣሊያን መንግስትና የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሲሆኑ በስምምነቱ መሠረት የፖለቲካ፣ የአስተዳደርና የቱሪዝም ጉዳዮች ተካተውበታል፡፡

ቫቲካን እና አስተዳደር

ቫቲካን የዓለማችን ትንሿ ሀገር ናት፡ ፡ የቆዳ ስፋቷም 110 ሄክታር ሲሆን የህዝብ ቁጥሯም አንድ ሺህ አይሞላም ፡፡ እ.ኤ.አ በ2011 የተደረገው ትንበያ እንደሚያሳየው ከሆነ የቫቲካን ከተማ ነዋሪ 842 ብቻ ነው፡፡ ከዚህ




ውስጥ የቫቲካን ዜግነት ያላቸው 450 ያህሉ ብቻ ሲሆኑ ቀሪዎቹ በቫቲካን ሲቲ የመኖር ፍቃድ ያላቸው የሌሎች ሀገራት ዜጎች/አብዛኛዎቹም ጣሊያናውያን/ ናቸው። ያም ሆኖ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በቀኖናዋ መሠረት ለተለያዩ ቀሳውስትና ጳጳሳት የቫቲካንነት ዜግነት ሰጥታ በመላው ዓለም በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ስለምትመድብ የዜጎቿ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው። ይህቺ የእጅ መዳፍ የምታክል ትንሽ ሀገር እንዴት አድርጋ እንደመንግስት ልትቆም ቻለች? መደበኛ የመንግስት ስራዋንስ እንደምን አድርጋ ትወጣለች? የሚለው ጥያቄ የብዙዎቻችሁ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡ ፡ የኔም ጥያቄ ነው። እኔም ከተማዋን በአካል ተገኝቼ እንከምመለከታት ድረስ ይህ ጥያቄ ሳያስጨንቀኝ አልቀረም። አንድ ቀበሌን ያህል እንኳ ስፋት የሌላት ቫቲካን ዙሪያዋን በሮም ከተማ የተከበበ በመሆኑ ወሳኝ የሚባሉ የመንግስት ህንፃዎቿ የሚገኙት በሮም ነው። በመሆኑም በሮም ከተማ የሚገኙት የቫቲካን መንግስት ቢሮዎች ልክ እንደ አንድ ሀገር ኤምባሲ የሚታዩ በመሆናቸው ሠራተኞቹም የዲፕሎማቲክ ከለላ እንዳላቸው የላተራን ስምምነት ይደነግጋል።

የፀጥታ ስራውን በተመለከተም የከተማዋን ዙሪያ የጣሊያን ፖሊሶች የሚጠብቋት ሲሆን በሮም ወንጀል ፈፅመው ወደ ቫቲካን ገብተው ለመሸሸግ የሚሞክሩ ወንጀለኞችን የጣሊያን ፖሊስ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ገብቶ የመያዝ መብትም አለው። ቫቲካን ዋናውን የቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይና ቤተ መንግስት በተመለከተ የቫቲካን ዜግነት ባላቸው የስዊዝ ወታደሮች የምታስጠብቅ ሲሆን የቱሪስቶችን ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ ቀላል የሚባሉ ወንጀል ፈፃሚዎችና ኪስ አውላቂዎችን ይቆጣጠራሉ። ያም ሆኖ ወንጀለኞቹን ቫቲካን አስራ የምታስቀምጥበትና ፍርድ ቤት ከሳ የምታስቀጣበት ቦታ ስለሌላት ፍርዱም ሆነ የእስር አፈፃፀሙ በሮም ማረሚያ ቤት የሚከናወን ነው። ለዚህም የሮም ግልጋሎት ቫቲካን በየዓመቱ የተወሰነ ክፍያ ለሮም ከተማ ከአስተዳደር ትከፍላለች።የራሷ የሆነ ባንዲራ፤ብሔራዊ መዝሙርና የተሸከርካሪ ታርጋ መለያ፤ፖስታና የስልክ ኮድ ያላት ቫቲካን የመንግሥቱ ፕሬዚዳንት ዋና ፅ/ቤትና መኖሪያም በከተማዋ ይገኛል። ቫቲካን ምንም እንኳ የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገር ባትሆንም የመገበያያ ገንዘቧ ዩሮ ነው።እንግሊዝ የህብረቱ አባል ሀገር ሆና በዩሮ ለመገበያየት ‹አሻፈረኝ› ያለች ብቸኛ ሀገር ስትሆን ቫቲካን ደግሞ አባል ሳትሆን በዩሮ የምትገበያይ ሀገር ናት።

ቫቲካን በገና ዋዜማ

ከሮም ወደ ቫቲካን የገባነው በእግራችን/ ዎክ/ እያደረግን ነው። ወደ ቫቲካን ከተማ ለመግባት የስፖርትም ሆነ ሌላ የጉዞ ሰነድ ማሳየት አይጠበቅም፡ ፡ ወደ ቫቲካን ለመግባት አምስት ያህል አማራጭ በሮች አሉ፤ ከዋናው ቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ መገኛ መጀመር የከተማዋን ኪነ ህንፃና ውበት ለመመልከት ያስችላል። ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ የደረስነው በገና በዓል ከብረ በዓል ዋዜማ ላይ ስለነበር በቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ ላይ በየዓመቱ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አቡነ ፍራንሲዝን ቃለ ምዕዳንና ቡራኬ ለመቀበል ለሚሰበሰበው ህዝበ ክርስቲያን ወንበር እየተደረደረ ነበር።አቡኑ በዚህ ስፍራ ላይ ለሚሰበሰቡና በመላው ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያኖች በየዓመቱ በ162 ሀገራት ቋንቋ /አማርኛን ጨምሮ/ ‹መልካም ገና› የሚል የመልካም ምኞት መግለጫ ከህንፃው ቤተመቅደስ መስኮት ላይ ብቅ ብለው ያስተላልፋሉ፤ ይኸው ስነ ሥርዓት በመላው ዓለም በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት ያገኛል።

በአደባባዩ መሀል ላይ የዓመቱ ትልቅ የገና ዛፍ የሚቆም ሲሆን እኛ በደረስንበት ጊዜ በትላልቅ ክሬኖች አርቴፊሻል የገና ዛፎች ከመኪና ላይ በክሬን እየወረደ ነበር። ቫቲካን ሲቲ ገብቶ የቫቲካን ሙዚየምን ሳይመለከቱ መመለስ አይታሰብም። ከንብኚዎች ከፍተኛ ገቢ ለሀገሪቱ ከሚያስገባው የቱሪስት መስህብ መሀከል አንዱ የሆነው የቫቲካን ሙዚየም ከልዩ ልዩ ሀገራት በተዘረፉ ቅርሶች የተሞላ ሲሆን የሀገራችን ጥንታዊ የብራና መፃህፍትና የወርቅ መስቀሎች እንዲሁም የነገስታት አልባሳትና ደብዳቤዎችን ይዟል። ቫቲካን እንደ ጣሊያን ሁሉ ከልዩ ልዩ ሀገራት የተዘረፉ ቅርሶችን እንድትመልስ የተለያዩ ጥያቄዎች እየቀረበባት ቢሆንም ‹ጆሮ ዳባ ልበስ › ያለች ትመስላለች። እንደ አብነትም ልክ እንደ አክሱም ሀውልት ከክርስቶስ ልደት በፊት ሮምን ያስተዳድር በነበረው ንጉስ ካሊጉላ ከግብፅ ተዘርፎ በከተማዋ እምብርት ላይ የቆመው ሐውልት አሁንም ድረስ የከተማው ውበት ነው። ምንም እንኳ ለግብፃውያን ‹የመልሱልን› ውትወታ ቫቲካን ምላሷ



ዝምታ ቢሆንም ግብፃውያን ግን ጥያቄያቸውን ከማቅረብ አልቦዘኑም።

ሰሞኑንም በማህበራዊ ሚዲያዎችና ድረ ገፆች ላይ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቅርሶችን በማስመለስ ስራ ላይ የተሰማራው ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅት በቫቲካን ተዘርፈው ለዓመታት የሙዚየሞቿ ማድመቂያና መጠቀሚያ ስለሆኑት ቅርሶቻችን የመልሱልን ዘመቻ መጀመሩን የሚያበስር የፊርማ ማሰባሰቢያ ዘመቻ ተጀምሮ ስለነበር እኔም ፊርማዬን ከማኖሬ በተጨማሪ በስፍራው ስለተገኘሁ ያገኘሁትን አጋጣሚ በመጠቀም ስለጉዳዩ ለመጠየቅና ስለቅርሶቻችን ለማስረዳት ሞክሬ ነበር፡ ፡ በተለይም በቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ ላይ ትልቁን የገና ዛፍ ለማቆም ተፍ ተፍ ከሚሉ የቤተክርስቲያኒቱ ቀሳውስትና ዲያቆናት መሀከል አንዱን ላናግረው ሞክሬ ነበር።ከእኔ ጥያቄ ይልቅ ለገና ዛፉ መቆም ቅድሚያ የሰጠ የሚመስለው አንድ ዲያቆን ገና ጥያቄዬን ስጀምር ሳያዳምጠኝ ነበር ሰው ሰራሽ ዛፉን ከመኪና ላይ ለማውረድ ጥሎኝኝ የሄደው - ሳሳዝን!!

በክብ ቅርፅ የተገነባውን የቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ ተመልክተው ቁልቁል ሲሄዱ የቲበርን ወንዝ ድልድይ ያገኛሉ። በነገራችሁ ላይ ሮም ከተማን ከቫቲካን የምትለየው በዋናነት በዙሪያዋ ባለው ኪነ ህንፃ ግንብ ሲሆን ከህንፃዎቹ ውጪ ያለው የሁለቱ ሀገሮች መለያ በመሬት ላይ የተሰመረ ነጭ መስመር ነው። ነጭ መስመሩ በመኪና አስፋልቱ ላይ የተሰመረ ሲሆን ከመስመሩ ወዲህ ሮም፤ ከመስመሩ ወዲያ ቫቲካን ነው። እኛም ይንን መስመር ተሻግረን በቲበር ወንዝ ድልድይ ስናቋርጥ አይናችንን አንድ ነገር ያዘው። ሮም ከተማን በሚያቋርጠው ቲበር ወንዝ ድልድይ ግራና ቀኝ ላይ የመላዕክት ኪነ ህንፃ በብዛት ይታያል። የድልድዩም የመላዕክት ድልድይ ወይም የፍቅረኞች ድልድይ እንደሚባል አውቀናል፡ ፡ ድልድዩ የፍቅረኞች ድልድይ የተባለው ከመላው ዓለም የሚመጡ ፍቅረኞች በምሽት ጥንድ ጥንድ ሆነው የሚዝናኑበትና ፎቶግራፎችን የሚነሱበት በመሆኑ ሲሆን በድልድዩ ብረት ላይ በሚያኖሩት የቃል ኪዳን ማህተም ጭምር ስያሜው እንደተሰጠው ይነገራል። አብዛኛዎቹ ፍቅረኞች በዚህ ስፍራ ‹ላልኩዳሽ - ላልኩዳህ› በሚል ቃል የሚገባቡ ሲሆን ለዚህም ቃል ኪዳናቸው ማረጋገጫ የሚሆን ቁልፍ

ወደ ገጽ 23 ዞሯል

አውሮፓውያን በሽብር ስጋት ውስጥ



ፓሪስ

አውሮፓውያንና ሌሎች በጎርጎሣውያን የዘመን አቆጣጠር የሚጠቀሙ ሀገራት አዲስ ዓመታቸውን ከተቀበሉ ገና የመጀመርያ ወራቸው ላይ ነው የሚገኙት፡፡ በደማቅ አጀብ የተቀበሉት አዲስ ዓመት ገና ከመስከረም መባቻ አዲስ መዓት ይዘባቸው የመጣ ይመስላል፡፡ በውበቷ ከዓለም ቁጥር አንድ በሆነችው ፓሪስ ውስጥ በምጸታዊ ይዘቱ የሚታወቀው ቻርሊ ሄብዶ የተባለ ሣምንታዊ መፅሔት አዘጋጆች ላይ በሽብርተኞች በደረሠ ጥቃት እንዲሁም በኮሸር የገበያ ማዕከል ላይ በተከፈተ ተኩስ የአስራ ሠባት ሰዎች ህይወት አልፏል፡፡

መስከረም 7 ቀን 2015 (እ.ኤ.አ) ከላይ እስከታች ጥቁር በጥቁር የለበሱና ክላሽንኮቭና ሌሎች መሳሪያዎች የታጠቁ ሁለት ሠዎች የቻርሊ ሄብዶ መፅሔት ወደሚዘጋጅበት ቢሮ ሲዘልቁ አገር ሠላም ነው ብለው ቢሯቸው የተቀመጡት 15 የመፅሔቱ አባላት የዓመቱን የመጀመርያ ስብሰባ በማካሔድ ላይ ነበሩ፡፡ መሣሪያ የታጠቁ ሁለት ወንድማማቾች በከፈቱት ተኩስ በቻርሊ ሄብዶ እንግዳ መቀበያ ክፍል የነበረውን ፍሬዴሬክ ቦይሠው የተባለ የጥገና ሠራተኛ ጨምሮ አስራ ሁለት ሠዎች ተገድለዋል፡፡ እነኚህ ሽብርተኞች እስከ 50 ያህል የተኩስ እሩምታ ማድረጋቸው ነው የተነገረው፡፡ በተያያዘ ሁኔታ አልደፍራንስ በተባለ ቦታ በተፈጠረ ጥቃትም አምስት ሠዎች ተገድለዋል፡፡ በቻርሊ ሄብዶ የህትመት ድርጅትና በኮሸር የገቢያ ማዕከል ላይ ተኩስ ከፍተው አደጋውን ካደረሡት ስድስት ታጣቂዎች መካከል ሰይድ ኩዋቺ እና ሸሪፍ ኩዋቺ የተባሉት ወንድማማቾች ዋነኛ ተጠርጣሪ መሆናቸውን የፈረንሳይ ፖሊስ አስታወቆ የነበረ ሲሆን በኮሸር የገበያ ማዕከል ጥቃት የፈፀመው ሠው ደግሞ ኩሊባሊ የሚባል መሆኑ ነው የተነገረው፡ ፡ ታጣቂዎቹ በፖሊስ ተገድለዋል፡፡ ይህን አስከፊ ጥቃት ተከትሎም በሀገሪቱ የሚገኙ የሚዲያ ተቋማት፣ የሀይማኖት ስፍራዎችና የህዝብ ትራንስፖርቶችን ከተመሣሣይ ጥቃት ለመከላከል በወታደሮች ጥበቃ ተደርጎላቸዋል፡፡ የፈረንሣዩ ፕሬዚዳንት ፍራንሷ ኦላንድ በጥቃቱ ማዘናቸውን የገለፁ ሲሆን ጥቃት አድራሾችንም ተከታትለው ለህግ እንደሚያቀርቡ ቃል መግባታቸውን ተከትሎ ነው ፖሊስ የጥቃቱን ፈፃሚዎች ማደን የጀመረው፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን ፈረንሳይ የሽብር ጥቃት ኢላማዎች ሊሆኑ ይችላሉ ባለቻቸው አካባቢዎች 15,000 ወታደሮች አስፍራለች፡፡ ከእነኚህ አካባቢዎች መካከል የአይሁዳውያን አካባቢዎችና ት/ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ዳግም የሽብር ጥቃቱ እንዳይከሠት ለመከላከልም የፈረንሳይ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሃያ አራት ሰዓት በተጠንቀቅ ለመቆም ተገድዷል፡፡ ለዚህ የሽብር ጥቃት የባህር ሰላጤው የአልቃኢዳ ክንፍ ኃላፊነቱን የወሰደ ሲሆን ከገዳዮቹ መካከል ዋነኞቹ ሁለት ወንድማማቾች ጀኔቪለርስ በተባለ አካባቢ የተወለዱ የፈረንሳይ ዜግነት ያላቸው ሙስሊሞች መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ እነኚህ የ32 እና የ34 ዓመት ወንድማማቾች ወደ ፈረንሣይ ከገቡ አልጄሪያውያን ቤተሠቦች የተወለዱ መሆናቸው ተገልፆል፡፡ በቻርሊ ሄብዶ የህትመት ድርጅት ውስጥ በተፈፀመው ጥቃት ከሞቱት አስር ጋዜጠኞች መካከል ሁለቱ በጣም ታዋቂ የካርቶን ስዕል ባለሙያዎች ነበሩ፡ ፡ ይህ የምፅት ይዘት ያለው መፅሔት አሣታሚ ድርጅት እ.ኤ.አ በ2006 ለህትመት ባበቃው የነቡዩ መሐመድ የካርቶን ስዕል የተነሣ በርካታ ሙስሊሞችን አስቆጥቶ የነበረ ሲሆን በህዳር 2011 በድጋሚ «ቻሪያ ሄብዶ» በተሠኘ ርዕስ የመሐመድን የካርቶን ስዕል ይዞ ወጥቶ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የመፅሔቱ ኤዲተር የሆነው ስቴፋኒ ቻርቦኒየር በደረሠበት የግድያ ዛቻ የተነሣ በፖሊስ ጥበቃ ሲደረግለት ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ጥቃት ህይወታቸው ካለፈው የመፅሔቱ ሠራተኞች መካከልም አንደኛው ስቴፋኒ ቻርቦኒየር ነው፡፡

ዓለማቀፍ ምላሾች

የፈረንሣይ ፓሪስ በሽብር ጥቃት በተናጠች ማግስት የአንድ ቀን ሀዘን አውጃ ስትቀመጥ አይዞሽ ባይ አፅናኝ አላጣችም፡፡ ሦስት ነጥብ ሰባት ሚሊየን ፓሪሣውያን እንዲሁም አርባ አራት የሀገራት መሪዎችና ተወካዮች ተቃውሟቸውን በአደባባይ አሠምተዋል፡፡ ታላላቅ የዓለም መሪዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው በአንድ ልብ ጥቃቱን ያወገዙበት ይህ አጋጣሚም ዓለም ህብረት ፈጥሮ በአንድ ድምፅ የተሠለፈበት መድረክ የሚል ከፍተኛ አድናቆት ከተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ተችሮታል፡፡ በሀገሪቱ ታሪክም ታይቶ የማይታወቅ ግዙፍ ሠልፍ ተብሎለታል፡፡ የጣልያኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ማቲው ሬንዚ፣ የጀርመኗ መራኄ መንግሥት አንጌላመርክል፣ የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታኒያሁ፣ የፍልስጤሙ መሪ መሀሙድ አባስ፤ የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን በተቃውሞ ሠልፉ ላይ ከተገኙት መሪዎች መካከል ጥቂቶቹ ሲሆኑ ለወትሮው ከምዕራባውያን ጋር በበጎ ዓይን የማትተያየው ሩሲያም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሯን ሰርጌይ ላቭሮቭን ወደ ፓሪስ ልካለች፡፡ የስፔኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ማሪ⍰ኖ ራጆይ፣ የዮርዳኖሱ ንጉስ አብዱላህ ሁለተኛ እንዲሁም የማሊው ፕሬዚዳንት አቡበከር ኬይታም ከፓሪስ ጋር ያላቸውን ህብረት በቦታው ተገኝተው ካሣዩት የዓለም መሪዎች መካከል ይገኙበታል፡፡

የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን በበኩላቸው በአደጋው የተሠማቸውን ሀዘን ገልፀው አሸባሪዎችን ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት ሁሉ ሀገራቸው ከፈረንሣይ ጎን እንደምትቆም አስታውቀዋል፡፡

የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁም «የጋራ ጠላታችን የእስልምና አክራሪነት እንጂ መደበኛው የእስልምና እምነት ተከታይ አይደለም» በማለት ተናግረዋል፡፡፡ በስፔን ማድሪድ ጥቃቱን ለመቃወም የወጡ ሙስሊም ሰልፈኞች በበኩላቸው «ኢስላም የሠላም መገለጫ እንጂ የሽብር ምንጭ አለመሆኑን» ገልፀው ሠላምና ፍቅር እንጂ እንዲህ ያለውን ጭካኔ አንደግፍም» ሲሉ ተደምጠዋል፡ ፡ በሌሎች ሀገራትም አደባባይ የወጡ የእስልምና እምነት ተከታዮች «የአሸባሪዎች ድርጊት እስልምናን አይገልፅም፡፡ እስላም የሰላም ሃይማኖት ነው፡፡፡» በማለት አቋማቸውን ገለፁ፡፡ በፓሪስ ተገናኝተው የነበሩት የአሜሪካና የአውሮፓ የውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሮች ባደረጉት ምክክር «በትብብር የተጠናከረ ሥራ በመስራት የአሸባሪዎችን ጥቃት መመከት አለብን» የሚል መግባባት ላይ ደረሡ፡፡ ለወትሮው ሽብርን በመከላከል ዙሪያ ባላት ቁርጠኛ አቋም የምትታወቀው ኃያሏ አገር ዩናይትድ ስቴትስ በዚህ በርካታ የዓለም

መሪዎች በተሠበሠቡበት ታላቅ የተቃውሞ መድረክ በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የሚገኝ ባለሥልጣን ባለመላኳ በበርካታ የዓለም ሚዲያዎች ተብጠልጥላለች፡፡ ይህን ተከትሎም በየካቲት ወር መጀመርያ ላይ ዓለማቀፍ የፀጥታና የደህንነት ጉባዔ ለማዘጋጀት መወሰኗን አስታውቃለች፡፡ የፓሪሱ ጥቃት በበርካታ የማኅበራዊ ድረገፆችም ተቃውሞ ገጥሞታል፡ ፡ በተለይ ፈረንሳያውያን «juis Charlie (እኔም ቻርሊ ነኝ)» የሚል መፈክር ነበር ለተቃውሟቸው የተጠቀሙት፡፡ የዚህኑ ቋንቋ ትርጉም በእንግሊዘኛ ፅፈው « I am Charlie» የሚል መልዕክት በማስተላለፍ ከፈረንሳዮች ጎን መሆናቸውን ያረጋገጡ የዓለም ሠዎችም በርካታ ናቸው፡፡





የቤልጂየም እና ጀርመን ጥቃቶች

የፓሪሱ አስደንጋጭ ዜና በተሠማ ጥቂት ቀናት ውስጥ በቤልጂየም ዋና ከተማ ብራሠልስ ውስጥ የተደረገ የሽብር ጥቃት ሙከራም ነበር፡፡ በተከፈተው የፀረ-ሽብር ዘመቻም በብራሰልስና በአካባቢዋ ከፍተኛ አሠሣ ሲደረግ ነበር፡፡ በተለይ በምስራቅ ቤልጂየም በተካሔደው ዘመቻ ሁለት ተጠርጣሪ አሸባሪዎች ተገድለው አንድ ሠው በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡ ዘመቻው በዋነኝነት ትኩረት ያደረገው ከሦሪያ በተመለሡ ፅንፈኛ አክራሪዎች ላይ ሲሆን እነኚህ ቡድኖች ከፍተኛ የሽብር ጥቃት የማድረስ ዓላማ እንደነበራቸው ተነግሯል፡ ፡ ሁለቱ ተጠርጣሪዎች የተገደሉትም ፖሊስ ላይ ተኩስ መክፈታቸውን ተከትሎ ነው፡፡ በዚህ ስጋት ውስጥ ያለቸው ቤልጂየም ሽብርተኝነትን ለመከላከል ያስችላል ያለቸውን አዲስ የፀረ- ሽብር ህግ እቅድ በጠቅላይ ሚኒስትሯ በኩል ይፋ አደርጋለች፡፡

አሥራ ሁለት ነጥቦች የያዘው ይህ ዕቅድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝየሀገሪቱወታደሮች በፀጥታ ማስከበር ላይ መሣተፍ እንዲችሉ ይፈቅዳል፡፡ አሸባሪዎች ይገኙባቸዋል ተብሎ በታመነባቸው አካባቢዎች በተደረገ አሠሣ አሥራ ሦስት ተጠርጣሪ አሸባሪዎች ከተያዙና ሁለቱ ከተገደሉ በኋላ ይፋ የሆነው ይህ ዕቅድ ከሀገሪቱ ወጥተው ከአክራሪ ቡድኖች ጋር በሚንቀሳቀሱ ዜጎች ላይ ጠንካራ ቅጣት የሚያስተላልፍ እንዲሁም ሽብርተኝነትን በገንዘብ በሚደግፉት ላይ ንብረታቸውን እስከማገድ የሚያደርስ እርምጃ የሚያስወስድ ነው፡፡ ቤልጂየም ከዚህ የጥቃት ሙከራ በኋላ ወታደሮችና ፖሊሶችን አስተባብሮ ደህንነቷን በመጠበቅ ጉዳይ ላይ ከፈረንሣይ ጋር ተባብራ መስራት ጀምራለች፡፡ በቤልጂየም ጎዳናዎች ላይ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው ወታደሮች ተሠማርተው በተለይ የአይሁዳውያን ትምህርት ቤቶችንና የመንግስት ህንፃዎችን በንቃት መጠበቅ ይዘዋል፡፡ ግሪክ በበኩሏ ከቤልጂየሙ የሽብር ጥቃት ሙከራ ጋር ግንኙነት አላቸው ያለቻቸውን አራት ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር አውላለች፡፡

አውሮፓዊቷ ጀርመንም የሽብር ጥቃት ሙከራው በመጠኑም ቢሆን የታየባት ሌላኛዋ ሀገር ነች፡፡ ለቻርሊ ሄብዶ ማተሚያ መረጃዎች ይሠጥ በነበረው ሀምቡርግ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የጀርመን ጋዜጣ ማተሚያ ቤት ላይ የሽብር ጥቃት ሙከራ ተደርጓል፡፡ ማንነታቸው ያልተለየ ሠዎች በማተሚያ ቤቱ ላይ ድንጋይ የወረወሩ ሲሆን በእሣት እንዲያያዝ ማድረጋቸውም ተነግሯል፡ ፡ በዚህም የህንፃው ሁለት ክፍሎች አደጋ ደርሶባቸዋል፤ የማተሚያ ቤቱ የፅሁፍ ሠነዶችም ተቃጥለዋል፡፡ በሠው ላይ ምንም አይነት ጉዳት አልደረሠም፤ አደጋውን አድርሠዋል የተባሉ ተጠርጣሪዎችም በፖሊስ ተይዘዋል፡፡

የቻርሲ ሔብዶ ተቃዋሚዎች

በየሣምንቱ ዘወትር ረቡዕ አስቂኝ ነገር ግን መልዕክት ያላቸው የካርቶን ምስሎች እያሣተመ ለገቢያ የሚያቀርበው የቻርሊ ሄብዶ ኩባንያ የግራ ዘመም የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያራምድ ነው፡፡ በማተሚያ ቤት ህንጻው ላይ በደረሠበት ጥቃት በርካታ አባላቱ በተገደሉ ማግስት ቀሪዎቹየመፅሔትአባላትሣምንታዊውን መፅሔት ቁጥር 1178 መስከረም 14 ቀን ለገቢያ አቅርበዋል፡፡ ለወትሮው በፈረንሣይ ሀገር ብቻ ይሠራጭ የነበረው ምፀታዊ መፅሔት ከ60,000 ቅጂ በላይ አይሸጥም ነበር፡፡ በስድስት የተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጀው የዚህ ሣምንት ዕትም ግን ሠባት ሚሊየን የሚደርስ ቅጂ አሣትሟል፡፡ መፅሔቱም በከፍተኛ ደረጃ ተሸጠቶቧል፡፡


የቻርሊ ሄብዶ መፅሔት የነበዩ መ ሐ መ ድ ን የካርቶን ምስል ይዞ መውጣቱን ተከትሎ በፓኪስታን የካራቺ ከተማ ለተቃውሞ የወጡ ዜጎች ከፖሊስ ጋር ተጋጭተው በግፊት ውሃ እና በአስለቃሽ ጭስ ተበትነዋል፡ ፡ ከአርብ ፀሎት በኋላ በተካሔደው የተቃውሞ ሠልፍ አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ለተባለው የፈረንሣይ መገናኛ ብዙኀን የሚሠራ የፎቶ ጋዜጠኛ ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ ሌሎች አራት ሠዎችም ጉዳት እንደደረሠባቸው ነው የተገለፀው፡፡ በየመን ዋና ከተማ ሠነአ በሚገኘው የፈረንሣይ ኤምባሲ ቻርሊ ሄብዶን ለመቃወም የወጡ የእስልምና እምነት ተከታዮችም «የመፅሔቱ አዘጋጆች እኛንም ሃይማኖቶችንንም ሊያከብሩ ይገባል» ብለዋል፡፡ «በነቢያችን ላይ መቀለዳችሁን ካላቆማችሁ አንድ ቀን ታዝናላችሁ፡፡ » የሚል መልዕክት ነው ከሠልፈኞቹ የተደመጠው፡፡

በምዕራብ አፍሪካዊቷ ኒጀር ለተቃውሞ የወጡት ሠልፈኞች ደግሞ አስራ አንድ ቤተ ክርስቲያኖችን ያቃጠሉ ሲሆን አስር ያህል ሰዎች መሞታቸው ተዘግቧል፡፡ በኒጀር የሚገኙ የፈረንሣይ ንብረቶች ላይም ጉዳት ደርሷል፡፡ በሶማሊያ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ኢራናውያንም እንዲሁ በነብዩ መሐመድ የካርቶን ምስል የተማቸውን ቅሬታ በአደባባይ ከገለፀ የዓለም ማኅበረሠብ መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የአውሮፓ ህብረት

የፈረንሳዩን ጥቃት ተከትሎ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ የገቡት የአውሮፓ ሀገራት መሪዎች ሽብርተኝነትን ለመከላከል በተናጥል ከሚወስዷቸው እርምጃዎች ጎን ለጎን በአውሮፓ ህብረት በኩል ተገናኝተው ምክክር አድርገዋል፡፡ የአክራሪ ሙስሊሞችን ጥቃት ለመከላከል ሀገራቱ ከሚፈጥሩት ህብረት ባሻገር የሙስሊም ሀገራት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸውም ገልፀዋል፡፡ ፌዴሪካ ሞጌሪኒ የተባሉት የአውሮፓ ህብረት የውጪ ጉዳይ ኃላፊው የአረብ ሊግ ኃላፊው ነቢል አል-አረቢን አግኝተው የአብረን እንስራ መልዕክታቸውን አድርሠዋቸዋል፡፡ በእርግጥ የአውሮፓ የፓለቲካ የመሬት መንቀጥቀጥ የተባለውን የሰሞኑን የአክራሪ እስልምና ቡድኖች ጥቃት አውሮፓውን የከፋ ችግር ሣያደርስ ከወዲሁ ማስቆም ይችሉ ይሆን? መልሱን ጊዜ የሚያሣየን ይሆናል፡፡

አዲስ መፅሐፍ በገበያ ላይ !



ጸጥኛ ፍቅር

አዲስ የግጥም መድብል

ስንቱን ንቂ ውዬ
ስንቱን ችዬ ኗሜ
ሲያስገድፈኝ ያድራል
ስንተን እያዘጣ ዘናፍቀ ሕልሜ

በብሩክታዊት ጎሳዬ

በሁሉም መጽሐፍት መደብርና በአዟሪዎች እጅ ያገኙታል

አንዳንድ ነገሮች

የስልክ ፈጣሪው አሌክስ አንደር ግርሃም ቤል በፈጠረው አዲስ የስልክ ቴክሎኖጂ ወላጅ እናቱንና ባለቤቱን አላነጋገራቸውም፤ ምክንያቱም ሁለቱም መስማት የተሳናቸው ነበሩ።።

የሙዚቃ ጂኒየሱ ሞዛርት ገና የአራት ዓመት ልጅ በነበረበት ጊዜ በግማሽ ሰዓት ውስጥ አንድ ሙዚቃ አጥንቶ ጨርሶ ነበረ።።

በዚህ ዘመን ስዕሉ በከፍተኛ ሽያጭ የቁጥር አንድ ደረጃ ይዞለት የሚገኘው ሰዓሊ ቪንሰንት ቫን ጎግ በህይወት እያለ ሊሸጥለት የቻለው ስዕል አንድ ብቻ ነበር።።

የሚሊየኖችን ህይወት የጨፈለቀው አዶፍ ሂትለር አርክቴክት የመሆን ከፍተኛ ፍላጎት አስትሪያ ቪዬና ውስጥ በሚገኝ አንድ የአርክቴክቸር ትምህርት ቤት ውስጥ ለመማር ሞክሮ ነበር።። ነገር ግን ወደ ት/ቤት ውስጥ ለመግባት የሚያስችለውን የመግቢያ ፈተና ማለፍ ሳይችል ቀርቷል።።

ዛሬ በበርካታ የቴሌቭዥን ቃለ ምልልስ ፕሮግራሞችን ማየት የተለመደ ነው።። ለመጀመሪያ ጊዜ የቴሌቭዥን ቃለ ምልልስ የታየው ኤ.ኤ ኤፕሪል 1930 ላይ ሲሆን ቃለምልልሱንም ያደረገችው አይርላንዳዊ ተወላጅ የሆነችው ተዋናይት ፔጊ ኦኔል ነበረች።።

ይህን ያውቁ ኖሯል ?

- በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ የተመሰረተው ቤተክርስቲያን ቀራኒዮ መድህኢያለም ነው።።

- ምስጦች ለመኖሪያነት የሚሰሩት ቤት ኩይሳ ይባላል።።

- ሻላና ቪክቶሪያ በተባሉ ሁለት የአፍሪካ ሀይቆች ስም ግጥም በመግጠም ፤ግጥሙ በአፍሪካ ሕብረት አዳርሽ ላይ የተሰቀለለት ኢትዮጲያዊ ገጣሚ ብሩክ ገ/መድህን ነው።።

- የግሪኝ አህመድ ሙሉ ስሙ ኢብን ኢብራሂም አህመድይባላል።።

- ሲያሸልብ አንድ አይኑን ብቻ የሚከድን እንስሳ ዶልፊን ነው።።

- የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የንግስና በአላቸው በየዓመቱ ጥቅምት 23 ይከበር ነበር።።

- ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሀገራችን የገባው የመኪና አይነት ፎርድ ነው።።

- የመጀመሪያዋ አውሮፕላን ወደ ሀገራችን ስትገባ የተሰጣት ስያሜ ምስለ ተፈሪ ነበረ።።

- የዓለም ጤና ድርጅት (who) ዋና ጽፈት ቤቱ ስዊዘርላንድ ጀኔቭ ይገኛል።።

- የዛጉዌ ነገሥታት መቀመጫ ቦታቸው ሮሃ ወይም ላሊበላ ነበር።።

- ‹ወፌ ቆመች›የተሰኘው የግጥም መድ ብል ገጣሚ ወንድዬ አሊ ነው።።

አባባሎች

«በአካል ከመሞት ይልቅ በህሊና መሞት የበለጠ መራራ ነው።።

የረጋ አዕምሮ ባለቤት መሆን ማለት የሕይወት ስንክሳርን እንደያመጣጡ መቀበል ማለት ነው።።

«ስህተቶች ከመፈጠራቸው በፊት እንዳይከሰቱ አድርጋቸው።።»

«አንተነትህን የሚገልፀው ስራህ ይሁን።። »

ምኞታችን ሲሳካ ብዙ ጊዜ ሃዘን ይሰማናል።።

ደስታ ዱርዬ አይደለም ።።ሰዎች ዱርዬ እየመሰላቸው በየመጠጥ ቤቱ ይፈልጉታል።።

ብዙ ሰዎች ምክር ይቀበላሉ ጥቂቶች ብቻ ይተርፉበታል።።

ካነበብኩት /ሰኢድ ኑሩ/

የትምህርት ቤት ቀልድ

‹ተነስ ሰብስብልኝ ማርክ አለው›

በአንድ የግል ትምህርት ቤት አንደኛ ደረጃ የሚያስተምር መምህር ተማሪዎችን በሬዲዮ የትምህርት ፕሮግራም እንዲያዳምጡ እየመራቸው በሬዲዮ የሚተላለፈውን ትምህርት እየተከታተለ ያስረዳቸዋል።።

በሬዲዮ ትምህርት የሚያስተላልፈው መምህር «እባኮትን መምህር ለተማሪዎች የአንድ ብር ኖታ አውጥተው ያሳዩቸው» ሲል በከፍል ውስጥ ያለው አስተማሪ አንድ ብር ከቦርሳው አውጥቶ ለተማሪዎቹ አሳያቸው ፤ ቀጥሎም በድጋሚ የሬድዮ መምህሩ የአምስር ብር ኖታ አሳያቸው ሲል በከፍል ውስጥ ያለው መምህር አሁንም ብሩን ከቦርሳ ውስጥ በማውጣት ለተማሪዎቹ አሳየ፤ እንዲህ እንዲህ እያለ እስከ ሃምሳ ብር በማውጣት ለተማሪዎች አሳየ፤ በመጨረሻ የሬድዮ መምህሩ እንደለመደው «እባኮትን መምህር ለተማሪዎች የመቶ ብር ኖታ አውጥተው ያሳዩቸው» ሲል መምህሩ ደንግጦ ፀጥ አለ፤ ይህን ያዩት ተማሪዎቹ ከቦርሳቸው መቶ ብር በማውጣት ይህው ይኸው እያሉ እጃቸውን አወጡ፤ መምህሩም ፈጠን ብሎ «አለቃ በል ተነስተህ ከሁሉም ላይ ሰብስብልኝ፤ ማርክ አለው።።» ብለው እርፍ!

‹ፍሬንድ ሺፕ›

አስተማሪው ወደ ከፍል በመግባት ተማሪዎቹን «ዛሬ የፍሬንድ ሺፕ ቀን ስለሆነ የምንወያየው በዚህ ርዕስ ላይ ይሆናል።። እስቲ ከናንተ ውስጥ ስለ ፍሬንድ ሺፕ የሚያስረዳኝ ማነው?» ሲል ጠየቀ፤አንድ ሞልቃቃ ተማሪ እጁን ታነሳለች፤ እሱም እንድትመልስ ፈቃዱን ይሰጣታል፤ «ያው ቲቸር! እኔ እንደሚታወቀው ብዙ ጓደኞች አሉኝ፤ፍሬንድ ማለት ጓደኛ ሲሆን ሺፕ ደግሞ በግ ነው።። »

ታሳሳቅ ሰዎች ምን አሉ

- ማንበብ ሙሉ ሰው፤ ስብሰባ ዝግጁ ሰው፤ መጻሐፍት ትክክለኛ ሰው ያደርገናል።።

(ቢንጃሚን ፍራንክሊ)

- ለእብሪተኞች ጦርነት ማለት ሰላም፤ ነፃነት ማለት ባርነት፤ ማህይምነት ማለት ጥንካሬ ነው።።

(ጆርጅ አርዌል)

- ብልሆች በምክንያት፤ ተራ ሰዎች በዘልማድ ፤ ደደቦች በራስ ጥቅም፤ ጨካኞች በደመነፍስ ይመራሉ።።

(ሊሰር)

- እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ብሎ ድርቅ የሚል ሰው የደንቁርናው ምስክር ነው።።

(ሚካኤል ሞንቴን)

ቅኔ

- ተዋት አትገላግሏት እሩቅ ነው መንገዷ
የከበደ ነገር ይዛለች በሆዷ።።

- ልጅ ልጅ አብቦ እንዲህ የሚታየው
ይህ ተክላችን አዲስ አበባ ነው።።

- እያለለት መልኬ ከአንገቴ በላይ
እጅ እጄን ያየኛል ያ ዓለም አተላይ

ስፈ.ምጣና ቁቦ

ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ - ይበጣጠስ
- ለፋሲካ ይሆናል
ሳይቃጠል - በቅጠል
- እሳት አደጋ አይመጣም
የምላስ ወለምታ - በቅቤ አይታሸም
- ደደቢት ላይ ታየ
ውሃ በለዘበታ - ድንጋይ ይፈነቅላል
- መች ይዳረሳል

ፎዚያ ሰኢድ
/ከስውችብስ ተፌ/

ከአይን የራቀ - ከልብ ይርቀል
- ከኔትወርክ ይርቃል
መካሪየሌለው ንጉስ -አንድ ዓመት አይነግስም
-ሰልፍ ከለከለ
ዶሮ ብታልም - ጥሬዋን ነው
- ምርጫው እስኪደርስ
እባብ ልቡን አይቶ - እግር ነሳው
- ጨጓራውን ሸጠ
የቀበሮ ባህታዊ - ከበግ መሀል ይፀልያል
- ቦንድ ልግዛአለ
የቀበጡ ዕለት - ሞት አይገኝም
- መግለጫ ሰጡ

(ሰናይ ገ/ሠድን)

ፋሽን/ውበት

የሚዜ ልብስ



በሀገራችን ወርሃ ጥር በአብዛኛው ሙሽሮች የጋብቻ በአላቸውን ለማክበር የሚመርጡት ጊዜ ነው፡፡ ሙሽራና የሠርግ ድግስ ሲታሰብ ለዝግጅቱ ድምቀት ሲባል አብረው የሚደረጉ በርካታ ዝግጅቶች ይኖራሉ፡ ፡ በዕለቱ ከሙሽሮች ቀጥለው አምረውና ደምቀው የሚታዩት ሚዜዎች ናቸው፡፡ ሚዜዎች የሙሽሪትና የሙሽራው ጓደኞች ወይም ዘመድ ወዳጆች ሊሆኑ ሲችሉ፤ ሙሽሮችን አጅበው ዝግጅቱ ድምቀት እንዲኖረው ያደርጉታል፡፡

ሚዜዎች ልክ እንደሙሽሮቹ ሁሉ በሠርጉ ዕለት አምረውና ደምቀው እንዲታዩ ለውበታቸው አስቀድመው መጨነቅና መጠበብ የማይቀር ነው ፡፡ ምን አይነት ቀለም ያለው የሚዜ ልብስ እንደሚለብሱ፣የትኛው አይነት ዲዛይን ያለው ልብስ የቱ እንደሚጠቀሙ፣የወቅቱ ፋሽን የሚዜ ልብስ እንደሆነ አስቀድመው ሠርጉ ከመቃረቡ በፊት የወንድም ሆነ የሴት ሚዜዎች መወሰን አለባቸው፡፡ የሚመርጡት የሚዜ ልብስም በቀለሙም ሆነ በዲዛይኑ የወቅቱ ፋሽን ከመሆኑ በላይ በተቻለ መጠን ሚዜ ለሚሆኑ ሰዎች ተስማሚ መሆን አለበት ፡፡ ለዚህም ሲባል አስቀድሞ መነጋገር ያስፈልጋል፡፡

የሴት ሚዜ ልብስ በተለይ በአሁኑ ወቅት ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ በዲዛይንእና በቀለም ምርጫ በርካታ አይነት የሚዜ ልብሶች በገቢያ ላይ ይገኛሉ፡ ፡ በአብዛኛውን ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው የሚዜ ልብስ ግን መገተሪያ የገባለት የሚዜ ልብስ ነው፡፡ ይህ የሚዜ ልብስ የመኮፈስ / ቡፍ/ የማለት ባህሪ ሲኖረው ባለአንድ ማንገቻና ከጡት በላይ ከፍት ሆኖ ይዘጋጃል። እነዚህ ልብሶች እንደ ቀለማቸው አይነት ተመሣሣይ መጫሚያ ቢደረግላቸው የሚዜዎችን ውበት ይበልጥ ያጎለዋል፡፡ ሚዜዎች ሲዋቡ ደግሞ ሙሽሮቹ ይደምቁሉ፡፡

በዚህ መሠረት ቀይ ልብስ ከቀይ ጫማ ጋር ተስማሚ ይሆናል፡፡ በተለይ ለሴቶች ጫማው ሹል ሆኖ ከፊት ከፍት ባይሆን ይመረጣል፡፡ በተለይ አጠር ያለች ሚዜ የውበቷን ድባብ ለማሞቅ ከፍ ያለ ሹል ጫማ ብትመርጥ ለአቋሟምሆነ ለሠርጉ ቃና እንከን የለሽ ይሆናል፡፡

ሚዜና ሙሽራው በአብዛኛው ጊዜ እንደሚታየው የተለየ የአለባበስ ስታይል አላቸው ፡፡ በተለይ የወንድ ሙሽራ ሚዜዎች ከተስተካከለ ቁመና ጋር ከሙሽራው የአለባበስ ስታይል የተለየ አለባበስ በመጠቀማቸው የልዩነት ምርጫ በራሱ የሚፈጥረው ህብረ-ውበት ለአጃቢዎችም ሆነ ለዕድምተኛው ልዩ ሥሜት ያጭራል፡፡ ከተለያየ አለባበስ የሚመዘዘው የውበት ፀዳል የትየለሌ ነው፡፡

የሚዜ ልብሶች በባህሪያቸው በርከት ያሉ ናቸው፡፡ ይህም በወቅቱ ፋሽን የሚወሰን ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ጉርድ አላባሽ የሆነ አለ፤ነገር ግን ሲለበስ ወጥ ይሆናል፡፡ ኪሎሽ ቅድ የሆኑ የሚዜ ልብሶችም አሉ፡ ፡ በግማሽ ጎኑ ረጅም ሆኖ በሌላ ጎኑ ደግሞ የሚያጥር የሚዜ ልብስ ሌላው አማራጭ ነው፡፡ ባለአንድ እጅ የሚዜ ልብሶችም አንድ እጃቸው በአበባና በፈርጥ የተጌጠው እነዚህ ሁሉ የወቅቱ የሴት ሚዜዎችን ውበት የሚያወጡ ቅርጽና ይዘታቸው የተለያዩ የሚዜ ልብስ ስታይሎች ናቸው፡፡





በሠርግ ወቅት የሚስተዋሉ የተለመዱ የሚዜ ሻርፕ (ስካርብ) መጠቀም በአሆኑ ወቅት ፈጽመው የቀሩ ናቸው ባይባልም ተጠቃሚ አላጡም፡፡ በሚዜ ልብሱ ላይ ሻርፑን መደረብ የሚዜ ልብሱን ውበት የመቀነስ ባህሪ ቢኖረውም ማታ ማታ ብርድ ለመከላከል የሚሰጠውን አስተዋጽኦ መዘንጋት የለበትም፡፡

በሠርግ ዕለት ሚዜዎች አንድ አይነት ያሸበረቁ የሚዜ ልብሶችን ለብሰው ሙሽሮችን ከማጀብ በተጨማሪ ይበልጥ ለፕሮግራሙ ድምቀት የሚሰጠው ለምሳም ሆነ ለእራት ሙሽሮቹ ወደ አዳራሹ ሲገቡ ሚዜዎቹ የሚያደርጉት አንድ አይነት እንቅስቃሴ ለሠርጉ ድምቀት ይሰጠዋል፡ ፡ በተጨማሪም ሴት ሚዜዎች ከለበሱት የልብስ ቀለም ጋር ተመሳሳይነት ያለው የእጅ አበባ ቢይዙ ዝግጅቱን ያደምቀዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የተፈጥሮ አበባዎች በሀገራችን በተለያየ አይነት ቀለማት እየተመረቱ ስለሚገኝ ከአርቴፊሻል አበባ ይልቅ የተፈጥሮን መጠቀሙ ይበልጥ ተመራጭ ነው፡፡

ይድረስ፡-
ለተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን





ለአምስተኛ ጊዜ የሚደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ከአምስት ያነሡ ወራት በቀሩት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡ ፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ፅ/ቤትም ለምርጫው የሚያስፈልጉ ግብአቶች የማሟላት ሽርጉዱን ተያይዞታል፡፡ ታዲያ በዚህ ወቅት በተለይ ሰማያዊ ፓርቲ፣ አንድነት እና መኢአድ የተባላችሁት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተረጋጋና ሠላማዊ አካሔድ ውስጥ ያላችሁ አለመሆኑን ከሀገሪቱ መገናኛ ብዙኀን እየሠማን ነው፡፡ በተለይ የአንድነት ፓርቲ እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በውስጣችሁ ተፈጠረ የተባለው ከፍፍል እጅግ አሣስቦናል፡፡ ገና ወደ ማማው ላይ ወጥታችሁ ሀገር ታስተዳድራላችሁ የምትባሉ ፓርቲዎች እርስ በእርስ እንኳ መስማማት ካቃታችሁ በምን አምነን ልንመርጣችሁ እንችላለን፡፡ ስያሜያችሁ አንድነትን እየሠበከ በውስጣችሁ ያለው የእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ፉክክር ሲያጋጫችሁ መስማት አሣዘኝ ነው፡፡

የምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት እንደሚገልፀው የአንድነት ፓርቲ አመራሮች በፓርቲው ስም በየፊናችሁ ሁለት ጠቅላላ ጉባዔ ጠርታችኋል፡፡ ያለመግባባታችሁ ምክንያትም ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው የውስጥ አዲት አለመኖርና በፓርቲው ውስጥ ያለው ስር የሠደደው ሙስና መሆኑ ተነግሯል፡፡ ገና ምኑንም ሳትይዙት ሙስና ውስጥ መዘፈቃችሁ (እውነት ከሆነ) እጅግ የሚያሣፍር ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ ራሱ አልፀዳሁበትም ያለውን የሙስና ችግር እንደ ተቃዋሚ ፓርቲ ተከታትላችሁ በማጋለጥ ማስቆም ሲኖርባችሁ እናንተም በጉዳዩ መጠርጠራችሁ «የአባትህ ንብረት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ አይነት ነገር ይመስላል፡፡


ወድ ተቃዋሚዎች፡-

መቼም ገዢው ፓርቲ እንኳን ሠበብ አግኝቶባችሁ ድሮም ደካማነታችሁን ከመዘርዘር ተቆጥቦ አያውቅም፡፡ ሀገርን ማስተዳደር የሚያስችል ኃላፊነት መሸከም የሚችል ጫንቃ እንደሌላችሁ አዘውትሮ ይናገራል፡፡ ይኸው እናንተም ስማችሁን በበጎ ነገር ከማስጠራት ይልቅ «ገና ወጡ ሣይወጠወጥ» በስልጣን ሽሚያ ትታመሣላችሁ፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት / መኢአድ/ ፓርቲ የአመራሮቹ መከፋፈልም እንዲሁ በሚድያዎች እየተናፈሰ ነው፡ ፡ ይህን የከፍፍል ወሬ የሰሙ አንዳንድ ሰዎች እንዲያውም «ተቃዋሚ ፓርቲዎች ራሳቸውንም መቃወም ጀምረዋል» በማለት እያሟችሁ እኮ ነው፡፡ ይታያችሁ እስቲ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የሚል ግዙፍ ስም ይዞ መላው ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ «የሚታገል» ድርጅት ጥቂት አባላቱን ማስማማት አቅቶት በሁለት አመራሮች ሲከፋፍል ምን ይባላል?

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ትኩረት በማግኘት መነጋገሪያ እየሆነ የመጣው ሰማያዊ ፓርቲም እንዲሁ ከሥርዓት አልበኝነት ጋር ተያይዞ በምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት ስሙ እየተነሣ ይገኛል፡፡ የጋራ ምክክር መድረኮች ረግጦ የመውጣት፣ ምርጫ ቦርዱን በሃሠት የመወንጀል እና ስም የማጥፋት ህገ ወጥ ተግባራት አከናውኗል

አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ!

ሰይጣን አምላኪዎቹ 3



የሕጻናትን ደም የሚጠጣው የሚስጥር ማኅበር እና ሌሎችም...

ወርቅአፈራሁ አሰፋ

በየመፅሀፍ መደብሩና በአዟሪዎች እጅ ይጠይቁ!

ማመንና መታመን



በህይወታችሁ እጅግ አምናችኋቸው የልባችሁንና የቤታችሁን ጓዳ ያሳያችኋቸው፤ ከማንም በላይ የተለየ ክብር ሰጥታችሁ መከታ ያደረጋችኋቸው፤ የምስጢራ ተጋሪ፤ የችግር ቀን ደራሼ ብላችሁ እጅግ የተመካችሁባቸው፤ ስለታማኝነታቸውን ለመናገር ቃላት አጥረዋችሁ በስማቸው ስትምሉ ኖራችሁ ሰዎች ድንገት ባልጠበቃችሁት ሁኔታ ሸርተት ብለው እንደ ይሁዳ የከዷችሁ ሰዎች አይኖሩ ይሆን? አመኔታችሁ ለጉዳት አሳልፎ ከሠጣችሁ በኋላስ 'ሰውን ማመን ቀብሮ ነው' ብላችሁ አልተረታችሁ ይሆን?

ሰዎችን ማመን የተሟላ፣ ደስተኛና ትርጉም ያለው ህይወት ይሰጠናል። የሰው ልጅ ማህበራዊ እንሰሳ እንደመሆኑ በጎዘንና በደስታ በህብረት ድንኳን መጣሉ፤ አይዘህ መባባሉ የተለመደ ነው። ለረዥም ጊዜያት ከሰዎች ተለይተው የኖሩ ሰዎች የሚገጥማቸውን የአዕምሮ መታወክ ስንመለከትም በእርግጥ የሰው መድኃኒቱ ሰው እንደሆነ ይገባናል። ታዲያ የምንተነፍሰውን አየር ያህል ለህይወታችን የሌሎች ሰዎች አጋርነት አስፈላጊ ከሆነ ከሰዎች ጋር ለረዥም ጊዜ በአብሮነት ለመዝለቅ የሚያስችለንን እምነት እንዴት ማግኘት እንችላለን?

Neotechie የተባለ ድረ-ገፅ ሰዎችን ማመን ያለባችሁ በቅድሚያ እነኚህ ነገሮች ተሟልተው ሲገኙ ነው ይለናል።

የሌሎችን መልካም ጎን መመልከት

አሁንም ድረስ በዓለማችን ላይ ጥሩ ሰዎች አሉ፡ ከአንድ ሰው ጋር ስንገናኝ ቀድመን ስለዚያ ሰው አሉታዊ ነገሮችን ማሰብ ተገቢ አይደለም። ያ ሰው ጥሩ አስተሳሰብ ቢኖረው እንኳን ልናምነው አንችልም። ስለዚህ የሰዎችን መልካም ጎን መመልከት ማኅበራዊ ህይወታችን በመተማመን የተሞላ እንዲሆን ያደርጋል።

እውነቱን መነጋገር

እኛ የምንዋሽ ሰዎች ከሆንን ሌሎችም እንደሚዋሹ ነው የምናስበው። ስለዚህ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢገጥሙን እንኳ ሁሌም እውነት መናገር አለብን። አንዲት ትንሽ ውሸት በሰዎች ዘንድ የሚኖረንን እምነት ልታሳጣን ትችላለች፡ ምናልባት በግዴታ ውስጥ ሆነን ውሸት የተናገርን ቢሆን እንኳ መዋሸታችን ስህተት መሆኑን አምነን ይቅርታ መጠየቅና ግንኙነታችን ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥል ጥረት ማድረግ አለብን። በሌላ አጋጣሚ በድጋሚ ላለመዋሸትም መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው።

ሰዎችን መረዳት መቻል

ሁሉም ሰው ይሳሳታል። ስለዚህ የሰዎችን ስህተት መቀበል አለብን። አብረውን የሚሰሩ ሰዎች ጓደኞቻችን ወይም የቤተሰባችን አባላት ሲሳሳቱ ወይም ግልፅ ያልሆነልንን ነገር ሲሰሩ እምነታችንን ፈጥነን ከማፍረስ ይልቅ ምክኒያቱን ለመረዳት መሞከር ይኖርብናል።

ይቅር ማለት

ሰዎችን ለማመን ከፈለግን ይቅር የማለት ልምዳችንን ማዳበር መልካም ነው፡ ሰዎችን ማመን ቀላል ነገር አይደለም። ነገር ግን የህይወትን ጣፋጭነት የምናውቀው ሰዎችን ማመን ስንጀምር ነው።

በሌላ በኩል wikihow.com የተባለ ድረ-ገፅም እንዲሁ በሰዎች መካከል መልካም ግንኙነት ለመመስረት መተማመን ቀዳሚ ሊሆን እንደሚገባ ጠቁሞ በሌሎች ዘንድ መታመን እንድንችል የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ መልካም ነው ሲል አስፍሯል።

ቃላችንን መጠበቅ

ምናልባት የገባነው ቃል ቀላል እና ብዙም ለውጥ የማያመጣ መስሎን ላንፈፅመው እንችላለን። እኛ ትኩረት ያልሰጠነው ነገር በሌሎች ዘንድ ትልቅ ዋጋ ያለው ሊሆን ስለሚችል የተናገርነውን በተግባር ባለማዋላችን ወዳጆቻችን ተቀይመውን ግንኙነታችንም እስከመጨረሻው ተቋርጦ ይቀራል። ስለዚህ በቃላችን መገኘት ከሰዎች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት በመተማመን የተሞላ እንዲሆን ያደርጋል።

የልባችንን መናገር

ከአንገት በላይ የሆነ ግንኙነትም ሆነ ንግግር ወዳጅነታችንን አደጋ ውስጥ የሚከት በመሆኑ ንግግራችን እውነተኛ ስሜታችንን የሚገልጽና ከልባችን የሚወጣ መሆን አለበት። ከተናገርን በኋላ ወዳጆቻችን ተራውን ወስደው ሲናገሩም ከልባችን በማድመጥ ለሚያነሷቸው ጉዳዮች ያለንን አክብሮት እንዲገነዘቡ ማድረግ ተገቢ ነው።

ግልፅነት

ግልፅነት የመተማመን መሠረት ነው፡ ከጓደኞቻችን የምንደብቀው አንዳች ምስጢር አለመኖሩን በማሳየት በግልፅነት ስንቀርባቸው የእነርሱም ግልፅነት የዚያኑ ያህል ይጨምራል። ምናልባት ጉዳዩ የግል ከሆነና የእነርሱን ጣልቃ ገብነት የማይጠይቅ ከሆነ ጉዳዩን በእነርሱ ፊት አለማንሣት የተሻለ ነው። በግልፅነት እጦት ምክኒያት ምን ያህል ሰዎች ተቆራርጠው ቀርተው ይሆን?

የሚል ስሞታ ነው የቀረበበት። ይህ ስሞታ ሀሠት ቢሆን እንኳ ፓርቲው መግለጫ አውጥቶ ማስተባበል በቻለ ነበር። ሀገርን ለመምራት የሚወዳደር ፓርቲ በእንዲህ ያሉ እንከኖች ስሙ ሲጠፋ ዝም ብሎ መመልከት የለበትም፡ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በሀገሪቱ ፖለቲካ የተለመደ ባይሆንም ይቅርታ በመጠየቅ ትልቅነቱን ማስመስከር አለበት። በዚህ ጥቂት ወራት በቀሩት የሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ ታላላቅ አጀንዳዎች አንስቶ ገዢውን ፓርቲ መሞገት ሲገባው ሠማያዊ ፓርቲ «በመድረክ መርገጥ» ስሙ ሲነሳ መስማት አሣዘኝ ነው። ዛሬ መድረክ ረግጦ የወጣ ፓርቲ ነገ የመረጠውን ህዝብ ረግጦ ላለመግዛቱ ምን ዋስትና አለን? ደግሞ ከትጥቅ ትግል ይልቅ በሃሳብ የበላይነት ለማሸነፍ ፈቅዶ ወደ ፖለቲካው ማዕከል የገባ ፓርቲ በርካታ ሃሳቦች የሚንሸራሸሩበት መድረክ መርገጥ ከምሁራን የሚጠበቅ ነውን?

ውድ ተቃዋሚዎች:-

ገዢው ፓርቲ እንደሁ ብልጥ ነው። እንኳን እንዲህ ላይነት ታላቅ ስህተትአግኝቶባችሁ ወትሮም ስማችሁን ከማጠየም ሠንፎ አያውቅም። አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች «በመካከላችሁ ያለውን አለመግባባት በማስወገድ ወደ ምርጫው ፉክክር ግቡ» እንዳሏችሁ የሚገልፅ ዜናስ ከ‹ታላላቅ› ሚዲያዎቻችን አልሠማችሁም? ይኸው መከፋፈላችሁን ሀገር አውቆ አንዳንድ የአዲስ አበባ ሰዎችም ‹እባካችሁ አንድ ሁኑ› የሚል ጥሪ ያቀርቡላችሁ ጀመር።


ኢህአዴግ ዘመናዊ በሚላት ኢትዮጵያ ውስጥ የ1997 ቱ ምርጫ ጥሎ ያለፈውን አሻራ አትዘንጉም አይደል?! አዎን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይደርስብናል የሚሏቸውን ተፅዕኖዎች ሁሉ ተቋቁመው አንድ መሆን ከቻሉ ኢህአዴግን ማንቀጥቀጥ እንደማይሳናቸው ቅንጅቶች አሣይተውናል። በሚሊየን የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ማፍራት ችለውም ተመልከተናል። (የኋላ ኋላ አጨራረሳቸው ያማረ ባይሆንም)

በተለይ አንድነት እና መኢአድ ይህቺን ሀገር ካሉባት ችግሮች አላቅቃችሁ ወደ ብልፅግና ለመምራት በቅድሚያ እንደሰማችሁ አንድ መሆን ይኖርባቸኋል። ገና ስልጣን ሳትይዙ በሁለት አመራሮች የተከፈለቻችሁ ነገ ሀገር የማስተዳደር ኃላፊነት ብንሰጣችሁ እንዴት ትመሩን ይሆን? እኛስ ምናችሁን ዓይተን እንምረጣችሁ?

ውድ ተቃዋሚዎች:-

እባካችሁ ከዚህ በኋላ የመከፋፈልና የስነ-ምግባር ችግር በእናንተ ዘንድ አይሰማ፡ ቢያንስ ለጥቂት አባላቶቻችሁ ክብር ስትሉ እንኳን አካሔዳችሁን አስተካክሉ። እባካችሁ!!

ላ ኩዌ ኖ ፖዲያ አማር



በተለያዩ ጊዜያት የውጪ ሀገር ፊልሞችን እየመረጠ ለተመልካቹ የሚያቀርበው የቀድሞው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በአሁኑ ወቅት ከሚያስተላልፋቸው ፊልሞች መካከል ኩዊዳዶ ኮን ኤል ኤንጅል እና ላኩዌኖ ፓዲያ አማር የተሠኑት ተወዳጅ የሜክሲኮ ፊልሞች ይገኙበታል፡፡ እነኚህ ፊልሞች በብዙ የሀገራችን ፊልም አፍቃሪያን ተወዳጅ መሆናቸውን የተገነዘበችው ቁም ነገር መፅሔት ከዚህ ቀደም በተከታታይ እትሞች ኩዊዳዶ ኮን ኤል ኤንጅል የተሠኘውን ፊልም የታሪኩን ምንነትና የተዋንያኑን የህይወት ታሪክ ስታቀርብ ቆይታለች፡፡ ከዚህ እትም ጀምሮ ደግሞ ላኩዌ ኖ ፖዲያ አማር የተሠኘውን ፊልም ታሪክና የተዋንያኑን የግል ታሪክ ለማቅረብ ትሞክራለች፡፡

በጆዜ አልቤርቶ ካስትሮ ፕሮዲውሠርነት ቴሌቪዛ በተሠኘው እውቅ የሜክሲኮ መገናኛ ብዙኀን ቀርቦ ለመታየት የቻለ ተወዳጅ የሜክሲኮ ፊልም ነው፡፡ የፊልሙ ርዕስ ወደ አማርኛ ቃንቋ ሊመለስ «ማፍቀር የማይችለው/የማትችለው» የሚል ትርጉም ይሠጣል፡፡ የታሪኩ መነሻ ሀሣብ ባለቤት ዲሊያ ፊያ ሲሆን ፀሐፊው ደግሞ ዚሜና ሱዋሬዝ ይባላል፡፡ ጆርጅ ሣሊናስ፣ አና ብሬንዳ ኮንትሬራስ እናጆዜረን የተባሉት ተዋንያን ዋና ገፀባህርያትን የወከሉት ሲሆኑ ሱዛና ጎንዛሌዝ፣ ጁሊያን ጊል እና ፋቢያን ሮብልስ የተባሉት ተዋንያን ደግሞ በፊልሙ ላይ ተቀናቃኝ ገፀባህሪያትን በመወከል ይጫወታሉ፡፡ ላ ሙጀር ኬ ኖፖዲያ አማር የተሠኘውን የዴሊያ ፊያሎ ተከታታይ የሬዲዮ ድራማ ታሪክ ለቴሌቪዥን እንዲስማማ ተደርጎ የተሠራበት ላ ኩዌኖፖዲያ አማር የተሠኘው ይህ ፊልም በምርጥ መሪ ገፀባህርይ እና በምርጥ ረዳት ገፀባህርይ ዘርፎች ሁለት ሽልማቶች ማግኘት የቻለ ነው፡፡

የፊልሙ ሴራ

አና ፓውላ የተባለች በቺፓስ ከተማ የምትኖር ሴት አለች፡፡ ለረጅም ጊዜያት እናቷን ስታስታምም በመቆየቷምክንያት ለታመሙ ሠዎች ያላት ፍቅር እያደገ ሲመጣ የነርስ ሙያ የማጥናት ፍላጎት አደረባት፡ ትምህርቷን አጠናቅቃ ለመመረቅ ጥቂት ጊዜ ሲቀራት ብሩኖ ከተባለ የህግ ባለሙያ ጋር ተዋወቀች፡፡ ይህ የህግ ባለሙያ ደግሞ በደረሠበት አደጋ ምክንያት የእግር ጉዳተኛ በመሆኑ በሁዊልቸር ብቻ ለመንቀሣቀስ የተገደደውን አለቃውን አገናኛትና የግሉ ሀኪም ሆና እንድትቀጠር አደረገ፡፡ ከዚህ ሥራዋ የምታገኘውን ጥሩ ክፍያ እርሷና ሚጉዌል የተባለ ወንድሟን ከልጅነታቸው ጀምሮ ተንከባክበው ያሣደጉትን ሮዛውራ የተባሉ አክስቷን ለመርዳት ታውሰዋለች፡፡

አና ፓውላ ይህንን ሮጂሊዮ የተባለው ሠው በህክምና ለመርዳት ወደሚኖርበት «ሀሲኤንዳዬል ፉኤርቴ» የተሠኘ ቦታ ከሄደች በኋላ የተመለከተቸው የሠውየው ኃይለኛነትና ተቆጪነት አስደንቋታል፡ የዚህ ጸባዩ ምክንያት ደግሞ በደረሠበት አደጋ ምክንያት ጥላው የጠፋችው የቀድሞ እጮኛው ነች፡ ሮጂሊዮ በሚኖርበት ቤት ውስጥ ሲንቲያ የተባለች እህቱ አብራው ትኖራለች፡፡ ሮጂሊዮ እህቱ አጠገቡ ተቀምጣ አስፈላጊውን እንክብካቤ እንድታደርግለት ያስገደዳት ሲሆን ለዚህም ውለታዋ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ ከወንድሟ ታገኛለች፡፡ የምትፈልገውን የኑሮ ዘዴ እንድትከተልም ፈቅዶላታል፡፡ ሲንቲያ አንዳንድ ጊዜ የድብርት ስሜት ሲሠማት ኢፍሬን ከተባለ የቤታቸው የቁጥጥር ሠራተኛ ጋር ትጫወታለች፡፡ እርሷ ድብርቷን ለማስወገድ ትቅረበው እንጂ ኢፍሬን በፍቅሯ ክንፏል፡፡ በዚሁ ቤት ውስጥ ሮጂሊዮና ሲንቲያን እንደ እናት ስትንከባከብ የኖረች ማሪያ ተባለች ሴት አለች፡፡

በፊልሙ ላይ የነርስ ሙያተኛዋ አና ፓውላ የሮጂሊዮን ግትርነትና መጥፎ ስሜት በመታገስ ለመቀጠል ስትቸገር ይስተዋላል፡፡ ስለዚህ ስራዋን ለማቆም ትወስናለች፡፡ በአንድ ወቅት በወንዝ የመስጠም አደጋ ገጥሟት ጉስታቮ ዱራን የተባለ መልከ መልካምና ቅን አሣቢ የምህንድስና ባለሙያ ከአደጋው ያተርፋታል፡ በዚህ አጋጣሚ የተጀመረ ግንኙነታቸው ወደ ፍቅር ቢያመራም ጉስታቮ ከአባቱ ጋር በሚጓዝበት አንድ አጋጣሚ አደጋ ደርስበታል፡፡ አና ፓውላም ጉስታቮ ሞቷል ብላ ታምናለች፡፡

በሌላ በኩል በፍቅሯ ጨርቁን የጣለው ሮጂሊዮ፤ ብሩኖ የተባለ ሠራተኛውን አና ፓውላ ወደ መኖሪያቸው ትመለስ ዘንድ እንዲጠይቃት ይልከዋል፡፡ ጥያቄው የቀረበላት እና መጀመሪያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባትሆንም ሮጂሊዮ የተባለ ወንድሟ ባደረሠው ጥፋት ወደ እስር ቤት መግባቱን ተከትሎ የምታገባው ከሆነ ወንድሟን እንደሚያስፈታላት ሲነግራት በሃሳቡ ትስማማለች፡፡ ከሮጂሊዮ ጋርም ትዳር መሠርታለች፡፡ በዚህ ጊዜ በአንድ ወቅት በወንዝ ከመስጠም አደጋ ያተረፋት ጉስታቮ የተባለ ሠው አና ፓውላን ለማየት ወደ ምትኖርበት ቤት ይመጣል፡፡ ነገር ግን አሣዳጊዋ ሮዛውራ ከአና ፓውላ ትዳር የምታገኘው የገንዘብ ጥቅም እንዳይቀርባት ስትል አና ፓውላ እንደማትፈልገው ትነግረዋለች፡፡ጉስታቮ ይህን ሲሰማ ይናደዳል፤ እስመጨረሻውም እርሷን ለመርሣት ይወስናል፡ ሀሲኔዳ ወደሚገኘው ሮጂሊዮ መኖሪያ ቤት ከገባች በኋላ የአና ፓውላ ህይወት የምድር ላይ ሲዖል ነበር የሆነው፡፡ ሲንቲ የተባለች የሮጂሊዮን እህት ንቀትና ቀናተኝነት ችላ ማሣለፍ አለባት፤ እስር ቤት ያለውን የወንድሟን ችግር መፍታት አለባት፤ ብሩኖ እና ሮዛውራም የእርሷን እጅ እየጠበቁ ነው የሚኖሩት፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ



ደግሞ ጉስታቮ የተባለው የፍቅረኛዋ ሁኔታ ያስጨንቃታል፡ ከእርሡ ጋር ተገናኝተው በአንድ ጎጆ የሚኖሩበትን ጊዜ ትናፍቃለች፡፡ እንግዲህ ታሪኩ እንዲህ እያለ በዚህ መልክ ተዋቅሮ ይቀጥላል፡፡

የፊልሙ ስርጭት

ከሃያ ሁለት ሦዎች በላይ በትወና የተሣተፉበት ይህ ፊልም እ.ኤ.አ ከነሐሴ 1/2011 እስከ መጋቢት 18/2012 ድረስ በሜክሲኮው ካናል ዲ ላስ ኤስ ትሬላስ (የከዋክብቶች ጣቢያ) በተባለ የቴሌቪዥን ቻናል ላይ በተለያዩ ክፍሎች ሲተላለፍ ቆይቷል፡፡ በአሜሪካዋ የኒውዮርክ ከተማ ላይ በሠፈረው ዩኒቪዥን የተባለ የስፓኒሽ ቋንቋ ማሰራጫ የቴሌቪዥን ኔትወርክም ከጥር 2 ቀን 2012 እስከ ነሐሴ 10/2012 ድረስ ለዕይታ በቅቷል፡፡

ተቀባይነት

በአሜሪካው ዩኒቪዥን የቴሌቪዥን ጣቢያ በተላለፈበት የመጀመሪያ ምሽት ብቻ 4.1 ሚሊዮን ተመልካቾች ተከታትለውታል፡፡ በሜክሲኮ ውስጥ ለተለያዩ ሽልማቶች በእጩነት የቀረበ ሲሆን ሁለት ሽልማቶች ለማግኘት ችሏል፡፡ ፊልሙ 166 ክፍሎች አሉት፡፡

ቫቲካን...

ከገጽ 15 የዞረ

በብረቱ ላይ አስገብተው በመቆለፍ መክፈቻ ቁልፉን በቲበር ወንዝ ውስጥ ይወረውሩታል፡፡ ቁልፉን ከወንዙ ውስጥ ፈልጎ ለማግኘት ስለማይቻል የፍቅረኞቹ ፍቅርም ልከ እንደ ጓጉንቸሩ እንደተቆላለፈ ይዘልቃል ነው ሚስጥሩ፡፡ ለዚህም ይመስላል በድልድዩ ብረት ላይ ብዙ የተቆለፉ ቁልፎች የሚታዩት ፡፡ አስጎብኚያችን እንደነገረን በዚህ ድልድይ ላይ ቃል ኪዳን ለመገባባትና በብረቱ ላይ ቁልፉን አስገብቶ ቆልፎ ወደ ወንዙ ለመወርመወር በየጊዜው በርካታ አሜሪውያን ይመጣሉ፡፡

አሁን ከቫቲካን ወጥተን ወደ ሮም ገብተናል፡ የቀረን በጣሊያን ትልቅ የተባለውንና Passsion of the Christ ፊልም ጨምሮ ታላላቅ የሆሊውድ ሲኒማዎች የተሰሩበትን የYhanten Film Complex የፊልም መንደር መመልከት ነው፡፡ ከዚያም በማግስቱ በግዙፍነቱ በአውሮፖ ካሉ አውሮፕላን ማረፊያዎች መሀከል በስምንተኛ ደረጃ ላይ ወደሚገኘውና ከሮም 10 ኪሎ ሜተር ርቀት ላይ ወዳለው ሊዮዎናርዶ ዳቪንቺ አውሮፕላን ጣቢያ በማምራት ወደ ዱባይ መመልስ ነው፤ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ...

ከሰሞኑ

በደሴ ከተማ ዘመናዊ ሲኒማ ቤት ተከፈተ

በጥንታዊቷ እና ታሪካዊቷ ደሴ ከተማ መሀል በሚገኘው ህንጻ ላይ ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ ሲኒማ ቤት መከፈቱ ተገለፀ፡፡


«ብዙ ሲኒማ» የሚል ስያሜ የተሠጠው ይህ አዲስ ሲኒማ ቤት 265 ምቹ መቀመጫዎች ያሉት ሲሆን የአየሩን ሁኔታ የሚቆጣጠር ዘመናዊ መሣሪያ እንደ የተገጠመለት እና ለአደጋ ጊዜ የሚሆኑ 3 መውጫ በሮች እንዳሉት ተነግሯል፡፡

ሲኒማ ቤቱን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የጂታብ (GTAB) ኢንተርቴይመንት ፒ.ኤል.ሲ. ስራ አስኪያጅ አቶ ታዲዮስ ጌታቸው «ደሴ ከተማ ካላት ረጅም ዕድሜ እና የከተማው ነዋሪ ለኪነጥበብ ካለው ጥልቅ ፍቅር አንፃር ሲታይ ደሴ እስካሁን እንዲህ ያለ ዘመናዊ ሲኒማ ቤት ሳታገኝ መቆየቷ የሚያስቆጭ ነው» ብለዋል፡፡

ሲኒማ ቤቱ ኤች.ዲ ዘመናዊ ፕሮጀክተር እና ዘመኑ የደረሰባቸው የድምፅ ቴክኖሎጂዎች የተገጠሙለት መሆኑን አክለው የገለጹት አቶ ታዲዮስ አዳራሹ ከሲኒማ በተጨማሪ እንደ ቴአትር፣ ስታንድአፕ ኮሜዲ እና ሰርከስን ለመሳሰሉ ጥበባዊ ትርዒቶች ምቹ በመሆኑ በዚህ ዘርፍ የሚሠሩ ባለሙያዎች ቢመጡ አብረው ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

አስራ አንድ በአምስት (11x5) ሜትር ስፋት ያለው ዘመናዊ ስክሪን የተዘረጋለት አዲሱ ዙም ሲኒማ ቤት ከቅዳሜ ጥር 16 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ ስራ የሚጀምር ሲሆን ኢትዮጵያዊያን የፊልም ፕሮዲውሰሮችም በዚህ ሲኒማ ቤት ፊልማቸውን እንዲያሳዩ ጥሪ ቀርቧል፡፡

‹‹ጾመኛ ፍቅር›› በገበያ ላይ ዋለ



በገጣሚ ብሩክታዊት ጎሳዬ የተፃፈው ጾመኛ ፍቅር የተሰኘ የግጥም መድብል ጥር 7 ቀን ተመርቆ በገበያ ላይ ውሏልል፡፡ የመፅሐፉን ምረቃ በማስመልከት አዲስ ምዕራፍ ፕሮሞሽን በካፒታል ሆቴል አዳራሽ ባዘጋጀው ፕሮግራም ላይም በርካታ አንጋፋና ወጣት የሥፅሁፍ ባለሙያዎች የተለያዩ የግጥሞችና የሥፅሁፍ ሥራዎች ቀርበዋል፡፡ ጋዜጠኛ ደረጀ በላይነህ በመፅሐፉ ዙሪያ አጭር ቅኝት አቅርቧል፡፡ ከመፅሐፉ ውስጥ የተመረጡ ግጥሞች በዕለቱ ለተገኙት ታዳሚያን የቀረቡ ሲሆን ገጣሚዋ በሲዲ ያዘጋጀቻቸውን ግጥሞች በዕለቱ ለተገኙት ታዳሚያን አደርሣለች፡፡ በገጣሚ ብሩክታዊት ጎሣዬ የተፃፈው ጾመኛ ፍቅር የተሠኘው ይህ የግጥም መድብል ሠማንያ ገጾች ያሉትና 59 ያህል ግጥሞች የተካተቱበት ነው፡፡

ገጣሚ ብሩክታዊት ጎሣዬ በ1990 ዓ.ም በአዲስ አበባ መስተዳደር የተሠጠውን የአንድ ዓመት የስነ ፅሑፍ ስልጠና በከፍተኛ ውጤት በማጠናቀቅ በአንደኛ ደረጃ ተሸላሚ ነበረች፡፡ እንዲሁም በብሔራዊ ቴአትር፣ በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ፣ በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤትና በፑሽኪን አዳራሽ በሚዘጋጁ የሥነ ፅሑፍ ምሽቶ ላይ ግጥሞቿን በማቅረብ ትታወቃለች፡፡

ከኮካ ኮላ ዋጋ ደልቅ ጦር መሳሪያ በርካሽ የሚገኝባት ሀገር



መከከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ በእርስ በርስ ጦርነት መታመስ ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል፡ የሃገሪቱ ዜጎች ከመሞት መሰንበትን መርጠው በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩት በተለያዩ ሃገራት በስደት ተበታትነው ይገኛሉ፡፡

እ.ኤ.አ በ2013 ታጣቂ ቡድኖች የሀገሪቱን ቤተ መንግስት ከተቆጣጠሩ በኋላ የጦር መሳሪያ ድምጽ ሳይሰማ ውሎ አድሮ አያውቅም፡፡ ከሠሞኑ ሂዩማን ራይትስ ወች ባወጣው መረጃ መሠረት ወደ መካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ በርካታ ጦር መሳሪያ በህገወጥ መንገድ የሚገባ ሲሆን በተለይ ቻይና ሰራሽ የሆነው 82-2 የተባለ ፈንጅ በብዛት ይገኛል፡፡ በዚህች ሀገር ይህ አደገኛ ፈንጅ በ0.50 ዶላር እየተሸጠ ነው፡፡ ይህም አንድ ጠርሙስ ኮካ ኮላ ከሚሸጥበት ዋጋ ያነሰ ነው፡፡

በመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ በእርስ በርስ ጦርነት ሳቢያ ህጻናትና ሴቶችን ጨምሮ በርካታ ሠላማዊ ሠዎች ህይወታቸውን በማጣት ላይ ይገኛሉ፡፡

የጎዳናው ወግ

መንገድ ያደርሳል፤ መንገድ ይመልሳል ይሉት ወግ፤ መንገድ ማድረሱንም መመለሱንም የተቸገርንበት ጊዜ ላይ መድረሳችንን ስመለከት፤ መንገድ ላያደርስ አድክሞ፤ ላይመልስ አዝግሞ፤ አናውዞና ተስፋን ነጥቆ፤ የብሶት አደባባይነቱን በማን አለብኝነቱ መያያዙ ስወጋችን መነሻ፤ ለቁም ነገራችን ማዋዣ ሲሆን ቢያስገድደን፤ ይህንን ወግ ላቀብላችሁ በመንገድ ዳር አገኛለሁ...

(ክፍል 24)

ሀገሬ የኔ ተስፋ (ከሳፍቶ)

“የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ነገር...”
“የጣቢያዎቻችን ጉዳይም ቢታሰብበት...”

አንዳንድ ነገሮች ብዙ ይደንቁኛል...



ሰሞኑን በዓል አይደለ! “ገናና ጥምቀት እኩል ዓውድ ዓመት” እንዲሉ አባቶች፤መውሊድም ቢሆን ተከታትሎ የመጣ በዓል በመሆኑ፤አገሩ ሁሉ በዚህ የበዓል ስሜት ውስጥ ሆኖ ከወዳጅ ከዘመዱ ጋር ደስታውንና ፌሽታውን እየተጋራ ይገኛል። የነዳናው ወግም በኢትዮጵያ ባንዲራ ልዩ ህብር ሰርቶ ያሸበረቀውን መንገድ ፤በወጣቶች ጽዳት ውበቷን ያገኘችውን አዲስ አበባ እየተመለከተ፤ምናለ ሁልጊዜ ጥምቀት በሆነ ሲል ምኞቱን ሳይገልጽ አላለፈም። ያለው የወጣቶች የትብብር መንፈስ፤ለሃይማኖታቸው ያላቸው ቀናኢነት(አክራሪነት አለመሆኑ ልብ ይባል፤እዚህ ላይ ሰማያዊ ቲሸርት እንዳይለብሱ ተከልክለዋል የምትል አፈትልካ የወጣች መረጃ ግን አላነጋገረችም ማለት አይቻልም) ና ለአገራቸው ባንዲራ ያላቸውን ፍቅር(መንገዱን ሁሉ ከነጻነት በዓል በበለጠ በተቀጣጠለ ባንዲራ አንጠልጥለው አየሩን ሁሉ በአገራቸው ባንዲራ አሳምረውታልና) ስመለከት ምኞቴን ብመኝ ስህተት አይመስለኝም።

ታዲያ! በዚሁ የበዓል ሰሞን እኛም ከተደሳቾች አንደአንዱ የሆንን በመሆናችን ደስታችንን ከምንወዳቸውና ከሚወዱን ህዝቦች(ማን ነበር እንዲህ ያሉት?)ጋር እያሳለፍን እንገኛለን ። ዳሩ ምን ያደርጋል ! በበዓላችን ሰሞን እንኳን አልዘለን ያለው ተራችን(የመብራት መጥፋት ተራ ይኖር ይሆን እንዴ?) ብልጭ ድርግም እያለ ደስታችንን ሙሉ እንዳይሆን አልያም በሸራፋው እንድናከብር እየተገድድን ከረምን ። መቼስ ! ይሄ ችግር ለማን ይነገራል ። አላማርርም ነበር ያለው ያ ዘፋኝ ? ማለቴ የአሁኑ ዘማሪ! አዎ ፤ብናማርር ደግሞ የተራችን ጉዳይ የሁለት ሰፈሩን እኛ ሰፈር ይደርቡትና ጨለማ በጨለማ አያደርጉትም ለማለት አንችልም። ስለዚህም ያ ቻይናዊ አማርኛ ቋንቋ መናገር ችያለሁ ብሎ ለአገሩ ሰዎች ሲነግራቸው፤እስኪ አማርኛ ተናገር ቢሉት “መብራት መጣ፤መብራት ጠፋ “ብሎት እንዳረፈው ማለቴ ነው ።ምን ያድርግ እዚህ በቆየበት የአምስት ዓመት ቆይታው በህዝቡ ዘንድ በተደጋጋሚ የሰማው ይህንኑ ቃል ብቻ በመሆኑ ነው ። እናሳ! ካላችሁኝ እንደቻይናው “መብራት መጣ፤መብራት ሄደ“ እያልን እየተደሰትን ከመኖር ባለፈ አናማርርም።ተመስገን ብቻ ነው!።

ሌላ ተጨማሪ ወግ ልጨምር።ህጻናት ናቸው። በትምህርት ቤታቸው እንቆቅልሽ ትምህርት ሲማሩ ከቆዩ በኋላ አንዱ ህጻን፤”እንቆቅልሽ?” ይላል።”ምን አውቅልህ?” ሲሉት፤”ቢሄዱ ቢሄዱ የማይሰለቻቸው?”የሚል ጥያቄ ያቀርባል።ህጻናት የመሰላቸውን መልስ ሁሉ ይደረድሩለታል። በመጨረሻም መልሱን ስላልመለሱለት “እኔ እራሴ እመልስላችኋለሁ፤መብራትና ውሃ ናቸው” ብሎ አረፈው።ምን ያድርግ ፤ይህ ህጻን እቤት የሚሰማው ”መብራት ሄደች፤ውሃ ሄደች” ተብሎ በየቀኑ ሲነገር ነው፤ ወደ እንቆቅልሽ አስገብቶ በመሄድ የማይሰለቹ አድርጓቸው የአረፈው።ውሃ እንኳን እየሰለቸው ይመስላል።መብራት ግን መሄድ የማይሰለቸው ይመስላል።

በዚሁ የመብራት ችግር ምክንያት ብሶታችንን በዚያው በፈረደበት ጎዳናው ላይ ስናወጋ፤አንድ ለእናቱ የሆነውን የቴሌቪዥን ጣቢያችንን (ቲቪ ፣2፣3 እንዳትሉ ቅኝቱ አንድ ነው ለማለት ነው፤ያው ልማታዊና ባለቤቱም አንድ ነው በሚል ይያዝልን) ዜናና ወሬ እንኳን በአግባቡ ለመስማት ባለመቻላችን የመረጃ ልዩነት በመካከላችን ተፈጥሮአል።አንዳችን ስለአንድ ጉዳይ ስናወጋ ሌላኛው ደግሞ ይሄ መቼ ነው የተባለው ይላል፡ ፡አይ! መብራት ሃይል የመንግስታችንን ልማታዊ ዜና እንኳን በአግባቡ እንዳንሰማና እንዳንከታተል እንዲህ ከቴሌቪዥናችንን ታቆራርጠናለህ ስንል ሳናዝንበት አልቀረንም።ምን ያደርጋል ታዲያ!

እኛ የፈለግነውን ያህል ብንጨረጨር፤ፕሬዚዳንታችንም በይፋ ይቅርታ ቢጠይቁ፤የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ማስጠንቀቂያ ቢሰጡ ወንዱ ያባቢላ ልጅ ከነበረው ይበልጥ ቢያብሰው እንጂ መሻሻልን ሳያሳይ ይሄው ቀናትን፤ወራትን እንዲሁም ዓመታትን በድል እየተሸጋገርን ነው::

ከስራ የቆዩ እመቤት ናቸው አሉ፤ መኪናቸውን አቁመው ወደ ቤታቸው ሲገቡ መብራት የለም::መብራት ባለመኖሩ ምክንያት ደግሞ እራት አለመዘጋጀቱን ሰራተኛቸው አረዳቻቸው::አንድዬ ልጃቸው ደግሞ “እራት እያለ“ ቢያስቸግራቸው “መብራት ስለሌለ አራት›› የለም፤በመኪናዬ ነዳጅ ስለሌለ ደግሞ ሆቴል ልጋብዝህ አልችልም” ሲሉ የዜሮ ድምር የላቸውንም አረዱት::የሚገርመው እኮ መብራቱም የለ፤ነዳጁም በነዳጅ ባለቤቶች የለም::

በነዳጅ ማደያዎች አላቀርብም ባይነትና ነዳጁም በመጥፋቱ ነዳጅ ፍለጋ የሚኳትነውን ህዝብን አገር ይፍረደው::ተገኝም ከተባለ ያለው ሰልፍ እስከ ሁለትና ከዚያ በላይ በሚፈጅ ሰዓት ወረፋን መጠበቅ ሌላ ስራ እንዳይሰራ መሰናክል ሆኗል::ምክንያቱ ሲባል ለዘመናት ሲጨምር በቆየው የነዳጅ ዋጋ በወር መጨረሻ እያፈኑ የተጠቃሚነታቸውን ቁጥር ሲያሳድጉ የቆዩ ልማታዊ ያልሆኑ ባለማደያዎች፤የነዳጅ ዋጋ ሲቀንስ “ለምን እንቀንሳለን፤ለምንስ የአንድ ጉዞ ኪሳራ ይነካናል“ በማለት ነው ሲሉ አንዳንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች አልተናገሩም ማለት አይቻልም::ይቺ አንዳንድ የዚህ ከተማ ነዋሪዎች የምትለዋ ቋንቋ ብዙውን ጊዜ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና የመንግስት ሚዲያዎች በፍቅር የሚወዷት ገለጻ ናት::በተለይም የምርጫ ሰሞን አልያም የሆነ አጣብቂኝና መነገር አለበት ተብሎ የሚፈለግ ጉዳይ ሲኖር ከተደበቀችበት ትወጣና የፈረደባቸው በቀበሌ ሰዎችና በካድሬዎች አንደበት(የተጠና በሚመስልና የአንድ መልዕክት አስተላላፊ ሰዎች መሆናቸውን ቴሌቪዥን ተከታታይ ሁሉ የሚናገረው አባባል ነው) አንዳንድ የከተማዋ ነዋሪዎች ተብሎ መባል የሚፈለገው ይባልበታል::ሰሞኑን እንኳን እነዚህ ተቃዋሚዎች በራሳቸውም ይሁን በሌላ ወገን በተፈጠረ ችግር አለመግባባቶች እንዳሉ የመንግስት ሚዲያዎች “ከተፈጠረ 20 ዓመት የሞላው የግል ሚዲያ“ ከመቼውም ጊዜ በላይ በትጋት እያራገቡትና እየሰሩበት የሚገኝ ጉዳይ ነው፤ታዲያ አንዳንድ የከተማው ነዋሪዎች የተባሉ እነዚያ ሰዎች በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ አሉና ምርጫ ቦርዱን አመስግነው ፤ተቃዋሚዎችን ችግራቸውን እንዲፈቱ ሲለምኑ (ስለእነርሱ ተጨንቀው መሆኑ እኮ ነው !ኪ,ኪ,ኪ አሉ እማ ታንጉቴ) ታይተዋል::

ወደ ጉዳያችን ብንመለስ ሳይሻል አይቀርም ፤ወደዚህ ጉዳይ ከገባን መውጫ የለንም፤ጉዳያችንም ሌላ መልክ እንዳያስይዝብን ዝም ብንል ይሻላል::ስለነዳጁ ጉዳይ ግን ትንሽ እንበል::የነዳጅ ጉዳይ በአገራችን በየጊዜው በመጨመሩ ተጠቃሚው(ሸማቹ)የጉዳቱን ሸክም ሲሸከም መቆየቱ እውነት ነው::የፈለገውን ያህል ሲጨምር የቆየ የነዳጅ ዋጋ ቢቀንስ እንኳን በምግብና መጠጥ(ትኩስ መጠጥ) የዋጋ ቅናሽ አለማሳየቱ ሁሌም የሚገርመኝ ጉዳይ ነው :: ተከታትሎም የሚያስፈጽም አካል ስለሌለ እንደልባቸው በልዩነቱ መካከል ባለው ትርፍ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ከመጣር ባሻገር ደንበኞቻቸውን በቅናሹ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚፈልጉ ነጋዴዎች አላጋጠሙኝም:: ወደ ማደያዎች ስመለስ ከዚህ ቀደም በየወሩ መጨረሻ የዋጋ ጭማሬ ስለሚደረግ የመንግስታችን ከፍተኛ ሃላፊዎች ተወያይተውና ወስነው እንደወጡ በሚዲያ ሳይገለጽ መረጃው ይደርሳቸዋል::በዚህን ወቅት 45ሺ ሊትር የሚጭን ከየአይነቱ ከሦስት የማይበልጥ

“የፈለገውን ያህል ሲጨምር የቆየ የነዳጅ ዋጋ ቢቀንስ እንኳን በምግብና መጠጥ(ትኩስ መጠጥ)የዋጋ ቅነሽ ስለማሳየቱ ሁሌም የሚገርመኝ ጉዳይ ነው ::ተከታትሎም የሚያስፈጽም አካል ስለሌለ እንደልባቸው በልዩነቱ መካከል ባለው ትርፍ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ከመጣር ባሻገር ደንበኞቻቸውን በቅናሹ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚፈልጉ ነጋዴዎች አላጋጠሙኝም::

ተሽከርካሪ የሚያዝዙት ባለማደያዎች መረጃው እንደደረሳቸው የገንዘብ አቅማቸው የሚፈቅድላቸውን ያህል በብዛት በአሮጌው ዋጋ በርካታ ተሽከርካሪዎችን አሰማርተው ነዳጁን ገዝተው ይጠባበቃሉ::የአንድና ሁለት ብር ልዩነት ካለው በየተሸከርካሪው ላይ ከ90ሺ ብር በላይ ትርፍ በዚች የቀናት ልዩነት በሚፈጠር የመረጃ ቅብብሎሽ ብቻ ሲዝቁት ቆይተዋል::ይሄን የመሰለ የድብብቆሽ ስራ መስራታቸው ሳያንሳቸው ፤አንዳንድ ባለማደያዎች ቤንዚንና ነጭ ጋዝን በመቀላቀልም በቤንዚን ዋጋ እንደሚሸጡ ስራውን ጠንቅቀው የሚያውቁት ባልደረቦቼ አጫውተውኛል::የነጭ ጋዝ ዋጋ15 ብር ሲሆን ፤የቤንዚን ዋጋ 19 ብር በመሆኑ በመካከሉ ያለውን የ5 ብር ልዩነት በቤንዚን ዋጋ በመሸጥ ከፍተኛ ጥቅም እንደሚያግበሰብሱ ይታወቃል::ይሄ ሁሉ ባለበት ሁኔታ የነዳጅ ዋጋ በሚቀንስበት ወቅት የአንድ ጊዜን ጉዞ ዋጋ ለምን እንከስራለን በሚል አገራዊ ሃላፊነትን ያለመወጣት ችግር፤”ማሸን ተበላሽቶብኛል” የመሳሰሉ መሰናክሎችን በመደርደር ህዝቡ በነዳጅ እጦት ምክንያት እንዲጉላላ ያደርጋሉ::ይሄ ችግር በአግባቡ ሊፈተሽና የማያዳግም እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል:: እዚህ ላይ የመንግስታችን አቋም የዓለም ነዳጅ ዋጋ ሲቀንስ ፤ ማደያዎችም እንዲቀንሱ ማድረጉ አግባብነት ያለው ተግባር ቢሆንም ፤በዚህ መካከል በሚፈጠር ውጥረት የሚጎዳና በመሃሉም የሚጠቀም አካል ስለሚኖር ለሶስት ወራት ያህል ዋጋ ቢጨምርም ቢቀንስም ዋጋውን ተመሳሳይ አድርጎ፤ዋጋው ከቀነሰ የተገኘውን ገቢ ለአባይ ግድብ እንዲውል አድርጎ ዋጋውን ከምስቅልቅል ችግር ቢያረጋጋው መልካም ይመስለኛል::

ወደ መብራቱ ጉዳይ ስመለስ ፤ይሄ የመብራት ችግር ያልገባበት ስራና ቤት ይኖር ይሆን? ከፍ ብሎ የወይዘሮዋን አጋጣሚ አነሳን እንጂ፤ከግለሰብ ተጠቃሚዎች በላይ በተለያዩ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ችግሩ በበለጠ እያሳመማቸውና እየጎዳቸው መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ለአገልግሎት ስንሄድ በምሬት ሲገልጹት የምንሰማው ጉዳይ ሆኗል ::ከመብራት ጋር ስራቸው የተያያዙ ሁሉ ስራ ለመስራት በመቸገራቸው ከደንበኞቻቸው ጋር በወቅቱ ምርታቸውን ለማድረስ ባለመቻላቸው ከፍተኛ ጭቅጭቅና ከዚያም ሲያልፍ ኪሳራ እየደረሰባቸው እንደሚገኙ ይናገራሉ:: የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እጥረትና መቆራረጥ አሁንም ችግር ሆኖ ዘልቋል::

ከአነስተኞቹ ስራዎች እንኳን ብንነሳ ፤በጎዳና ላይ ድንች ችብስ ጠብሳ እራሷንና ቤተሰቧን የምታስተዳደር ሴት በመብራት ምክንያት የአንድ ቀንና የሁለት ቀን ገቢዋ ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮባታል፡ ፡ጸጉር አስተካካዩ፤የሴቶች የውበት ሳሎን፤የፎቶ ቤቶች፤ሌሎችም በርካታዎቹ የስራ መስኮች ካለመብራት ስራ መስራት ባለመቻላቸው የእለት ገቢን በማጣት፤ለኪራይ ግን የግድ ክፍያው የማይቀር በመሆኑ፤የግብር ጉዳይ ይህን ያህል ቀን መብራት ስላልነበረ ይሄን ያህል እቀንስልሃለሁ አይባሉምና እጅጉን እየተቸገሩ መሆናቸውን ይናገራሉ:: ጀኔሬተር ገዝተው እንዳይሞከሩት ገቢያቸው ወደዚህ የሚያንደረድር አቅም ስለሌለው መፍትሄውን በመፈለግ ላይ ይገኛሉ::ይሁን እንጂ ይኼ ነው የሚባል መፍትሔ ባለመኖሩ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ መወትወታቸውን አላቆሙም::

ወደ ትላልቆቹ ኢንዱስትሪዎች ስንመጣ የጉዳት መጠኑ ከፍተኛ ሆኖ እናገኘዋለን:: እኔ እንኳን የማውቃቸው የአንድ ቆዳ ፋብሪካ ባለቤት እንደተናገሩት በፋብሪካቸው በተደጋጋሚ የሚያጋጥመው የመብራት መጥፋትና መቆራረጥ በምርት ጥራታቸው ላይ ችግር እየፈጠረ እንደሚገኝ ይገልጻሉ::የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎትን ሲጠይቁ “ጠብቁ ይመጣል” የሚል መልስ ብቻ ያገኛሉ::እንዳሉት ግን መሻሻልም ሆነ ለውጥ አላገኙም ::መብራት የሚጠፋበት ወቅትና ቀን አስቀድሞ ቢነገራቸው ምናልባትም ቅድመ ጥንቃቄ በማድረግ ምርቶችን ከብልሽት መከላከል እንደሚቻል ይናገራሉ::የቆዳውን ለአብነት ያህል አነሳን እንጂ ፤ችግሩ ያልነካው አካል አለ ለማለት አንችልም :: ሌላው የብረት ፋብሪካ ባለቤትም በሚያጋጥማቸው የመብራት ችግር ምክንያት ምርቶችን በሚፈለገው

ወደገጽ 32 ዞሯል

የቀበጡ ዕለት ሞት ደገኛል?

የዓለማችን አደገኛ የቱሪስት መዳረሻዎች

ባለፈ ተረቱን እንገልብጠው፡፡ ‹የቀበጡ ዕለት ሞት ደገኛል› እንበል፡፡ ጀብድ ለመስራት ፈልገው ወደም ቀብጠው ከዚህ በታች ወደተዘረዘሩት የቱሪስት መዳረሻዎች ጎራ ካሉ ቤተሰቦችዎንና የሚያውቋቸውን ሠዎች ሁሉ ለመጨረሻ ጊዜ መሰናበትዎን እርግጠኛ መሆን አለብዎት፡፡ እዳዎን ይክፈሉ፤ ያበደሩት ካለም ይቀበሉ፡፡ ኑዛዜዎትን ይጻፉ፤ ምክንያቱም ወደ ነዚህ ቦታዎች ከሄዱ በኋላ በህይወት የመመለስ እድልዎ ጠባብ ሲሆን ይችላል፡፡

ፍስሐ ገትነት

ዮሴሚቴ ብሔራዊ ፓርክ



መገኛው አሜሪካ ውስጥ ነው፡፡ ዮሴሚቴ ፓርክ የተከለለው እ.ኤ.አ በ1964 ሲሆን በውስጡ ባለው ፏፏቴና በተራራው ይታወቃል፡

፡ በቅርብ ጊዜ ወደ ስፍራው ካቀኑ ሰዎች መካከል 60 የሚሆኑት ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ አብዛኞቹ ለሞት የተዳረጉት ሃፍዶሜ የተሰኘውን አደገኛ ተራራ ለመውጣት ሲሞክሩ ነው፡፡ ከተራራው ተምዘግዝገው ቁልቁል 180 ሜትር ላይ ይወድቃሉ፡፡ ተራራው አናት ላይ በሠላም የሚደርሱት ጥቂት ዕድለኞች ብቻ ናቸው፡
፡

ሌላኛው አስገራሚ ነገር ዮሴሚቴ ፓርክ ውስጥ በጠራራ ፀሀይ ሳይታሰብ ከሠማይ የሚወርደው መብረቅ ነው፡፡ የፓርኩ ነፍስ አድን ሠራተኞች የሞቱና የተጎዱ ሰዎችን በመሰብሰብ ስራ የተጠመዱ ናቸው፡፡

አልንዊክ የአትክልት ስፍራ

እንግሊዝ ውስጥ .አልንዊክ በተባለች ከተማ



ይገኛል፡፡ የኖርተምበርላንድ 3ኛው ጉዑስ የነበረው ሃግ ፐርሲ አትክልቶችን መሰብሰብና መትከል የሚወድ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው አልንዊክ በተባለው የጉዑሳዊያኑ የአትክልት ስፍራ ላይ ከመላው አለም የተለያዩ ተክሎችን እያስመጣ ያስተክል ነበር፡፡ ንጉሡ ካስተከላቸው ተክሎች መካከል አብዛኞቹ በጣም መርዘኛ የሆኑና በፍጥነት የሚገድሉ ናቸው፡



እንኳን ደስ አላችሁ!

የ30ኛ ዓመት የጋብቻ በዓላችሁን ጥር 14 ቀን 2007 ዓ.ም በደመቀ ሁኔታ ላከበራችሁት

አቶ ተሾመ ግርማ

እና

የመቶ አለቃ አልማዝ ይማም

እንኳን ደስ ያላችሁ!

መልካም የትዳር ዘመን!!

ጓደኞችሁ አማረ ሐይሉ

፡ ይህ ቦታ አሁንም አልንዊከ ከተማ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በተለያዩ የማስጠንቀቂያ መልዕክቶች የተከበበ ነው፡፡

ወደ ተከሎቹ የሚጠጋ ሰው በእጁ ባይነካቸው እንኳ በሽታቸው ብቻ ይገድሉታል፡፡ በዚህም ምክንያት ወደ ስፍራው የሚያቀኑ ጎብኚዎች በርቀት ይቆሙ ዘንድ ግድ ነው፡፡

አካፑልኮ



እርግጥ ነው፡፡ አካፑልኮ ተወዳጅ ከተማና አዝናኝ በሆኑ የተፈጥሮ ስጦታዎች የታደለች ናት፡ በባህር ዳርቻዎቿ እየተንሸራሸሩ ፀሀይዋ ስትገባ መመለከት ነፍስን በሃሴት ይሞላል፡፡ ግን ከዚያ ስሜት ገና ሳይወጡ ከየት እንደተተኮሰ ያላወቁት ጥይት በአጠገብዎ ያለውን ሰው ጭንቅላት ሲበድሠው ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡ አያድርግብዎትና የዚያ ዕጣ ፋንታ ባለቤት እርስዎም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ምክያቱም በሜክሲኮዋ ከተማ አካፑልኮ መሳሪያ የታጠቁ በርካታ ወንጀለኞች ተሰማስገዋል፡፡ ያለዎን ንብረት ከመውሰዳቸው በፊት ነፍስዎን የሚነጥቁ አረመኔ ናቸው፡፡ በአካፑልኮ ከ100 ሺህ ሰዎች መካከል 142 የሚሆኑት በወንጀለኞች ይገደላሉ፡፡ አብዛኞቹ ደግሞ ቱሪስቶች ናቸው፡፡

የሞሄር ኮረብታዎች



አየርላንድ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ለሚመለከታቸው ሰው አስደሳችና ትንፋሽን ቀጥ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በቪዲዮ የተቀረጸውን ምስል ሲመለከቱ በአለማችን ላይ እንዲህ የሚያምር ቦታ አለ እንዴ ብለው ለመጎብኘት ልብዎ ይነሳሳል፡፡ በስፍራው ከደረሡ በኋላ ግን አደገኛ ነገር ይጠብቅዎታል፡፡ ኮረብታዎቹ ላይ ከወጡ በኋላ ድንገት ከየት መጣ ያልተባለ ሃይለኛና ፈጣን ነፋስ ወደሞት ይዞዎት ሊሄድ ይችላል፡፡ በየዓመቱ በርካታ ሰዎች ከኮረብታዎቹ ቁልቁል ወደ መሬት በነፋስ ተገፍተው እየወደቁ ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡

ኮኮዳ



የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ታሪክ የማወቅ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በብዛት ወደዚህ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ ፓፓኒው ጊኒ ውስጥ የሚገኘው ኮኮዳ የተባለው ደን የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ከተካሄደባቸው ቦታዎች አንዱ ነው፡ ፡ የአውስትራሊያና የጃፓን ወታደሮች በዚህ ስፍራ ተጨፋጭፈዋል፡፡ በአደገኛ የዱር አንስሳት በተሞላው በዚህ ስፍራ ለረዥም ዘመናት የኖሩ ጎሳዎች አሉ፡፡ ጎሳዎቹ በተደጋጋሚ በቱሪስቶች ላይ ጥቃት ያደርሳሉ፡፡ በርካታ ቱሪስቶች በሰይፍ አንገታቸው ተቀልቶ ሞተው ተገኝተዋል፡፡ በወባ በሽታና በዱር አንስሳት ጥቃት ደርሶባቸው ህይወታቸውን የሚያጡም አሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ ስፍራ በአለማችን እጅግ አደገኛ የቱሪስት መዳረሻ ተብሎ ተፈርጇል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስፔኑ ካሚኒቶ ዴል ሬይ፣ የኮሎራዶ ወንዝ፣ የብራዚሉ ቦአቪንም የባህር ዳርቻ፣ ስታር ዋር ፊልም የተቀረጸበት ስኬሊንግ ሚካኤልና የሃዋዩ እሳተ ጎመራ ስፍራ ለቱሪስቶች የማይመከሩ አደገኛ ቦታዎች ናቸው፡፡

አስቴር...

ከገጽ 9 የዞረ

የጠየቅሁት እንጂ ‹አንድ ሰው ተነስቶ እኔ ንጉስ ነኝ› ቢለኝ ሺ ዓመት ንገስ ነው የምለው› አልኩት፡፡ይሄ ግን የብዙዎቹን አስተሳሰብ የሚወክል አስተያየት እንዳልሆነ ይገባኛል፡፡ በነገራችን ላይ እኔ የተለየ ነገር ፈጥሬ የተናገርኩ ሰው አይደለሁም፡፡ የተሰማኝን ነው የተናገርኩት፡፡እውነት ነው ብዬ የያዝኩት ነገር ካለ በድፍረት እናገራለሁ፡፡

ቁም ነገር፡- በየማህበራዊ ድረ ገፅች ላይ ስላንቺ እየተባሉ ያሉትን ነገሮች ተመልክተሻቸዋል?

አስቴር፡- እኔ ብዙ የፌስ ቡክ ተጠቃሚ አይደለሁም፡፡ በሳምንት አንድና ሁለት ጊዜ ባይ ነው፡፡ ለምሳሌ የእኔን ፎቶና የባለስልጣናትን ፎቶ አድርገው ስድብ በመፃፍ የሚያሰራጩ አሉ፤ ይሄ ትክክል አይደልም፤ የእኔ አላማ መሳደብ አይደለም፤ በመሳደብም ሆነ የሰውን ክብር በመንካት የሚመጣ ለውጥ አለ ብዬ አላምንም፡፡ እነዚህ ሰዎች እኮ ከፋም ለማም ሀገራቱን እያስተዳደሩ ያሉ ሰዎች ናቸው፤ ያለፉበትንም የትግል ሂደት ሄደን ተመልከተናል፡ ፡ የሚካድ አይደለም፡፡ ያሉትን ጠንካራ ጎኖች አጠንክሮ ችግሮቹንም መንገር ነው የሚያስፈልገው፡ ፡እኔ በአሁኑ ወቅት ጊዜ የለኝም፤ ብዙ ስራ አለኝ፤ አራት መፅሐፍ ላሳትም ያዘጋጀኋቸው አሉ፤ አንድ ግጥም ሲዲ ጨርሻለሁ፤ የቤተሰብ ሀላፊ ነኝ፡፡ የልጆች እናት ነኝ፡፡ ፌስቡክ በሚሰጠው አፍራሽ አስተያየት ላይ ምንም ልል አልችልም፤ አልሞቀኝም አልበረደኝም፡፡ ከዚህ ይልቅ ፊልም ሰርቼ ብታወቅ ነው የምመርጠው፡፡ የሚገርምህ ቤተመንግስት ሁሉ ተጠራች ብለው የሚያወሩ አሉ፡፡

ቁም ነገር፡- ጉዳዩ ከፖለቲካ ጋር መያያዙ አስጨንቆሻል?

አስቴር፡- ለምን ያስጨንቀኛል? የፖለቲካ ጥያቄ ስትጠይቅ ጉዳዩ ወደ ፖለቲካ እንደሚሄድ እገምታለሁ፡፡ግን እኔ የጠየቅሁት ጥያቄ ካየሁት ከሰማሁት፤ሰው ከሚያወራው ተነስቼ በመሆኑ ያን ያህል አነጋጋሪ መሆኑ አስገርሞኛል፡፡

ቁምነገር፡- አስቴር ፖለቲከኛ ናት?

አስቴር፡-አይደለሁም፤

ቁምነገር፡-ፖለቲካ ትወጃለሽ?

አስቴር፡- ማለት.. የሚያናድዱኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ በዚያ በኩል ያለውን ሁኔታ ለማወቅ የምቆፍር አይነት ሰው ነኝ፡፡ ግን የፖለቲካ ጋዜጣና መፅሔት የምከታተል ሰው አይደለሁም፡፡ እርግጥ ነው በሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል ባይ ሰው ነኝ ፡፡

ቁምነገር፡- አርቲስት ከፖለቲካ ነፃ መሆን ይችላል ብለሽ ታስቢያለሽ?

አስቴር፡- አርቲስት ፖለቲከኛ ሳይሆን መስታወት ነው፡፡ መስታወት ደግሞ ያለውን ነገር በግልፅ ነው የሚያሳየው ብዬ ነው የማምነው፡፡

ቁም ነገር፡- በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያስችው አስቴር ምን አይነት ሴት ናት?

አስቴር፡- አስቴር በጣም ቆንጆ፤ በንጉሱ ፊት ሞገስ ያገኘች፤ ለህዝቧ ምህረትን ያመጣች ብልህ ሴት ናት፡፡እናትም አባትም ሆኖ መርዶኪዮስ ነው ያሳደጋት፡፡መርዶኪዮስ ከህንድ እስከ ኢትዮጵያ ነበር የሚያስተዳድርው፡፡ ንጉሱ ሲያገባት አይሁዳዊ መሆኗን አያውቅም፡፡ መርዶኪዮስ ሐማ ለሚባለው የንጉሱ ባለሟል አልሰግድም በማለቱ እንዲገደል ይወሰናል፡፡ እሱ ብቻ ሳይሆን መላ ዘሩ ሁሉ እንዲጠፋ ይፈረድበታል፡፡ ይህን ጊዜ መርዶኪዮስ አስቴርን በዚህ ጊዜ ህዝብሽን ማዳን አለብሽ ይላታል፡፡ንጉሱ ብዙ ሚስቶች ስላሉት የሚፈልጋትን ካላስጠራ በቀር እሱ ጋር መቅረብ አይቻልም፡፡ አስቴር ግን ህዝቡ ለሶስት ቀን ፆም ፀሎት ይያዝ አለች፤ ከሶስት ቀን በኋላ ንጉሱ ሳያስጠራት ቢገድለኝም ይግደለኝ ብላ ንጉሱ ፊት ሄዳ ቆመች፡፡ ንጉሱ ዘንጉን ከዘረጋላት አለፈች ማለት ነው፤ ዝም ካለ ግን ያው ትገደል ነበር፡፡ ግን አስቴር በንጉሱ ፊት ሞገስ አገኘች፡፡ ምንድነው የምትፈልጊው? ሲላት ስለህዝቧ ተናገረች ፤ ስለህዝቧ የተጻፈው የሞት ደብዳቤ ለጠላቶቿ ሆነ፤ህዝቧንም አዳነች ማለት ነው፡፡ በጣም ነው አስቴርን የምወዳት፤

ቁም ነገር፡- በመጨረሻስ?

ቁም ነገር፡-ለሁሉም አስተያየት ለሰጡኝ ሰዎች ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ አድናቆታቸውን ለሰጡን ብቻ ሳይሆን ለተቹኝም ለሰደቡኝም አመሰግናለሁ፡፡ ምክንያቱም ሰው ሁልጊዜ የሚናገረው በአዕምሮውና በአስተሳሰቡ በእውቀቱ ደረጃ ነው፡፡ ሁሉም ሰው እንደእኔ ያስብ ለማለት አይቻልም፡፡የተነገረውን ነገር የምትቀበልበት ልብ ነው አንተን የሚገልፅህ፡፡ ቀና አስተሳሰብ እንዲኖረን ነው የምፈልገው፡፡አንድ የሚያደርገን ነገር ላይ ብናተኩር ነው ደስ የሚለኝ፡ ፡ በፖለቲካ ልዩነት ሳቢያ እንደ ጠላት ባንተያይ እላለሁ፡፡ፖለቲከኝነትና እንጀራም ቢለያይ ጥሩ ነው፡ ፡ እኔ ለማንም ጥላቻ የለኝም፤ ማንንም አልቃወምም፡ ፡ሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ያለችውን ኢትዮጵያ እንፍጠራት ነው የምለው፡፡ እየተፈራራን የትም አንደርስም፡፡የመሪዎቻችንን ልብ በፍቅር መማረክ ይቻላል፤ፈሪ ህዝብ ለምንም አይጠቅምም ፡፡ መንግስትም ፈሪ ህዝብ ይዞ ልማቱን መቀጠል አይችልም፡፡ ከዚህ ፍርሃት እንደ ህዝብ ተላቀን በፍቅርና በሰላም ለሀገር ይጠቅማል የምንለውን አሳብ እየሰጠን እንድንኖር ነው የምምኘው፡፡

ቁም ነገር፡- አመሰግናለሁ፡፡

ዶ/ር ዘውዱ...

ከገጽ 13 የዞረ

በዲኤንኤ ምርምራ የተረጋጠላቸው ሰዎችም ምን ማድረግ እንዳለባቸው በዘርፉ ስፔሻይዝድ ወዳደረገ ሀኪም እንልካቸዋል፡፡በሌላ መልኩ ብዙ ጊዜ የሚወለዱት ህፃናት ጤናማ ናቸው፡ ፡ አልፎ አልፎ ግን ወላጆች ችግር ያለባቸው የተለየ ባህሪ የሚያሳዩ ህፃናትን ሊወልዱ ይችላሉ፡፡ የዛን ጊዜ መጥተው ምርመራ በማድረግ ያ የታየው ችግር በትክክል መኖሩን ማየት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ከተወለዱት ልጆች መሀከል አንዱ የአዕምሮ ዘገምተኛ ወይም ጡንቻዎቹ ያልጠነከሩ ሊሆኑ ይችላል፡፡ እነዚህን በአይን አይቶ ብቻ ላይታወቅ ይችላል፡፡ በዲኤንኤው ላይ በሚደረግ ምርመራ ግን ቤተሰብ እውነታውን እንዲያውቅና የአማራጭ ህክምና ለመጀመር ይቻላል፡፡ የተለመደው ነገር ግን ከቤተሰብ ውስጥ አንዱ ልጅ ብቻ የዚህ አይነት የተለየ ባህሪ ሲያሳይ ከተለያዩ ባዕድ ምልኮ ጋር በማያያዝ ጉዳዩን በሌላ መልኩ ለመፍታት ይሞከራል፤ ይህ ከሚሆን ይልቅ ግን ምርመራ በማድረግ ነው መፍታት የሚቻለው፡፡

ቁም ነገር፡- በዚህ ማዕከል ውስጥ የሚሰጡት ምርመራዎች ምን ምን ናቸው?

ዶ/ር ዘውዱ፡- ለምሳሌ በሂሞግሎቢን አይነት በመቀየር የተነሳ የሚመጣን የደም ማነስ ማወቅ ይቻላል፡፡ ደማቸው በቆሰሉ ሰዓት ቶሎ የማቆምላቸው ሰዎች አሉ፤ እነዚህ ሰዎች የጂን ችግር እንዳለ በቤተሰባቸው ውስጥ ማወቅ ይቻላል፡ ፡ የደም ካንሰርን ሉኬሚያን ማወቅ ይቻላል፡፡ ከዚህ በፊት የአዕምሮ ዝግመት ያለበት ልጅ የወለዱ ወላጆች ቀጣዩ ልጃችን እንደዚህ ይሆናል ወይ? የሚለውን ለማወቅ የሚፈልጉ ወላጆች በምርመራ ሁኔታውን ማወቅ ይቻላል፡፡ከዚያም ከማህፀን ሀኪም ጋር እንዲገናኙና ሰፋ ያለ ህክምና እንዲያደርጉ ለማድረግ ይቻላል፡፡ የማህፀን ሀኪሞች ናሙና ከወላጆች ላይ በመውሰድም የሚልኩልንን በመመርመር በዚህኛው ልጅ ላይ ችግሩ ሊኖር ይችላል ወይስ አይችልም የሚለውን ለማወቅ ይረዳል፡፡

ቁም ነገር፡- ወላጆች በዘራቸው ችግር እንዳሰባቸው የሚታወቅ ከሆነ ልጅ እንዳይወልዱ ለማድረግ ይቻላል?

ዶ/ር ዘውዱ፡-እርግዝና በመሰረቱ በአጋጣሚ የሚከወን ነው፡፡ ሁሉም ሴቶች በአንድ ጊዜ አያረግዙም፡፡ ያም ሆኖ ግን በዘር የሚወረስ ችግር በጂን ዲፌክቲቭ የሆኑ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ችግሩ በሁለቱንም ወገኖች በኩል ሊኖር ይችላል፡፡ እንዲህ አይነት ሰዎችን እንዳይጋቡ መከልከል ያስቸግራል፤ ነገር ግን ልጅ እንዳይወልዱ መምከር ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም በዘራቸው የወረሱት የጂን ችግር ስላለ በሚወልጁት ልጅ ላይ ወይ ሙሉ ለሙሉ ወይ በግማሹ ወይም ከዚያ ባነሰ የጤና ችግር ይዘው ሊወለዱ ይችላል፡፡ ያ የጤና ችግር ብዙ ሳይቆዩ ሊገላቸው ይችላል፡፡ ወይ ደግሞ ከነችግሩ ለተወሰነ ዓመት ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ያ ደግሞ በመላጆች ስነ ልቦና ላይ ከባድ ችግር ያስከትላል፡ ፡ከስነ ልቦናው ችግሩ በተጨማሪም የህክምና ወጪ ጉዳይ የአንድን ቤተሰብ ሰላም የሚያናጋበት አጋጥሚ ብዙ ነው፡፡ ለምሳሌ ከአርባ ዓመታት በኋላ የሚከሰቱ በሽታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡ ፡ እነዚህ አይነት ነገሮች በፊት ለፊት የሚታዩ ሳይሆኑ በዲኤንኤ ምርመራ ብቻ የሚታወቁ በመሆኑ አስቀድሞ ምክር ማግኘት ይቻላል፡፡ለምሳሌ ሀቲንተን ዲዚዝ የሚባል በሽታ አለ፡ ፡ ብዙ ጊዜ የሚታየው አርባ ዓመት ባለፋቸው ሰዎች ላይ ነው፡፡ ከአዕምሮ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ግለሰቡ ይህንን በሽታ ለልጅ ልጆቹ ያስተላልፋል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ቤተሰብ የቤተሰቡን ታሪክ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ እንደውም የቤተሰብን ታሪክ መዝግቦ የመያዝ ልምድ ሊዳብር ይገባል፡፡

ቁም ነገር፡- አሁን ይህንን ምርመራ የምትሰሩበትን መሳሪያዎች በጣም ዘመናዊ ናቸው፤ ከዛው ከሆላንድ የመጡ ናቸው?

ዶ/ር ዘውዱ፡- ሁሉም ለማለት በሚቻል መልኩ የመጡት ከሆላንድ ነው፡፡ የተወሰኑትን እዛው ሆላንድ የነበርኩ ጊዜ ስንጠቀምባቸው የነበሩ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹን ግን አዲስ ተገዝተው የመጡ ናቸው፡፡እዚህ ሀገር ቴክኖሎጂውም ስለማይታወቅ አዲሶች ናቸው፡፡

ቁም ነገር፡- ቀደም ሲል ከፕሮስ ሳሙና ጋር በተያያዘ ጥናት ማድረግዎን ጠቅሰውልኝ ነበር ምንድነው?

ዶ/ር ዘውዱ፡- አመስተርዳም ዩኒቨርሲቲ የጥርስ ህክምና ፋካሊቲ ውስጥ በምሰራበት ጊዜ አንድ ምርምር አድርጌ ነበር፡፡ አፍ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ባክቴሪያዎች አሉ፡፡ በላብራቶሪ በማሳደግ ከሚታወቁት ውጪ በማሳደግም የማይታወቁ ነገር ግን በአፍ ውስጥ መኖራቸው የሚታወቁ ባክቴሪያዎችን አሉ፡ ፡ እነዚህን መኖራቸውን በዲኤንኤ ምርመራ ማወቅ የሚቻልበት መንገድ አለ፡፡ ከ500 በላይ የሚሆኑ የባክቴሪያ አፋችን ውስጥ አሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ለጤና ጎጂ አይደሉም፡፡ ነገር ግን የተወሰኑት ከምንመገባቸው ምግቦች ውስጥ ስኳሩን ወስደው አብላልተው አሲድ የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡፡ የሚፈጥሩት አሲድ ደግሞ ኢናሜል የሚባለውን ነጩን የጥርሳችንን ክፍል ይበሉታል፡፡ አፕላይ ማይክሮ ባዮሎጂ የተባለው የምርምር መፅሔት ላይ የታተመው የኔ ምርምር ውጤት በአፍ ውስጥ ያለውን ምራቅ ዲኤንኤ በመመርመር ወደ 50 የሚሆኑ ባክቴሪያዎችን መኖራቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ መኖራቸውን ብቻ ሳይሆን ቁጥራቸውስ ምን ያህል ነው? የሚለውን የሚያረጋግጥ ነው፡ ፡ ይህ የምርምር ውጤት በመፅሔቱ ላይ ታትሞ ሲወጣ የኮልጌት የጥርስ ሳሙና አምራች ካምፖኒ ሳይኒቲስቶች መጥተው እኛም ይህንን የምርምር ውጤት ልንጠቀምበት እንፈልጋለን አሉና ፋካሊቲውን ጠየቁ፤ የምርምሩም ባለቤት አሰልጣኙም እኔ ስለሆንኩ ወደ አሜሪካ ሄጄ ኒውጀርሲ ስቴት ውስጥ ትልቅ የምርምር ምዕከል አላቸው ስልጠናውን ለነሱ ሰጥቼ ነው ወደ ጀኔቲክስ ምርምር እንደገና ፊቴን ያዞርኩት፡፡እንግዲህ እነሱ በሚያመርቱት ኮልጌት ውስጥ እነዛን ባክቴሪያዎችን ሊያጠፋ የሚችለውን ኬሚካል በምን ያህል መጠን ነው መጨመር ያለብን የሚለውን እንያውቁ ያግዛቸዋል ማለት ነው፡፡

ቁም ነገር፡- ምን ያህል ጊዜ ሆነው ክሊኒኩ ከተከፈተ?

ዶ/ር ዘውዱ፡- አሁን ወደ ስምንት ወር ሆኖታል ክሊኒኩ ከተከፈተ፤

ቁም ነገር፡- አንድ ሰው የዲኤንኤ ምርመራ ስማድረግ ምን ያህል ጊዜ ደመስድበታል?

ዶ/ር ዘውዱ፡- በአብዛኛውን ሁለት ሳምንት ይስዳል፤ ነገር ግን እንደ በሽታው አይነት ይለያያ፤ ለምሳሌ የምንወስደው ናሙና ብዙ ጂኖችን ብዙ ክሮሞዞሞችን የሚይዝ ከሆነ ሊቆይ ይችላል፡፡እንደገና ተጨማሪ ማረጋገጫ የሚፈለግ ከሆነ ወደ ሆላንድ ልከን ተጨማሪ ማረጋገጫ እናገኛለን፡፡

ቁም ነገር፡- በጄኔቲክ መዛባት ወይም ዲፌክት የተነሳ የሚመጡ የጤና ችግሮች ላይ በሀገራችን የጀመራችሁት አዲስ ስራ ምንድነው?

ዶ/ር ዘውዱ፡- ከጳውሎስ ሆስፒታል ሀኪኮሞች ጋር በመሆን አንድ የጀመርነው ነገር አለ፡፡ ይህውም የጂኔቲክ ችግር ኖሮባቸው የሚወለዱ ህፃናት ምዝገባ ያስፈልጋል በሚል ለመጀመር እንቅስቃሴ እያደረግን ነው፡፡ይህ ምዝገባ መኖሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የትኛው አይነት የጂኔቲክስ ችግር ነው በብዛት የሚታየው የሚለውን በቀላሉ ለማወቅ ይቻላል፡፡ የትኛው ክልልስ ነው በዝቶ የሚታየው የሚለውንና ለዚህ ህመም የሚሆነውን መድሃኒት ወደየት ነው በብዛት መላክ ያለብን የሚለውን ለማወቅ ይረዳል፡ ፡ የዲኤንኤ ምርመራ ለሁሉም ህመሞች ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ በመሆኑ የሀገሪቱ የጤና መረጃ በሂደት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ይያዛል ብለን እንጠብቃለን፡፡

ቁም ነገር፡- አመሰግናለሁ፡፡



አራቱ ሻማዎች

እስክንድር ከበደ



የፈረንጅ ወግ ናት ፡፡ እንዲህ በማለት ትጀምራለች “በአንድ ቤት ውስጥ አራት ሻማዎች አብርተው ይታዩ ነበሩ፡፡ “ እነዚህ አራት ሻማዎች በሹክሹክታ ይጨዋወታሉ፡፡

አንደኛው እንዲህ አለ” እኔ ሰላም(PEACE) ነኝ ማንም ግን እንዳበራ የሚፈልግ የለም፡፡ስለዚህ መሄድ አለብኝ “ ወዲያው ነበልባሉ ቀንሶ ሙሉ ለሙሉ ጠፋ፡፡

ሁለተኛው ሻማ “ እኔ እምነት(FAITH) ነኝ ፡፡አብዛኛው ጊዜ እታመማለሁ፡፡ከእንግዲህ ወዲህ አላስፈልግም ፡፡ በመሆኑም እየበራሁ መቆየቴ ዋጋ የለውም ፡፡” ይህን እንደተናገረ ወዲያው ንፋስ ነፍሶ ጠፋ፡፡

በተራው ሶስተኛው ሻማ በሀዘን ይናገራል፡ : “እኔ ፍቅር(LOVE) ነኝ፡፡በርቼ ለመቆየት ብርታቱ የለኝም፡፡ሰዎች እኔን ጠቀሜታ ወደ ጎን ብለውታል፡ : አጠገባቸው ያሉትን መውደድ ዘንግተውታል፡፡” ብሎ ይጠፋል፡፡

ወዲያው አንድ ልጅ ወደ ቤት ሲገባ ሶስቱ ሻማዎች ጠፍተው ተመለከተ፡፡” ለምን አልበራችሁም ...እስከመጨረሻው መብራት ይጠበቅባችኃል!”አለ፡፡

ይህን ብሎ ልጁ ማልቀስ ጀመረ፡፡ይህን ጊዜ አራተኛው ሻማ “ አይዞህ እኔ እየበራሁ እስካለሁ ድረስ ሌሎቹን ሻማዎች ደግመን ማቀጣጠል እንችላለን ፡፡ እኔ ተስፋ(HOPE) ነኝ፡፡

ልጁ አይኖቹ ብሩህ ሆነው በደስታ ፊቱ ተሞላ፡፡የተስፋ ሻማውን አንስቶ ሌሎቹን ሶስቱን ሻማዎች አቀጣጠላቸው(አበራቸው)፡፡

የተስፋ ነበልባል በጭራሽ ከህይወታችን ውስጥ መጥፋት የለበትም፡፡ እንዲህ ሲሆን እያንዳንዳችን ተስፋን(HOPE) ፣እምነትን(FAITH) ሰላምን (PEACE) እና ፍቅርን(LOVE) ማቆየት እንችላለን፡፡

በቅርብ ቀን

“ሶስት ማዕዘን” በሎስ አንጀለስ ፊልም ፌስቲቫል ሊታይ ነው



በአሜሪካ ሎስአንጀለስ ከጥር 28 እስከ የካቲት 9 ቀን 2007 ዓ.ም የሚካሄደው የፓን አፍሪካን ፊልም ፌስቲቫል ላይ የአርቲስት ቴዎድሮስ ተሾመ ስራ የሆነው ‹ሶስት መአዘን› ፊልም እንደሚታይ ተገለፀ፡፡

በፌስቲቫሉ ላይ ከተመረጡት 200 ፊልሞች በአምስት ዘርፍ ለተዘጋጀው ሽልማት ከየዘርፉ አምስት አምስት ፊልሞች እንደሚመረጡ ሲሆን በመክፈሉ ቻቸው፣ በፌስቲቫሉ መሃልና በመዝጊያው ስነ-ስርዓት ላይ ለመታየት የተመረጡ ፊልሞች በአምስቱም ዘርፍ ውስጥ ለመመረጥ ከፍተኛ እድል እንዳላቸው ታውቋል፡፡

አርቲስት ቴዎድሮስ፤ “ሶስት ማዕዘን” ፊልም ለዚህ መብቃቱ ለሀገራችን ፊልሞች እንደ ፋና ወጊ የሚታይ እንደሆነ ገልጿ በፌስቲቫሉ ከአምስቱም ዘርፍ ተመርጠው ለሚያሸንፉ ፊልሞች አምስት ትልልቅ ሽልማቶች የተዘጋጁ ሲሆን “ሶስት ማዕዘን” ፊልም በአምስቱ ዘርፎች ውስጥ በዳኞች የመመረጥ እድል ካጋጠመው ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ጭምር ኩራት መሆኑን ለቁም ነገር መፅሔት አስረድቷል፡፡

በፌስቲቫሉ ላይ በአፍሪካውያንና በአፍሪካ አሜሪካውያን የፊልም ባለሙያዎች የተሰሩ የተመረጡ ፊልሞች ለዕይታ የሚበቁ ሲሆን፣ የፓናል ውይይቶችና የተለያዩ ስነጥበባዊ ዝግጅቶችም የሚከናወኑ ሲሆን ለዚሁ ፊስቲቫል በፊልሙ ላይ የሰሩ አምስት መሪ አርቲስቶች ወደ ስፍራው እንደሚያመሩ አርቲስት ቴዎድሮስ ተናግሯል፡፡



እግዚአብሔር ደመስገን ደህና ነን!!

ሚሬ

ሰውየው ለረዥም ጊዜ ባሕር ማዶ ቆይቶ ወደ ሃገሩ እየተመለሰ ያለ ወዳጁን ሊቀበል ቦሌ አየር ማረፊያ ይሄዳል፡፡ እንግዳውም በሰላም ደረሰና ተገናኙ፡፡ ከብዙ ሰላምታ መለዋወጥ በኋላ እንግዳው ከቤተሰቦቹ ጋር እስኪቀላቀል አላስችል ስላለው በመንገዳቸው ላይ ስለ ወዳጅ ዘመድ፣ ስለ ጋራ ሸንተረሩ ደህንነት ይጠይቀዋል፡፡ ተቀባይም ሁሉ ሰላም ሁሉ በጎ መሆኑን ይነግረዋል፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ እንግዳው መልሶ

እንግዳ፡- “የኔም ያንተም ቤተሰብ ሁሉም ሰላም ነው አልከኝ?”

ተቀባይ፡- “አዎ ፈጣሪ ይመስገን ሁሉም ደህና ናቸው፡ :”

እንግዳ፡- “እኔ ካገር ከወጣሁ በኋላ ምንም የተፈጠረ አዲስ ነገር የለም?”

ተቀባይ፡- “አረ ሁሉም አንተ እንዳለህ እንደነበረው ሰላም ብቻ ነው፡፡”

እንግዳ፡- “ከሆነ መልካም....ብዙ ጊዜ ወጥቼ ስለቆየሁ ብዙ አዲስ ነገር እንደሚኖር ጠብቄ ነበር”

ተቀባይ፡- “አይ ምንም አዲስ ነገር የለም....እንደው ብቻ ያቺ የምንወዳት አንዲት ድመት ሞተች እንጂ ሁላችንም በጣም ሰላም ነን፡፡”

እንግዳ፡- ሳቅ እያለ “ምን ሆና ሞተች?”

ተቀባይ፡- “ለዝግጅት የታረደን የበሬ ሥጋ ከአቅሟ በላይ በልታ ”

እንግዳ፡- “የምን ዝግጅት ነበር?”

ተቀባይ፡- “አይ እሱስ ተዝካር ነበር....” አለ ቀለል አድርጎ፡ :

እንግዳው በሁኔታው ግራ እየተጋባ

እንግዳ፡- “የማን ተዝካር ሊዘክር? የቅርብ ዘመድ ይሆን የሞተው ...?”

ተቀባይ፡- “አይ እሱስ የሞተችው ሚስትህ ናት...” ይለዋል አሁንም ማቅለሉን ሳይተው፡፡

እንግዳው በጣም ተደናግጦ እጅግ ካዘነ በኋላ ይህ ሁሉ ችግር እያለ ነው እንዴ ሁሉ ሰላም ነው የሚለኝ ብሎ ተናደደ፡፡ ቆየት ብሎም ሃዘኑን እንደምን ዋጥ አድርጎ

እንግዳ፡- “እሺ.... ቆይ ሚ-ስ-ቴ ም-ንን ሆና ሞተ-ች?”

ተቀባይ፡- “አስወርዳለሁ ብላ ነው” ይለዋል አሁንም ቀለል አድርጎ፡፡

እንግዳው ግራ መጋባቱ ጨመረ፡፡ መጀመሪያ የት የታሰበውን? አዞረው....


እንግዳ፡- “መቼ--ከ-ማን አ-ርግ-ዛ?” ብሎ ሲጠይቀው

ተቀባይ፡- “ሰዎች ካንተ ነው ይሉኛል.... እኔ ግን እጠራጠራለሁ!!!” ብሎት እርፍ፡፡



በፍስሃ ጌትነት

ቼድ ኢቫንስ ማረፊያው የት ይሆን?



የመሃልዳኛው ውሳኔያቸውን ማንበብ ጀምረዋል፡፡ «ተበዳይዋ የ19 ዓመት ወጣት ስትሆን በጊዜው ከፍተኛ የሆነ የአልኮል መጠጥ ወስዳ ነበር፡ ፡ ፍርድ ቤቱ እንዳረጋገጠው በጣም ከመስከሯ የተነሳ በፍቃደኝነት የግብረ ስጋ ግንኙነት ለማድረግ በምትችልበት ደረጃ ላይ አልነበረችም፡፡ ተከሳሹ ወጣቷን ወደ ሆቴል ሲወስዳትና ድርጊቱን ሲፈጽም ይሄን ያውቅ ነበር፤ በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቱ የቪዲዮና የሠው ማስረጃዎችን መርምሮ ውሳኔውን አሳልፏል፡፡ በዚህም መሠረት ተከሳሽ ቼድ ኢቫንስ ለ5 ዓመታት በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ተወስኗል»

እ.ኤ.አ. ሚያዚያ ወር 2012 ዌልስ የሚገኘው ካርናርተን ክሮውን ፍርድ ቤት የሼፊልድ ዩናይትድና የዌልስ ብሔራዊ ቡድን አጥቂ በነበረው ቼድ ኢቫንስ ላይ የፍርድ ውሳኔ የሠጠው በዚህ መንገድ ነበር፡፡ ኢቫንስ የ19 ዓመቷን ወጣተ ዌልስ ውስጥ በሚገኝ አንድ ሆቴል ከጓደኛው ጋር በመሆን አስገድዶ ደፍሯል በሚል ክስ ቀርቦበት የ5 ዓመት እስር በፍርድ ቤት ከተወሰነበት በኋላ ሁለት ዓመት ከግማሽ ቆይቶ በቅርቡ በአመክሮ ተፈቷል፡፡ ይሁንና ኢቫንስ አሁንም ድረስ ወንጀለኛ አለመሆኑን በመናገር ላይ ይገኛል፡፡ በወቅቱ ከወጣቷ ጋር የወሲብ ድርጊት የፈጸመው በስምምነት መሆኑን ይገልጻል፡፡ አሁን የ26 ዓመት እድሜ ላይ የሚገኘው ኢቫንስ ዳግም ወደ እግር ኳስ ተመልሶ ለሃገሩም ሆነ ለተለያዩ ክለቦች መጫወት ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን ወደ እግር ኳስ እንዳይመለስ በርካታ እንቅፋቶች ከፊቱ ተጋርጠዋል፡፡ እሱን ለማስፈረም ፍላጎት ያሳዩ ክለቦች ሁሉ ተቃውሞ እየገጠማቸው ሲሆን ለ14 ወራት ያህል ወደ ሜዳ መመለስ እንደማይችል በህግም ተነግሮታል፡

የነገረ መነሻ

ቼድ ኢቫንስ በወቅቱ የሼፊልድ ዩናይትድ ተጫዋች ነበር፡፡ በክለቡ ወሳኝ አጥቂ የነበረው ዌልሳዊ ወደ እስር ቤት ከመግባቱ አስቀድሞ በነበረው የመጨረሻ የውድድር ዓመት ለክለቡ በሁሉም ውድድሮች 35 ጎሎችን መረብ ላይ ማሳረፍ ችሏል፡፡ ኢቫንስ ሼፊልድን ከመቀላቀሉ በፊትም ለማንቼስተር ሲቲ ተጫውቷል፡ ፡ ይህ ተጫዋች በ2011 እ.ኤ.አ አንድ ምሽት የፖርት ቫሌ ክለብ ተከላካይ ከሆነው ጓደኛው ክሌይተን ማክዶናልድ ጋር ዌልስ ደንቢቫየር ውስጥ በሚገኝ አንድ ግሮሰሪ ውስጥ መጠጥ እየጠጡ ሲዝናኑ ነበር፡፡ በወቅቱ ከነሱ ጋር ስሟ ያልተጠቀሰች የ19 ዓመት ወጣት ሴት አብራቸው ስትዝናና ነበር፡፡ ምሽቱ በጣም ገፍቶ ወደ ሆቴላቸው ሲያመሩ የኢቫንስ ጓደኛና ሴቷ በስካር ራሳቸውን የዘነጉ ሲሆን ፍርድ ቤቱ እንደሚለው የሚያደርገውን ሁሉ የሚያውቀው ቼድ ኢቫንስ ብቻ ነበር፡፡ በዚያ ምሽት የ19 ዓመቷ ወጣት በሁለቱ ወንዶች የወሲብ ግንኙነት ተፈጽሞባታል፡፡ ይህ ሲሆን ግን እሷ አታውቅም፡፡ ለፍርድ ቤት በሠጠችው ቃል በወቅቱ የተፈጠረውን አንዱንም ነገር ማስታወስ እንደማትችል ተናግራለች፡፡ በሁለቱ ወንዶች ወሲብ እንደተፈጸመባት ግን በሆቴሉ መኝታ ክፍል የተገጠመው የደህንነት ካሜራ ቀርጾ ያስቀረው ቪዲዮ አሳይቷል፡፡

የሼፊልዱ ቼድ ኢቫንስ ለፍርድ ቤት በሠጠው

በወሲባዊ ጥቃት ተከሶ ከእስር የተፈታው ኳስ ተጫዋች ክለብ አጥቷል



ምላሽ ክሱን ሙሉ ለሙሉ ተቃውሞ ነበር፡፡ «ከወጣቷ ጋር የወሲብ ግንኙነት የፈጸምነው በእሷ ስምምነት ነው» በማለት በነጻ እንዲለቀቅ ጠይቆ ነበር፡፡ ነገር ግን በነጻ የተሰናበተው ጓደኛው ማክዶናልድ ብቻ ነበር፡፡ «ማክዶናልድ ራሱን አያውቅም ነበር» ብሏል ፍርድ ቤቱ፡፡ «ኢቫንስ ግን ሁሉም ነገር ሲፈጸም ያውቅ ነበር፡፡ የተመለከትናቸው የተቀረጹ ቪዲዮዎች የሚሳዩት ይሄንን ነው» በማለት ፍርድ ቤቱ አምስት ዓመታትን በእስር ቤት እንዲቆይ ወስኖበት ነበር፡፡

በእንግሊዝ ህግ መሠረት ያለ ፍቃደኝነት የሚፈጸም ማንኛውም አይነት የወሲብ ግንኙነት በአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈረጀ ነው፡፡ በአካልም ሆነ በስሜት ዝግጁ ካልሆነች ሴት ጋር ወይም ወንድ ጋር ወሲብ መፈጸም ያስቀጣል፡፡ ቼድ ኢቫንስ በዚህ ህግ መሠረት ውሳኔው እንደተላለፍበት በፍርድ ቤት ቢገለጽም ተጫዋቹ አሁንም ድረስ ጥፋተኝነቱን ለመቀበል አይፈልግም፡፡ «ሁሉም ነገር የተከናወነው በስምምነት ነው» ሲል ይናገራል፡፡

‹‹የመደቀ ዛፍ...››

ኢቫንስ ከወራት በፊት ከእስር ቤት እንደወጣ ያመራው ወደ ቀድሞ ክለቡ ነበር፡፡ የክለቡ አመራሮች በሥላም ተቀብለው ልምምድ እንዲሠራ ፈቀዱለት፡፡ ይሁንና ብዙም ሳይቆይ ከየአቅጣጫው ተቃውሞዎች መጉረፍ ጀመሩ፡፡ የክለቡ ደጋፊዎችና አንዳንድ ታዋቂ ግለሰቦች ኢቫንስ ወደ ሼፊልድ ዩናይትድ ተመልሶ ልምምድ መስራቱ እንዳሳዘናቸው በይፋ መግለጽ ጀመሩ፡፡ ማህበራዊ ድረ ገፆችና የመገናኛ ብዙሀኑ ቼድ ኢቫንስ ወደ እግር ኳስ መመለሱን የሚያወግዙ ጽሁፎችን በብዛት ይዘው ታዩ፡፡

በዚህ ምክንያት የ26 ዓመቱ ዌልሳዊ «ቤቴ» ካለው ክለብ ለቆ እንዲወጣ ተደረገ፡፡ በቅርቡ ደግሞ ኦልድሃም የተሰኘው የእንግሊዝ ክለብ ሊያስፈርመው ከስምምነት ደርሶ የነበረ ቢሆንም ይሽኛውም ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ ከመጀመሪያው የበለጠ ተቃውሞ እንግሊዝ ምድርን ሞላት፡፡ 165 ሺህ የሚደርሱ ሰዎች ቼድ ኢቫንስ ወደ እግር ኳስ መመለስ የለበትም የሚል የተቃውሞ ፊርማ አሰባ ሰቡ፡፡ የክለቡ የበላይ አመራር የሆኑ አንድ ስማቸው ያልተጠቀሰ ግለሰብም «ኢቫንስ ለኦልድሃም ከፈረመ ልጄ እንደተደፈረች እቆጥረዋለሁ» የሚል ሃይለ ቃል መናገራቸውን የተለያዩ ጋዜጦች ጽፈው አስነበቡ፡፡

በዚህ ሰበብ በሶስተኛ ዲቪዚዮን የሚሳተፈው ክለብ ከተጫዋቹ ጋር ያደረገውን ስምምነት አፈረሠ፡፡

«ተቃውሞ በረከተ፤ ደጋፊዎቻችን የግድያ ዛቻዎችን ሳይቀር ሰነዘሩ፤ ስፖንሰሮቻችንና የክለቡ አመራሮችም ቅሬታ ገብቷቸዋል፤ ስምምነቱን ያቋረጥነው በዚህ ምክንያት ነው» ሲል ክለቡ በድረ ገጹ ስለ ጉዳዩ መረጃ ሠጠ፡፡

ይሄንን የክለቡን ድርጊት እንደ ጎላ ቀርነት የቆጠሩት አሉ፡፡ የነል ዶት ኮም ፀሀፊ የሆነው ፒተር ስቷንቶን ክለቡ ስለ እግር ኳሱ ብቻ ማሰብ እንዳለበት በመጥቀስ በሌሎች አካላት ጫና ተገፍቶ የሚፈልገውን ከማድረግ ወደኋላ መመለሱ አሳፋሪ መሆኑን ጽፏል፡ ፡ ኢቫንስ በህግ የተፈረደበትን ቅጣት ከጨረሰ በኋላ ህግ የሠጠውን በነጻነት የመስራት መብት ሊነፈግ እንደማይገባ ገልጻል፡፡ ሰዎች ተቃውሞአቸውን ማሰማታቸው ዲሞክራሲያዊ መብት ቢሆንም ህግን ሊገለብጡ ግን እንደማይቻላቸው ፔተር በጽሁፉ አስፍሯል፡፡

የሃል ሲቲው ክለብ አሰልጣኝ የሆኑት ስቲቭ ብሩስም ተመሳሳይ ሀሳብ አላቸው፡፡ የተጫዋቹ መብት እየተገፈፈ ነው ባይ ናቸው፡፡

የኦሎምፒክ አሸናፊዋ እንግሊዛዊቷ ጆሲካ ኢኒስ ግን የሁለቱን ሰዎች ሀሳብ በእጅጉ ትነቅፋለች፡፡ ኢቫንስ ደግሞ ወደ እግር ኳስ መመለስ እንደሌለበት ተናገራለች፡፡

የሼፊልድ ዩናይትድ ስታዲየም አንደኛው ጎን በስሟ የተሰየመላት ጆሲካ «ኢቫንስ ለክለቡ የሚፈርም ከሆነ ስሜ ከስታዲየሙ እንዲነሳ እፈልጋለሁ» ብላ በይፋ ተናግራ ነበር፡፡

ቀጣይ አጣ ፋንታ

ቢቢሲ እስከ አራተኛው ዲቪዚዮን ድረስ በመውረድ የተለያዩ ክለቦችን በቼድ ኢቫንስ ጉዳይ አንድ ጥያቄ አቅርቦላቸው ነበር፡፡ «ልታስፈርሙት ትፈልጋላችሁ?» በማለት፡፡ በሶስተኛው ዲቪዚዮን የሚገኙ 12 ክለቦች ሊያስፈርሙት እንደማይፈልጉ በይፋ ምላሻቸውን ሲሰጡ ሌሎቹ 36 ክለቦች ደግሞ ፍላጎታቸውን በግልጽ ከመናገር ተቆጥበዋል፡፡

በደጋፊዎቻቸው የሚደርስባቸው ተቃውሞ፣ የስፖንሰሮቻቸው ጉዳይና የጋዜጦቹ ወሬ ስለሚያስፈራቸው ክለቦቹ ደፍረው ኢቫንስን ለማስፈረም አይንቀሳቀሱም፡፡ በዚህ ምክያት የቢቢሲው ፊል ማክነልቲ እንደሚለው ቼድ ኢቫንስን ዳግም በእግር ኳስ መድረክ የማየት እድል ላይኖር ይችላል፡፡



የኤሌትሪክ...

ከገጽ 25 የዞረ

መጠንና ጥራት ማምረት እንደተቸገሩና ለደንበኞቻቸው በወቅቱ ለማቅረብ እንዳልቻሉ ይናገራሉ፡፡የበርካታዎቹ ጥያቄዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ የመብራት መጥፋት እንዲሁም መቆራረጥ እያደገ ያለውን የኢንዱስትሪ ዘርፍ እየጎዳው መሆኑን ምንም ምስክር አያስፈልገንም፡፡ እነዚህ ፋብሪካዎች ነባርና የቆዩት ሲሆኑ አዲስ አምራች ወደስራ ለመግባት ቢፈልግና ከነባሮቹ ፋብሪካዎች ደግሞ የማስፋፋት ስራ ለመስራት የሚፈልግ ድርጅት ቢኖር የሃይል አቅርቦት የሚፈቀድለት አይመስልም፡፡በትንሹ በሳምንት ለሶስት ቀናት ለስድስት ሰዓታት የመብራት መቋረጥ ያጋጥማል፡፡ይሄን ያህል ሰዓት ቢሰራበት ምን ያህል ምርት ማመረት እንችል ነበር? ምን ያህልስ ገቢ እናገኝ ነበር? ምን ያህልስ የስራ እድል እንፈጥር ነበር? ምን ያህልስ የግብር ገቢ እናገኝ ነበር? ችግሩ ተያያዥና ሰፊ ነው፡፡

በእርግጥ ፋብሪካዎች ያለባቸውን የኃይል አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ እንዲችሉ መፍትሔ ይሆናሉ የተባሉ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሲነገር ሰምተናል፡ ፡ ችግሩ ግን ሐሳቡን ወደ ተግባር ለመለወጥ ጊዜ እየተወሰደ ነው፡፡ መቼ መፍትሔ እንደሚገኝ እንኳን በእርግጠኝነት አይታወቅም፡፡ አምራቾች ያለባቸውን የኃይል አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ እንደ አማራጭ በጀነሬተር ቢጠቀሙም ዘላቂ መፍትሔ ሊሆናቸው አልቻለም፡፡በወጪያቸው ላይ ተጨማሪ ወጪ በማውጣት ከውጭ አገር ከሚገባው ምርት ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን አያስችላቸውም፡፡እንዲያውም እንዲያ ነው እንኳን ወጪአቸውን ጨምረውበት፡ ፡የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ተጠቃሚው ላይ የሚጫን በመሆኑ ችግሩ መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡ ፡

ይቻላል እንኳ ቢባል ጀኔሬተሮቻቸው የሚወስዱት ነዳጅ ወጪ ከፍተኛ እየሆነ በመምጣቱ የማምረቻ ወጪያቸውን እያሳደገባቸው ነው፡፡ ችግሩ በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የኃይል አቅርቦቱ በተደጋጋሚ በተቋረጠ ቁጥር በማሽነሪዎች ላይ የሚፈጥረው ከፍተኛ ጉዳት ደግሞ አሁን አሁን የበለጠ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህንኑ በመሥጋት ባላቸው የማምረት አቅም ለመሥራት እየተቸገሩ መሆኑን ነው የሚናገሩት፡ ፡የማሽኖች ለአደጋ መጋለጥና መበላሸት ደግሞየሚያሳድረው ተፅዕኖ የማምረቻ ባለንብረቱ ላይ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን አገራዊ ጉዳት ማስከተሉም አይቀርም፡፡ የኃይል መቆራረጡ ያበላሸውን ማሽን መተካት ቢቻል እንኳን፣ የሚጠይቀው የውጭ ምንዛሬ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ይህም የሚሆነው አቅም ሲኖር ነው፡፡ አቅሙ ከሌለ ደግሞ ከስሮ ፋብሪካን ዘግቶ መውጣትም ይሆናል፡፡የችግሩ ስፋት እዚህ ድረስ ሊደርስ የሚያስችል መሆኑን በደንብ ልንመከተው ይገባል፡፡

የውጭ ምንዛሪ እጥረት አለ በሚባልበት በአሁኑ ወቅት(የቦንድ ሽያጭ ድረስ የሄድንበት አንዱ ምክንያት መሆኑ ልብ ይባል) በኃይል መቆራረጥ በሚፈጠር ከፍተት ምክንያት ሊወጣ የሚችለውን የውጭ ምንዛሬ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ያውም ካለ ነው፡ ፡የኃይል መቆራረጡ ዘለቄታዊ መፍትሔ የሚያሻው መሆኑ ባይታበልም፣ ይህ እስኪሆን ድረስ ግን የአገር ሀብት እንዳይባክን ለማድረግ የተለየ አሠራር መቀየሱ ግድ እያለ መጥቷል፡፡ የተጀመሩት የሃይል ማመንጫ ተቋማት ተጨማሪ የኃይል አቅርቦት ይዘው ወደ መስመር እስኪገቡ ድረስ ፋብሪካዎች ያለችግር ኃይል እንዲያገኙ ለማድረግ አማራጮችን መጠቀም የማይቻልም ከሆነ፣ ወደ ዘርፉ ለመግባት ያለውን ፍላጐት ሊያቀዛቅዘው እንደሚችል መታሰብ ይኖርበታል፡፡ አለበለዚያ ኪራይ ሰብሳቢ ብቻ ይሆንና አገሩ ሁሉ ህንጻ እና አገልግሎት ሰጪ እንጂ ወደ ኢንዱስትሪ የመሳቡ ጉዳይ ሊያቀዘቅዘው ይችላል የሚል ቅን የሆነ ስጋት አለኝ፡፡የምንታገለውስ ኪራይ ሰብሳቢን አይደለ !ማን ነበር ያሉት?

የኃይል አቅርቦት ችግሩ አገራዊ ችግር መሆኑ ይታወቃል፡፡ይሄን ደግሞ የማንክደውና የእኛን ፍላጎት አሟልተን ለጎረቤት አገር ለመሸጥ ደፋ ቀና በማለት አንድ የገቢ ምንጭ የምንፈጥርበት ዘርፍ መሆኑም ይታወቃል፡፡ይሁን እንጂ በአንፃሩ ወደፊት ሊስተካከል ይችላል ተብሎ ቢታመንም፣ ያ ጊዜ እየራቀ በመጣ ቁጥር ጊዜያዊ መፍትሔ (የፊት የፊቱን አለች ጓያ ነቃይ እንዲሉ)መፈለጉ ጊዜ ሊሰጠው አይገባም፡ ፡ ያለ ኃይል አቅርቦት ምርት ማምረት አይቻልምና አምራች ኢንዱስትሪዎች በስራቸው ላይ ምንም አይነት መስተጓጐል ሳይገጥማቸው ኃይል እንዲያገኙ ማድረጉ ወሳኝና አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ በሃይል አቅርቦቱ አካባቢ ያለው ችግር ከአንዳንድ (ይቅርታ ከኢቲቪ ወስጀውና ለምዶብኝ ነው) አምራቾች እንደሚሰማው ችግሩ የኃይል አቅርቦት መቆራረጥ ብቻ ሳይሆን ለተገነባው ማምረቻ የሚሆን ኃይል ለመቀጠል ረጅም ጊዜ እየወሰደ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ሌላ መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ነው ፡፡ አሁን ያለው ችግር በቂ የኃይል አቅርቦት ያለማግኘት ብቻ ሳይሆን ኃይል ለማስቀጠል ያለውም ጊዜ ወሳጅና ደጅ ጥናትም አማራሪ በመሆኑ ለሙስና በር ከፋች ሂደት መሆኑን ያሳያልና በዚህ አካባቢም ያለው ችግር መታየት ይኖርበታል ከሚሉት ወገን ነኝ፡፡

ስለሆነም የጠቀስናቸውና ከእኛ ግንዛቤ ውጭ የሆኑ ተደማሪ ችግሮች ይኖራሉ ብዬ ስለምገምት(መገመት አያስጠይቅም ያለኝ ማን ነበር?) አሁን ባለንበት ደረጃ ግን መታሰብ የሚገባው ወደ ምርት የገቡ ኢንዱስትሪዎች ያለ ችግር እንዲያመርቱ ለማስቻል አቋራጭ መፍትሔ መፈለግ ነው፡፡ ለምሳሌ ቅድሚያ ለመኖሪያ ቤት ተጠቃሚዎች ይሰጥ ወይስ ማምረቻዎች ሁሌም ኃይል ቢኖራቸው ይመርጣሉ የሚሉ አይነት ጥያቄዎች፡፡ በስንት ሰዓት የመኖሪያ ቤቶች ቢጠፋ አይቸገሩም ከሚል አንስቶ (ለምሳሌ ከሌሊቱ ስድስት እስከ ንጋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ባይኖር ይሻላል፤ ቀንና እስከ ምሽቱ ሶስትና አራት ሰዓት ከሚጠፋብን)ለማለት ነው፡፡ በእያንዳንዳችን ቤት ኃይል የማናገኝበት ጊዜ ከሚፈጥርብን ችግር የበለጠ ግን ማምረቻዎች ተጐጂ እየሆኑ የመጡ ስለመሰለኝ ነው፡፡ የእነሱ ጉዳት ደግሞ ሲጠራቀም ወይም የማምረቻ ወጪያቸውን ከፍ ባደረጉ ቁጥር ወይም የምርት እጥረት ይከሰታል፡፡ የሚፈጠረው የዋጋ ግሽበት ተወደደም ተጠላ መደምደሚያ የሚሆነው የፈረደበት ሸማቹ ኪስ(እኛው) ውስጥ መግባት ነው፡፡ ያልታሰበ የማምረቻ ወጪ በዛብን ብለው የሚቀጥሉትን ዋጋ የሚሸከመው ልማደኛው ሸማቹ ይሆናል የሚል ግምታዊ መደምደሚያ ላይ ያደርሰናል፡፡ ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ተያያዥ ቀውሶች ሊከሰቱ ይችላሉና ጉዳዩ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ታይቶው የተሻለው አማራጭ መንግስታችን ጊዜ ሳይወስድ ሊያስቀምጥልን ይገባል እላለሁ፡፡



በዘገሊላ እለት እንዲህ መረርና ጠንከር ያለ የመብራት ችግርን ከመተረከ አዳዲስ የወጡትን ዘፈኖች(ሰሞኑን ምን ያልወጣ ዘፈን አለ?) የሙዚቃ ሻምፒዮን ተጀመረ እንዴ? ከባህል ይሁኔ በላይ፤አምሳል ምትኪ፤ከዘመናዊ ጸሀዬ ዮሀንስ፤አብነት አጎናፍር፤ማዲንጎ፤ምነው የትኛውን ከየትኛው እንድናስቀድም ነው የ ተ ደ ረ ደ ረ ል ን ፡ ፡ መ ል ካ ም ፤ ለማንኛውም ወቅቱ የበዓል ሰሞን አይደለ! በወደድነው ዘፈን ከዘገሊላ እስከ የኔታ ዘፈን ድረስ ሲዲ እየቀያየርን እስከስታውን ማስነካት ነው፡፡ቸር ይግጠመን፡፡

የከተማችን...

ከገፅ 6 የዞረ ...

የችግሩ ስፋት

በማህበራዊ ስነልቦና ባለሙያዎቹ አቶ በላይነህ ዘለለውና አቶ ዮሴፍ አህመድ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው ወሲባዊ ንግድ የሚፈጸምባቸው ማሳጅ ቤቶች በሴቶችና በወጣቶች ላይ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ስነ-ልቦናዊ እና የስነ-ተዋልዶ ጤና ችግሮችን እንደሚያስከትሉ ያሳያል፡፡ በአንድ ማሳጅ ቤት ትሰራ የነበረች ወጣት ከስራው ጋር በተያያዘ ስለሚያጋጥማት ችግር ምንም አይነት ዋስትና እንደሌላት እንዲህ ስትል ታስረዳለች።አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣው ሰው በጣም የተለያየ ባህሪ ያለው ሰው ነው፡፡በዚህ ምክንያት ሁሉም የተለያየ ፍላጎት ስላለው፤አንዳንዱ ሰው ኮንዶም መጠቀም አይፈልግም፣ሌላው ደግሞ በፊንጢጣ የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈልጎ የሚመጣ አለ፡፡ ይህን ጊዜ ነው እንግዲህ ግጭት የሚፈጠረው፡ ፡ በተለይም ማታ የሚመጡት ወንዶች አብዛኛዎቹ መጠጥ ጠጥተው ስለሚመጡ የጠየቁትን ወሲብ አይነት እንቢ ካልኳቸው በጉልበት ሊፈጽሙብኝ ይሞክራሉ፤ አንዳንድ ከውጭ የመጡ ኢትዮጵያውያን (ዲያስፖራ) ወሲባዊ ፍላጎታቸው የሚረካው እኔን በማሰቃየት፣በመምታት፣በመንከስ ስለሆነ የተለያየ ጊዜ አደጋ ደርሶብኝ ያውቃል፡፡ ግን ይህንን ችግር ለማን ትናገረዋለህ ለባለቤቱ ብትነግረው ቢዝነሱ እንዳይበላሽበት ስለሚፈልግ ለፖሊስ እንድንናገር አይፈልግም እንዲሁም ደንበኞችን ላለማጣት ሲል ምንም እርምጃ አይወስድም፡፡እኔ ተነድቼ ብቻ ነው የምቀረው ብናገር ሊያባረረኝ ስለምችል ዝም ነው የምለው፡፡ ›

እነዚህ ሴቶች ምንም አይነት ጥቃት ቢደርስባቸው ለህግ አስከባሪ አካላት ሄደው አይናገሩም፤ ምክንያቱም የሚሰሩት ስራ በማህበረሰብ የተወገዘና እራሳቸው እራሱ የማያምኑበት ስለሆነ ጉዳት ደረሰብኝ ብለው ለፖሊስ ሪፖርት አያደርጉም፡

> “ማታ የሚመጡት ወንዶች አብዛኛዎቹ መጠጥ ጠጥተው ስለሚመጡ የጠየቁትን ወሲብ አይነት እንቢ ካልኳቸው በጉልበት ሊፈጽሙብኝ ይሞክራሉ

፡ይህ ደግሞ በእነሱ ላይ የሚደርሰውን የህይል ጥቃት መጠን ለማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡የመፍትሄ እርምጃ እንዳይወሰድ ደብቆ ያስቀረዋል ከዚህም አልፎ በሴ ቶ ቹ ላይ የሚደርሰውን አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ተገንዝቦ ለመፍታት የሚደረገው ጥረት ያስተጓጉለዋል› ይላል፡፡


ይህ የስነ-ልቦና ችግር በተለይም እንደ ኢትዮጵያያሉ ህይማኖታዊና ወግአጥባቂማህበረሰብ ባለበት እነዚህ ወጣቶችና ሴቶች ከፍተኛ ለሆነ ለስነ-ልቦና ችግር ይጋለጣሉ፡፡በዚህም ምክንያት ወደ ጫትና ሺሻ ቤቶች በመሄድ ሱስ አስያዥ ዕፅና አልኮል በመጠቀም ችግራቸውን ለመርሳት ይሞክራሉ፡፡ በ2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ አስተዳደር ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ በተካሄደው ጥናት ሱስ አስያዥ ዕፆች(ጫት፣ሲጋራ፣ሀሺሽ፣ሺሻ፣ሄሮይን) እና የአልኮል መጠጦችን መጠቀም ችግር ከሁሉም በላይ የሆነ እና ለሌሎች ችግሮች ሁሉ መስፋፋት በመንስኤነቱ ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ ሁሉም ግለሰቦች አረጋግጠዋል፡፡ ለአንደኛው ሱስ ተጋላጭ መሆን ለሌላኛው መንገድ እንደሚከፍትና ተያያዥነትም እንዳላቸው በጥናቱ ላይ የተሳተፉ ሰዎች ገልጸዋል፡፡

የመፍትሔ አርምጃዎች

ጥናቱ የተለያዩ የመፍትሔ ርምጃዎችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ለማህበረሰቡ በቂ ግንዛቤ መፍጠር፣ ባለድርሻ አካላት በጋራ ተቀራርበው መስራት እንዳለባቸው፣ የተለያዩ የህይማኖት ተቋማት ለተከታዮቻቸው ግንዛቤ መፍጠር እንዳለባቸው፣ ባለሀብቱ ኢንቨስትመንቱን ሀገር በሚጠቅም ነገር ላይ እንዲያውለው ተከታታይነት ያለው ትምህርት መሰጠት እንዳለበት፣ህጋዊ ማሳጅ ቤቶችን ማበረታታና ሌሎችም የመፍትሄ ሀሳቦች ተጨምረዋል፡፡ ባለድርሻ አካላት ተቀራርበው በመስራት እየተፈጠሩ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የጋራ እቅድ በማውጣት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ፤ ስነ-ልቦናዊ የስነ ተዋልዶ ጤና ችግሮች ከወሲባዊ ንግድ ከሚካሄድባቸው ማሳጅ ቤቶች ጋር ያላቸው ትስስር ጠንካራና ቀጥተኛ መሆኑንና እነዚህ ችግሮች አምራች የሆኑትን ትውልዶች ለሀገራቸው ማበርከት የሚጠበቅባቸውን እንዳያበረክቱ እያደረጋቸው እንደሆነ ጥናቱ አሳይቶል፡፡ በስተመጨረሻም በመጤ ባህሎችና ልማዳዊ ድርጊቶች አሉታዊ ተፅዕኖ ምክንያት ላልተገቡ ባህሪያት እየተጋለጡ ያለውን ትውልድ ለመታደግ የተለያዩ እርምጃዎችን መወሰድ እንዳለበት ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

የተለያዩ የህይማኖት ተቋማት ሰለወሲባዊ ንግድ አስነዋሪነትና መጥፎ ገጽታዎች ለተከታዮቻቸው በማስተማር ወጣቶችና ሴቶች ከእንዲዚህ አይነት ተግባር እንዲቆጠብ ትምህርት ቢሰጡ፣ ባለሀብቱ ማህበረሰብን የሚጎዱ ተግባራት ላይ ኢንቨስት እንዳያደርግና ሴቶችንና ወጣቶችን ዘለቀታዊ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ ግንዛቤ መፍጠር ስራዎችን ማከናወን ይኖርበታል። ለማሳጅ ቤት ባለቤትቶች ህጋዊ ሆነው ለህብረተሰብ ተገቢውን ማሳጅ አገልግሎት እንዲሰጡ በየጊዜ ትምህራታዊ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል ። በህጋዊነት እና የማሰጅን ስነምግባር ጠብቀው የሚሰሩ ማሳጅ ቤቶችን የተለየ ደጋፍ እና እረዳታ በደረግላቸው በቀላሉ ከገበያው የማይወጡ ይሆናሉ፡፡ ትምህርት ቤቶች አካባቢ የተከፈቱ እንዲሁም መኖሪያ አካባቢ የተከፈቱ የወሲብ ንግድ የሚፈጸምባቸው ማሳጅ ቤቶች በቶሎ ካካባቢው ቢነሱ እና በቦታው ለሌሎች የማህበረሰብን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የማያውክ ተግባረት የሚፈፀምባቸው በሆኑ ሀገርም ህብረተሰብንም የሚጠቅም ይሆናል ። ቤተሰብና ትምህርት ቤት በጋራበመጣመርየልጆቻቸውንናየተማሪዎቻቸውን ውሎ በቅርብ ሆነው መከታተል አለባቸው፡፡ በተለያዩ ጊዜ የልጆቹን ሁኔታ ለመገምገም ወላጅና ትምህርት ቤት በጋራ በመዋያየት የሚታዩ ችግሮችን በእንጭጩ ለመቅጨት ይረዳቸዋል፡፡ቋ



ታደሰ...

ከገጽ ፲፩ የዞረ

መገለጫው ነው፡፡ የዚህን አይነት አጨራረስም እንዲኖረው ታሪኩ ራሱ ይገፋፋል፤ ስለዚህ እኔም ታሪኩን ለዚህ አይነት አጨራረስ አዘጋጀዋለሁ፡፡ ይሄነው ምክንያቴ፡፡

ቁም ነገር ፡- ታደሰ ብዙውን ጊዜ በድርሰት ገጸ ባህሪ ውስጥ ቆንጆ ብሎ የሚስላቸው ወንዶች የራሱን አቋምና መልክ የያዙናቸውና ገጸ ባህሪው ታደሰ ራሱ ነው የሚሉ አሉ ፤ይህ ትክክል ነው እንዴ?

ታደሰ ፡- /ሳቅ...../ ሊሆን ይችላል ፡፡ በፊት ስለኔ ብዙ ይወራል፤ ስለሚወራ እሱን አስገብቼው ይሆናል፤እኔ አሁን አይደለም ነው ማለት አልችልም፡ ፡ .

ቁም ነገር ፡- አሁን በሀገራችንም በውጭም ሀገር በስፋት ስለሚታየው የተመሳሳይ ፆታ ግኑኝነት (ግብረ ሰዶም) በሴላው መንገድ ድርሰትዎ ላይ ጽፈውታል፤ በዚህ ጉዳይ በዛን ዘመን የነበረው ሁኔታ ምን ይመስላል? እንዴትስ ደፍረው ሲፃፉት ቻልክ? ተቃውሞስ አልገጠመዎትም ?

ታደሰ ፡- አዎ! በዛን ዘመን በተወሰነ ደረጃ ነበረ፤ ግን እንዲህ በአደባባይና በግልጽ አይወራም፡ ፡ ነገሩ በጣም ነውር ነው ፡፡ በጣም አስከፊ ነው፡፡ ነገር ግን ከዕውነታው መሸሽ አልችልም ነበር፡፡ እኔ የያዝኩት እውነት የሆነ፤ ያለ ነገር ነበረ፡፡ ስለዚህ መጻፍ ስለነበረብኝ ፃፍኩ፡፡ በፊ ለፊት የሚቃወመኝ የለም ፤ከጀርባ ሆነው ግን የሚቀወሙ አሉ፡፡

ቁም ነገር፡- እንደውም አንዳንዶች እንደሚሉት ይህን ነገር ከፃፉ በኋላ ጫናዎች ስበዛብዎ ነው ታደሰ ሲበን ከድርሰቱ ስለም የወጡት የሚል ነገር አለ?

ታደሰ ፡- ይሄ ውሸት ነው፡፡ ራቅኩኝ እንዴ ከድርሰቱ አለም?

ቁም ነገር ፡- አራቁም? እንግዲህ የእርሶ አዳዲስ ስራዎች ስንባብ ከቀረቡ ቆዩ?

ታደሰ ፡- ያን ጊዜ የምጽፈውን ያህል፤ያቅሜን ያህል ጽፌ ነው ያቆምኩት፡፡ ከዛ በኋላ እንግዲህ ተሳትፎ ለማድረግ አልቻልኩም ይሆናል፡፡ ወይም ደግሞ በአንዳንድ ሁኔታዎች አለመመቸት ይሆናል እንጂ ያ ምክንያት አይደለም፡፡

ቁም ነገር ፡- ስህተመት ያልበቁ ስራዎች አሉዎት ?

ታደሰ ፡- አሉ ብዙ፤ግን አሁን የት እንዳሉ አላውቅም፡፡

ቁም ነገር ፡- እስቲ ስስቤተሰብና የትዳር ህይወትዎ ያጫውቱኝ?

'ታደሰ ፡- አግብቼ ነበር፤ በትዳር ውስጥም ሁለት ልጅ አፍርቻለሁ፤ ከወለድኳት ልጆቼ ውጭ ብዙ ያሳደኳቸው ልጆች አሉኝ፡፡ ልጆቼ ማርታ ታደሰና ፤ዮናታ ታደሰ ይባላሉ፡፡ የሚኖሩት ውጪ ነው፡፡ የመጀመሪያ ልጄ ማርታ ታደሰ አሜሪካን ሀገር ዶ/ር ነች ፤ አግብታ የሶስት ልጆች እናት ሆናለች፡፡

ቁም ነገር ፡- ከልጆዎ ሆነ ካሳደጓችው ልጆችዎ የእርሶን ፈለግ ተከትሎ ወደ ስነ ጹሑፉ የገባ አለ?

ታደሰ ፡- አይ ወደ ስነ ጹሑፉ እስካሁን የገባ አላየሁም ፡፡ ባይሆን የባንኩን ስራ ያሳደኩት የወንድሜ ልጅ ተከትሏል፡፡

ቁም ነገር ፡- ባለቤትዎስ የትናቸው?

ታደሰ ፡- እሷ ያለችው አሜሪካን ነው ፡፡ ከተለያየን ረጅም አመታት አለፉ፡፡

ቁም ነገር ፡- ስምን ተስያያችሁ?

ታደሰ ፡- እሷ እንደምክንያት የምታቀርበው አስመራ በነበርኩበት ወቅት ሚስትና ልጆች አሉት ነው የምትለው ፡፡ እኔ ግን ውሸት ነው፤ አጉል ጥርጣሬ ይዞሽ ብልም አልሰማቸኝም፡፡ እኔ እንድንፋታ አልፈልግም ነበር፤ባለቤቴን በጣም እወዳታለሁ፤ጥሩ ሰው ነበረች ለኔ፤ እኔ እሷ እምነት ታጎላለች ብዬ አልጠረጥራትም ፤እሷ ግን እኔን አታምነኝም፡ ፡ ያኔም እስከመጨረሻው ድረስ አብረን እንሁን ብዬ ጠይቂያታለሁ፤ እሷግን ለምን እንደማትፈልግ አይገባኝም፡፡ ሌላ ሰው ወዳ ነው እንዳልል አይደለም ፤ እንደማቃት በሁለታችን መሀል ሰው አታስገባም፡፡ እኔ ደግሞ ልጆች ቢኖሩኝ ይህን ያህል አመት መንፈስ አይደሉ ተደብቀው የሚኖሩት ፡፡

ቁም ነገር ፡- አሁን የመታዳደሪያ ገቢዎ ምንድ ነው?

ታደሰ፡- ጡረታ አለኝ፤ ሌላ ደግሞ የቤት ክራይ አለኝ፡፡

ቁም ነገር ፡- በወር ምን ያህል ያገኛሉ?

ታደሰ፡- ባንክ የነበረኝን ደሞዜን እንደያዝኩ ነው የወጣሁት፤የምኖረው ብቻዬን ነው፡፡ የወንድሜ ልጅ ዳንኤል ገዛህኝና የህቴ ልጅ እስከ ባለቤቷ ይደግፉኛል፡፡ እኔ እንደውም አሁን የሚያሳስበኝ ገቢና ወጪዬን አለማወቄ ነው /ሳቅ...../፡፡

ቁም ነገር ፡-አሁን ዕድሜዎ ስንት ደረሰ? የጤንነት ሁኔታዎስ ምን ይመስላል?

ታደሰ፡- አሁን 84 ዓመቴ ነው፡ ፡ ጤንነቴ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ምንም አይነት በሽታ የሉብኝም፡፡

ቁም ነገር ፡- ምን አይነት ባህሪ አለዎት?

ታደሰ ፡- እኔን? /ረጅም ሳቅ..../ ይሄ በጣም አስቸጋሪነው፡፡ ስለ ራሴ ለመናገር ትንሽ ይከብዳል፡፡ ጥሩ ሰው ነኝ እንዲህ ነኝ ለማለት ይከብዳል፡፡

ቁም ነገር ፡- እኔ እንደውም የሰማሁት ፊስፊት ተናጋሪ እንደሆኑና ያሳመኑትን ነገር እደማያደርጉ ነው?

ቁም ነገር ፡- አዎ! ይሄ እውነት ነው፤ ሁሉን ነገር ፊት ለፊት መናገር እወዳለሁ፡፡ እንደውም አንድ ጊዜ አንድ አብሮ አደግ ወዳጄ ሁል ጊዜ የኔን አጭር ልቦለድ ጀማሪነት ይናገር ነበረ፤ አንድ ቀን ይመጣና «አፈልግሀለው» ብሎ «አንተን በኔ የመጽሐፍ ምርቃ ዝግጅት ላይ ስለኔ እንድትናገር እፈልጋለሁ» አለኝ፤ እኔማምን ስላንተ እናገራለሁ እኔ የምናገር ከሆነ እውነቱን ስለምናገር ይበላሽብህልና ይቅርብህ አልኩት፡፡ እኔ በወቅቱ ሀሳቤ እሱን የሚደግፍ አልነበረም ፤ከተናገርኩ ደግሞ የምናገረው ይህን ሀሳቤንነው፡፡ ይህ ሰው ወዳጄ ቢሆንም ችኩልና ብዙ ጊዜ ስህተት የሚሰራ ነው ፡፡ በዛ ላይ በወቅቱ ቅድም ባልነው በግብረ ሰዶማዊነት ይታማ ነበር ፤ታዲያእንዴት ብዬ ነው የማወራው፡፡ ስለዚህ ከሚበላሽበት ብዬ ሌሎች ስለሱ ምስክርነት ሰጡ፡፡ እሱም ነገሩ ስለገባው በዚው የኔና የሱ ነገር አከተመ፡፡ እና ደባብቆ ማለፍ የሚባል ነገር አልወድም፡፡

ቁም ነገር ፡- ሴሳው መንገድን እና መስከረም መጽሐፎ በድጋሚ ታትሞ ስህትመት ሲበቃ እንደሆነ ሰምቻስሁ እርስዎ በዚህ ምን ደሰማዎታል ?በዚኛውስ ትውልድ እንደበፊቱ ተቀባይነት ይኖረዋል ብስው ያስባሉ?

ታደሰ፡- በድጋሚ ሊታተም በመሆኑ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ ሥራዎቹ ጥሩ ስለሆኑ ተቀባይነት የማይኖራቸው ምክንያት ይኖራል ብዬ አላስብም፡፡

ቁም ነገር ፡- አመሠግናስሁ፡፡

ሜሪ ጆይ የልማት ማህበር

የእርስዎ ማንኛውም ድጋፍ (በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በአልባሳት...) የህፃናት ድጋፍ(ስፖንሰር ሺፕ) ለአንድ ህፃን 300 ብር በወር፣ የአረጋውያን ድጋፍ (ስፖንሰር ሺፕ) ለአንድ አረጋዊ 300 ብር በወር፣ የድርጅቱ አባል መሆን (ፕሳቲኒየም፣ ወርቅ፣ የብር...) ቀጣዩን ትውልድ በመንከባከብና በማስተማር እንዲሁም አረጋዊያን ቀሪ ዘመናቸውን በደስታ ያሳልፉ ዘንድ እያንዳንዳችን ሃላፊነታችንን እንወጣ! በጋራ በምንደግፋቸው ህፃናትና አረጋዊያን ህይወት ላይ ሰውፕ እናምጣ!

ማህበሩ አድራሻ፡- መገናኛ ከዲያስፖራ አደባባይ ወደ ቶፕ ቪው (የካ ተራራ ት/ቤት) መውጫ 50 ሜትር ገባ ብሎ
ስበስጠ መረጃ ስልክ 0118-96-63-21/22/23 ሞባይል 0911 20 85 18

ንብረት ...

ከገፅ 36 የዞረ ...

ድራማን በድፍረት የጀመረ ሰው ነው። ከዛ ውጭ አዘጋጁ ይታገሱ ገስጥ ተጫኔና ሌሎችም ከፕሮዳክሽን ጀርባ ያሉት በሙሉ የነሱ አስተዋጽኦ እከን እንዲወደድ አድርጎታል።

ቀም ነገር፡- ህይወትህን የምትመራው በዕቅድ ነው? ወይስ እንደ አመጣጡ?

ንብረት፡- እኔ ምን አስዋሸኝ? እንዳመጣጡ ነው የምኖረው /....ሳቅ/፤ የምን ዕቅድ ነው።

ቀም ነገር፡- ከሞት በኋላ ቀጣዩ ምዕራፍ ምን ይመስልሀል?

ንብረት፡- እኔ ሰማያዊቷን እየሩሳሌምን እወርሳለሁ፡ ፡ ምክንያቱም እየሱስ ሞቶልኛል።

ቀም ነገር፡- ከሰማኸው ውሸት ውስጥ በጣም ያስገረመህ ውሸት አስ ?

ንብረት፡- እንዴ ብዙ ውሸት፤እኔም እራሴ ስኖር ውሸታም ነኝ፤ዓለም እንዳለች በውሸት የተሞላች ነች፤ ስለዚህ የትኛውን ውሸት ለይቼ ልንገርሽ?

ቀም ነገር፡- አይዶል ላይ ተወዳዳሪ ብትባል በምን ብትወዳደር ይሳካልኛል ትላለህ ?

ንብረት፡- በድብድብ! /....ሳቅ/ የሚችለኝ ካለ ይምጣ ።

ቀም ነገር፡- የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት እናድርግ ሲባል ምንድን ነው ወደ አዕምሮህ የሚመጣው ?

ንብረት፡- ማድረግ ይቻላል፤ በጣም ቀላል ነው። እኔ ክርስቲያን ስለሆንኩ እግዚያአብሔር ሟቾን በገነት አኑርልኝ እላለሁ። አንዳንድ ጊዜ ግን ምን ይመጣብኛል መሰለሽ? ሰው አይደለሁ! ተንኮልም ወደ አዕምሮዬ ይመጣብኛል። በአካባቢሽ ያሉ ሰዎች ሀሳብሽን ሊሰርቁት ይችላሉ፤አንዳንዱ የሆነ ተመስጦ በራሱ ሙድ ውስጥ የሚገባ ሰው አለ፤ሀሜት የሚጀምርም ሰው አለ፤እነዚህ እነዚህ ነገሮች ሳይ ሐሳቤ ሊሰረቅ ይችላል፤ከራሴ ህሊና ጋር ስሆን ግን የሞቱትን ነፍስ ይማር እላለሁ።

ቀም ነገር፡- የዘና ጥቅመ ይታወቃል፤ ጉዳቱስ ምንድን ነው?

ንብረት፡- እንደፈለጉ አለመሆን ፤ሰው በመሆን የምትፈጽሚያቸው ስህተቶች አሉ፤ አንዳንድ ጊዜ፤ያን ማድረግ አይቻልም። እኔ ግልፍተኛ ነበርኩኝ፤ያንን አሁን እህ..... ብዬ እተወዋለሁ፤ እንደምንም ችዬ እና ተወጣጥሬ፤ ይቺ በጣም ከባድ ነች። አንድ ጊዜ ከመገናኛ ጀምሮ አንድ መኪና መንገድ እየዘጋብኝ እየዘጋብኝ ይመጣል፤እኔም ችዬ ዝም አልኩት። መጨረሻ ላይ አልፈው ወደ ባልደረቡ ጋር ልዞር ስል መልሶ ከፊቴ መጣና ተናገረኝ፤ተናድጀ የሆነ ኃይል ቃል ስናገረው በአካባቢው ከነበሩት ጎረምሶች መካከል አንዱ ‹ሽረ እከዬ አንተም ስድብ› ሲለኝ ‹ሂድ እኔ ሚካኤል ነኝ› አልኩት /..ሳቅ/ ይቺ ይቺ ናት ጉዳቷ።

ቀም ነገር፡- ህይወት ምን አስተማረችህ ?

ንብረት፡- ብዙ ነገር። እኔ ነገን አላውቃትም ፤በእግዚያአብሔር ቸርነት እዚህ እንደደረስኩ አውቃለሁ፤ ተንገላትቼ ነው ያደኩት፤የረሐብ ጥጉን አውቀዋለሁ፤ከዛ ደግሞ አሜኝቼ በግል ሄሊኮፕተር አልሄድኩም እንጂ የመዝናናት ጥጉንም አይቻለሁ፤ ስለዚህ ህይወት ከዚህ በላይ ምንም ልታስተምረኝ አትችልም። ከዚህ በኋላ ከኔ ምን ይጠበቃል የሚለውን ለማድረግ ነው የምጥረው፤ እንደሰው ስህተት ብሰራም አሁን ለህይወት ዋጋ እሰጣለሁ፤ታላላቆቼን አከብራለሁ፤ማህበራዊ ጉዳይ ላይ በደንብ እሳተፋለሁ፤እንደ አንድ አርቲስት በአካል ጉዳተኞች ላይ የኢትዮጵያ የአዕምሮ ውስንነት ያለባቸው ብሔራዊ ማህበር አምባሳደር ነኝ፤እንደውም በዚህ አጋጣሚ መጽሔታቸውን የሚያነቡ ሁሉ ብሔራዊ ማህበሩን እንዲጎበኙ ጥሪ አቀርባለሁ። ምክንያቱም ማንም ሰው የአዕምሮ እድገት ውስንነት የሌለበት ልጅ ላለመውለድ ዋስትና የለውም፤ማንም ሰው ደግሞ ባጋጣሚ ድንገተኛ አደጋ ይህ እንደማይከሰትበትም ዋስትና የለውም፤ ስለዚህ ብሔራዊ ማህበራችን ከዘሪሁን ሀንፃ ጀርባ ይገኛል፤ በዚህ ጉዳይ ላይ መስራት የሚፈልጉ ሰዎች መጥተው እንዲያናግሩኝና አብረን እንድንሰራ እላለሁ፡ ፡ እና ህይወት እነዚህን እነዚህን ኃላፊነቶቼን እንድወጣ አስተምራኛለች።

ቀም ነገር፡- የመጀመሪያ ፍቅር ከሁስተኛው በምን ይስያል?

ንብረት፡- አዎ! ብዙ ሰው እንደዚህ ይላል። ስለዚህ እንደዚህ የሚሉትን ጠይቂያቸው እኔ አላውቅም /..ሳቅ/ ስለሁለቱም ።

ቀም ነገር፡- በልጅነትህ በባህሪህ ምን አይነት ልጅ ነበርክ ?

ንብረት፡- በልጅነቴ ቀይ ልጅ ነበርኩ /...ሳቅ/፤በባህል ታንፆ የማደግ ነገር ነበር ቤተሰባችን ውስጥ፤ይህ ማለት ስማር እራሱ የመጀመሪያ ትምህርቴ ሀ. ሁ ነው ፤ፊደል ተማርኩት ለጥቆ አቦጊዳ ከዚያ መልዕክተ ከዚያ ደግሞ ዳዊት ደገምኩኝ፤ እንደዚህ እያልኩ መደበኛ ትምህርት ቤት ስገባ እንደ አሁኑ ዕውቀት ተኮር መመዘኛ ሳይሆን እጄን ጭንቅላቴ ላይ አድርጌ በእጄ ተቃራኒ በኩል ያለውን ጆሮዬን ንካ ተብዬ ቢቃ ደርሷል ተብሎ ነው የገባሁት። በባህሪዬ የተረጋጋሁ ልጅ አይደለሁም ፤ቶሎ አኩራፊ ነኝ፡ትንሽ ደግሞ ተደባዳቢ ቢጤም ነበርኩኝ፤ቶሎ ውጤት ፈላጊ ልጅ፣ ብዙ የምጠይቅ ነበርኩ በአጭሩ /..ሳቅ/።

ቀም ነገር፡- ከዘሩ ሞሳና አዛሱ ስቤተሰቡ ደበልጥ የሚያስበው ማነው?

ንብረት፡- ለኔ ሁለቱም እኩል ናቸው ። ዘሩ ሞላ ስናየው ዝም ብሎ ቋጣሪ ስግብግብ ይመስላል፤የሚንገበገበው ግን ለልጆቹ ነው ፡ ፡ ዘሩ በአሳማኝ ወጪ ብቻ የሚያምን ሰው ነው ። አንዳንድ ጊዜ ግን አሳማኝ ወጪዎችን ጭምር መሸወድ የሚፈልግ ሰው ነው /..ሳቅ/ ፤ለመኖር ደግሞ ይሄ አስፈላጊ ነገር ነው ፡ ፡ አሳማኝ ያልናቸውን ነገሮች ትተን ወደፊት ደግሞ በርከት ብሎ ከዛ ይበልጥ አሳማኝ ነገሮች ሲመጡ ለነዛ ልናውላቸው እንችላለን፤እና ዘሩ ሞላ እንደዚያ አይነት ሰው ነው ። ደግም ነው። እከን ያህል እንቅልፋም ሰውዬ፣ትርፌን ያህል ሆዳም ሴትዮ፣ሻሼን ያህል ምላሳም ይዞ መኖር እንደቤተሰብ አባል፤ የዘሩን ደግነት ነው የሚያሳየው። አዛሉንም ካየናት ቀለል ያለች እናት ነች።

ቀም ነገር፡- ሀገራችን በቀሳሱ ከድህነት መውጣት ያልቻለችው ስምን ይመስልሀል ?

ንብረት፡- ለምዳው ነዋ! /...ሳቅ/ ፤ ለምዳው ነው የሚለው ቃል ከማሳቅ አንፃር ይታይልኝና፤እኔ ትልቁ ምክንያት ብዬ የማስቀምጠው ሰው ላይ አልተሰራም ። ከድህነት ለመውጣት ሰው አለማም ። የመስራት ባህላችን የደከመ ነው። ድሮ ይህችን ሐገር ቅኝ ግዛት ሊያደርጓት የፈለጉ ፈረንጆች ስለቱን የሚሰራውን ቀጥቅጦ ጎራዴውን የሚያበጀው፣መቆፈሪያውን ፣ማልሚያውን የእርሻ መሳሪያውን የሚሰራውን ቀጥቃጭ እያሉት፣ ሸማ የሚሰራውን ቡዳ ነው እያሉ፣ሸክላ የሚሰሩትንም እንደዛው እያሉ ማንነታችንን ወሰዱት፤ እኛም እስካሁን ቁጭ ብለናል ስንሰዳደብና ስንጣላ እንዲሁ አለን። አሁን ያለው ትውልድ ደግሞ በዘመናዊ እውቀት ሄደዋል ለመረጃም ቅርብ ናቸው፣ግን የማንነት ችግር በጣም አለ። ኢትዮጵያዊ የሚባለው ነገር በጣም ያሰጋል፤ በኪ ነጥበብ ስራዎቻችን ላይም የራሳችን የሆኑ ብዙ የሚሰሩ ታሪኮች እያሉን የውጭ አድናቂ ሆነናል። ሙዚቃችን ፣ፊልሞቻችን ፣የመድረክ ቴአትሮቻችን በውርስ ትርጉም እየተጨናነቁ ነው ያሉት። እና እነዚህ ነገሮች ተንከባለው ተንከባለው የሆነ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ እፈራለሁ። ክፉ ትንቢትም እየተናገርኩ አይደለም ስለዚህ ሰው መልማት አለበት እላለሁ።

ቀም ነገር፡- በመጨረሻ የጠቅሳሳ ዕውቀት ጥያቄ ነው የቀረን፤ የመጀመሪያው የአሜሮ ልብ ወለድ መጽሐፍ ደራሲ ማናቸው?

ንብረት፡- አላቃቸውም።

ቀም ነገር፡- አመሠግናለሁ።

ገርገሴኖን የአዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማህበር

ስደሃ ችርነት የሚያደርግ ስእግዚአብሔር ያበድራል በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል። ምሳሌ 19:17

መልካም ማድረግን ስሌሎች ማካፈልን አትርሱ

ማህበሩ የጀመረውን መልካም ራዕይ የሚያከናውንበትን ቦታ ከመንግስት ወይም ከስጋሽ ግለሰቦች ጠይቆ ማግኘት።

ማህበሩ አድራሻ

ቁስቋም 17 ቁጥር ባስ ማዞሪያ ከፍ ብሎ ውሃ ከፍሉ ጎን

0118 70 39 27 አቶ መለስ አየለ 0912-18-88-76

0922-82-12-35 ፓስታ 31209 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

Email:gergesenon@gmil.com

ንብረት ገላው (እኩ)

‹አምባሳደር ነኝ›



ተወልዶ ያደገው ስዲስ ስበባ ፊደንሳዩ ስጋሲዩን ስካባቢ ስንቀዩ ምህደት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ስመገብ ነው። በልጅነቱ ከገመር በስንገድነት ወደ ቤታቸው የሚመጡ ሰዎችን ያነጋገር ዘዩቤ ስማስመሰል በመጣር ስቤተሰብና ስት/ቤት ጓደኞቹ ሲያሳዩ ገበዝ በርታ የሚል ስስተያየት በማግኘቱ ወደ ኪነ ጥበቡ እንዲሳብ ምክንያት እንደሆነው ደገልሳል። የዚህ እትም የመሻለኪያ ስምዶ እንግዳችን ሁስገብ ስርቲስት የሆነው ጋዜጠኛ፣ ደራሲ፣ ስዘጋጅ እና ተዋናዩ ንብረት ገላው ነው።

በፊደንሳዩ ኪነት ውስጥ የገመረን የሀገራችንን የቋንቋ ዘዩ ሲሰራ ያየው ስንድ ሰው ከስብረሃም ስስመሳሽ ጋር እንዲገናኝ ያደርገውና ሲትዩዲያ ፊዲዩ ገብች ስመስራት እድሱን ዩከፍትስታል። ከዚህ በኋሳ በበርካታ በቴሌቭዥንና ፊድዮና የማስታወቂያ ስራዎች ሳይ በድርስት፣ ስዘጋጅነትና በትወና ስርቷል። ስስብነትም ፊድዮ ፋና ሳይ በራሱ የቴስትር ፕሮሞሽን ስር በሚያቀርበው ‹ብረህ ተስፋ› በተስኝ ስካስ ጉዳተኞች ሳይ በሚያተኩር ፕሮግራም ሳይ ‹ጅረት› የተስኝ ሃምሳ ሁስት ተከታታይ ክፍል ያስው ድራማ ደራሲ፣ስዘጋጅ፣ተዋናይ በመሆን ፣ፖፕሌሽን ሚዲያ ሲያስተሳስፈው በነበርው ‹መንታ መንገድ› የፊድዮ ድራማ ሳይ በትወና፣ ሲትዮጲያ ፊድዎ የቀዳሚ መዝናኛ ፕሮግራም ሳይ ከስብረሀም ስስመሳሽ ጋር ስደጅም ዓመት ጭውውት በማቀረብና በስያዩ የሲኒማ ፊልሞችና የመጽሪክ ቲያትሮች ሳይ ስርቷል።

ንብረት ገላው በተስይም በህዝብ ዘንድ በጀንብ ያስተዋወቀውና ተወዳጅ ያደረገው በስሁኑ ወቅት ማክሰኞ ማታ በሲትዮጲያ ቴሌቭዥን በሚቀርበው ‹ቤቶች› የቤተሰብ ኮሜዲ ድራማ ሳይ በሚጫወተው ‹ስክ› የተስኝ ገፀ ባህሪ ነው። መጽሔታችንም ‹ከስክ ደክ ማን ችሎት በብልጠቱም ሆነ በጉልበቱ ከወንድ በላይ ስበጀ› ጋር ቆይታ ስድርጋስች።

ትዕግስት ታደስ

ቁም ነገር፡- አንድ ሰው ምች መታኝ ቢልህ ምን ትመክረዋስህ?

ንብረት፡- ምስክር ነበር? ብዬ እጠይቀዋስሁ። ለመክሰስ! /...ሳቅ/፤ ወይም ከቻልከው ሂድና ግጠመው ነው የምለው ፤እና እኔ ሄጄ ልጣላለት ኖሯል!

ቁም ነገር፡- በሀገራችን የቤት ሰራተኞችና የጥበቃ ሠራተኞች የሚገባቸውን ያህል ቦታ ተሰጥቷቸዋል ብለህ ታምናስህ ?

ንብረት፡- በፍጹም! እኔ እንደውም አንዳንድ ጊዜ አረብ ሀገር ከፎቅ ላይ ተጣሉ ምናምን እያልን ስናማርር አንድ ቀን ግን ለምን ራሳችንን ዞር ብለን አናይም እላለሁ። እዚህም አገር ላይ እንኳ በገዛ ወገኖቻቸው ሰራተኞቸው ላይ ምግብ ቆልፈው የሚሄዱ፣የሚደበድቡና እንደውም ሰራተኛ ሊቀጥሩ ሲሉ ትማራለች ከተባሉ የማይፈልጉ ሞልተዋል። በጣም የሞላና የተረፋቸው ውሻቸውን በቂቤ እያሻሹ በጣም በሚያሳፍር ሁኔታ ለዘበኞቸው ከውሻ ያነሰ ምግብ የሚሰጡ አሉ፡ ፡ በዛው ልክ ደግሞ እጅግ በጣም ጥሩ ሰዎች እንደውም ለቤተሰባቸው እስከ መዳር የደረሱ ጥሩ ሰዎችም ገጥመውኛል። አሁን እኔ የምናገረው እንደ ሙያዊ አስተያየት አይወሰድብኝና ቤቶች ላይ የምናየው ግንኙነት ትንሽ ለቀቅ ይላል። ይህ ደግሞ የሆነው የሚሰራው የኮሜዲ ስራ ስለሆነ በታሪኩ ውስጥ የሰራተኞቹ ከቤተሰቡ ጋር ያላቸው ግኑኙነት እንደዚህመሆኑ ወሳኝ ሆኖ ስለተገኘ ነው። እንጂ እንደዛ መሆን አለበት ማለት አይደለም።

ቁም ነገር፡- ገበጣ ፣ዳማ ፣ካርታ ልዩነታቸው ምንድ ነው ?

ንብረት፡- ምን አይነት የሚገርም ጥያቄ ነው የምጠይቂኝ? ገበጣና ዳማ የኢትዮጵያ ባህላዊ ጨዋታ ነው። በቅርቡ እንደውም አንድ ጥናት ላይ ተሳትፌ ነበር ፤‹የባህል ስፖርቶቻችን ለምን ቀሩ?› የሚባል እና ዳማም ኢትዮጵያ ውስጥ ጥንት ነገሥታቶች ይጫወቱት ነበር የሚልነገር አለ፤ ስለ ካርታ ግን አላውቅም፤ የሚመስለኝ የፈረንጆቹ ጨዋታ ነው :: እኔ እንደውም ካርታ ሲነሣ ቁማር ቀመስነቱ ነው ትዝ የሚለኝ (ይቅርታ ይደረግልኝና) /.....ሳቅ/፤ልዩነታቸው ካርታ በወረቀት ነው። ገበጣ በድንጋይ ነው በጠጠር፤ዳማም ጠጠር አለው።

ቁም ነገር፡- ከቤቶች ድራማ ጋር በተያያዘ የገጠመህ ነገር አስ?

ንብረት፡- ምን የማይገጥመኝ ነገር አለ ?ብዙ ነው። ድንገት ስጠየቅ አይመጣልኝም እንጂ፤አሁን እኔ ቤቶች ድራማ ላይ ልክ በቀረፃ ወቅት ልብሱን አንዴ ከለበስኩ በኋላ እራሱን እከን የዘሩ ሞላ ዘበኛ ነኝ፤ ማንም ይምጣ ማንም በዚያ ገፀ ባህሪ ውስጥ ሁኜ ነው የማዋራው። እና አንዳንዴ በቀረፃ ወቅት ሐያት አካባቢ ነው የምንቀረጽበት ቤት፤እየሰራን እንዳለ ቁራሌው የሚሉ ይመጣሉ፣ ልዋጭ የሚል ይመጣሉ፤ የዛኔ ድምጹ ይረብሸናል፤ እኔ እረፉ ልል እወጣለሁ፤‹አባካቸሁ ሥራ ይዘን ነው ዝም በሉ› ስላቸው ‹ባክህ አንተም ዘበኛ ነህ እኛም ቁራሌው› ይሉኛል። እንዲሁም እከን ሲያዩ በጣም የሚገረሙ ሰዎች አሉ፤በቅርቡ መኪናዬን አስነስቼ ስሄድ አንዲት ልጅ የእውነት በመገረም ዘበኛው እኮ ነው። በሚል ስትገረም አየኋት፤ ልክ ዘበኛ ሁኜ የባለቤቱን መኪና ሰርቄ እንደምነዳ አድርጋ ነው የቀወጠቸው፤ እንደዚህ አይነት ነገሮች በተደጋጋሚ ይገጥሙኛል።

ቁም ነገር፡- ሰዎች ወሸመጤን በጠሰው፤ ወሸመጤ ተበጠሰ ሲሉ እንሰማቸዋስን ፤ስመሆኑ ወሸመጥ የትኛው የአካሳችን ክፍል ነው?

ንብረት፡- ብዙ ቦታ ወሸመጥ እንዳለ ላስብና፤ አንደኛው ብብት ላይ አለ ወሸመጥ /....ሳቅ/፤ ሁለተኛው ደግሞ እግርና እግር መካከል ውስጥ ወሸመጥ አለ።

ቁም ነገር፡- በምድር ሳይ ስትመስከተው እጅግ የሚያስደንቅህ ነገር ምንድ ነው?

ንብረት፡- ሰው ነው የሚያስደንቀኝ ነገር። እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አድርጎ ፈጠረው የሚለው ነገር ያስደንቀኛል። በነገራችን ላይ እኔ ይሄ ሰው ከዝንጀሮ ነው የመጣው የሚል ሳይንስ አይመቸኝም ። እንደዚህ አይነት ሳይንስን ሲያንስ ነው የምለው፤እግዚአብሔር ሰውን ምን ያህል ቢወደው ነው እንዲህ አድርጎ የፈጠረው እላለሁ። ከፈጠረው በኋላ ጥበብን ጥግ ድረስ ሰጠውና፤ አሁን አውሮፕላን ላይ ሆነን ስናይ አቤት የሰው ልጅ ስራ እንላለን። ግን ሰው መፍጠርና እንዲት ጣታችን እንኳን ተቆርጣ መልሶ መፍጠር አልቻልንም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰው መፍጠር ያስደንቀኛል።

ቁም ነገር፡- እከን ብዙ ህፃናት ደወዱታል፤ ደህ የሆነው ስምን ይመስልሀል?

ንብረት፡- አዎ እኔ ብዙ ጊዜ ሕፃናት ፕሮግራም ላይ ተገኝቼ አውቃለሁ፤ ልክ ስገባ ይጮኻሉ፤ ይህንን እንግዲህ እኔ ክብር ለእግዚአብሔር ብዬ ማለፍ ነው የምችለው። ምክንያቱም የእከን ገፀ ባህሪ አይተሸው እንደሆን የሚጮህ ነገር ነው፣ ጀው ጃዋ ዓይነት ነገር ነው። ሕፃናት ደግሞ እንደዚህ አይነት ሰውን የመፍራት ነገር ነው ብዙ ጊዜ የሚታይባቸው፤ የግርቢጥ ብዬ ልገልጸው እችላለሁ በአማርኛ እከን ወደውታል። እውነቱን ለመናገር ልጆች ላይ በትወና ግብት ማለት ይከብዳል፤እንደ አዋቂዎቹ አይደለም ነገሩ፤ማለት የምችለው ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ፕሮዳክሽኑን የጀመረው ጥላሁን ጉግሳ ወዳጄ በጣም ጀግና ሰው ነው ለኔ፤ወቅታዊ ኮሜዲ ተከታታይ

ወደ ገፅ 35 ዞሯል